# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሰኞ | 83ኛ ዓመት ቁጥር 154 የካቲት 4 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!








## ዓድዋ የሚወሳው

### ሀገርን ለማዳን የተሰዉትን ጀግኖች ለማስታወስና የሚገባቸውን ክብር ለመስጠት ነው



**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- ዓድዋን የምናወሳው ሀገርን ለማዳን የተሰዉትን ጀግኖች ለማስታወስና የሚገባቸውን ክብርና ቦታ ለመስጠት ነው ሲሉ ፕሬዚዳንት ሣሕለወርቅ ዘውዴ ተናገሩ፡፡

የዓድዋ ድል መታሰቢያ በትናንትናው ዕለት ተመርቋል፡፡

ፕሬዚዳንት ሣሕለወርቅ ዘውዴ በመርሐግብሩ ላይ ተገኝተው ባደረጉት ንግግር፤ ዛሬ ዓድዋን የምናወሳው ሀገርን ለማዳን የተሰዉትን ጀግኖች ለማስታወስና የሚገባቸውን ክብርና ቦታ ለመስጠት ስለሚረዳ ነው ብለዋል።

የእኛ ብቻ ሳይሆን ለነፃነት እና ለሕዝቦች እኩልነት ለሚታገሉ ሕዝቦች ተስፋን የሰጠ ድል ይዘን እስከ ዛሬ ድረስ የሚዘከርበት ቦታ አለመኖሩንም ገልጸዋል። መታሰቢያው የመዲናዋ እንብርት የዘመቻው መሰባሰቢያ በሆነው ቦታ መገንባቱ ከፍተኛ ተግባር መሆኑንም ጠቅሰዋል።

ዓድዋ ለሀገራችን ብቻ ሳይሆን ለአህጉራችን ጭቆናን የቅኝ ግዛትን ለሚታገሉ ሕዝቦች ድል ነው ያሉት ፕሬዚዳንቷ፤ በመካከላችን ልንገነባ የምናስበው ግንብ ይቅርና የአፍሪካው ድል የሆነውን መያዝ ያስፈልጋል ብለዋል።

ዓድዋ አልገዛም አልበገርም ያለ ሕዝብ ግዙፍ ታሪክ መሆኑን ጠቅሰው ከታሪክ አንዳንድ ነገሮችን ብቻ መዘዝን የምንጨቃጨቅበት ሁኔታ የታሪክ ባለቤት

ዓድዋ የሚወሳው ሀገርን ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል











## ኢትዮጵያን ከነክብሯና ነፃነቷ ማሸጋገር

### እንዲቻል የዓድዋ ድል መታሰቢያ አስፈላጊ ነው

**- የዓድዋ ድል መታሰቢያ ተመረቀ**



**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያን ከነክብሯና ነፃነቷ ማሸጋገር እንዲቻል የዓድዋ ድል መታሰቢያ አስፈላጊ ነው ሲሉ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)ተናገሩ፡፡

የዓድዋ ድል መታሰቢያ በትናንትናው ዕለት በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እና ፕሬዚዳንት ሣሕለወርቅ ዘውዴ በትላንትናው ዕለት ተመርቋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በዓድዋ ድል መታሰቢያ ሥነ ሥርዓት ላይ ባስተላለፉት መልዕክት እንደገለጹት፡- ኢትዮጵያን ከነክብሯና ነፃነቷ ለቀጣዩ ትውልድ ማሸጋገር እንዲቻል የዓድዋ ድል መታሰቢያ በእጅጉ አስፈላጊ ነው፡፡

ኢትዮጵያን ከእነ ክብሯና ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

**"የዓድዋ ድል መታሰቢያ ኢትዮጵያውያን የጋራ ጥቅማቸው የሚከበረው በመተባበር እንጂ በመለያየት እንዳልሆነ ያሳየ የወል ምልክታችን ነው"**

*- የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት*

ገጽ 3

## ወደ እህትማማችነት ያደገውን የኢትዮጵያና ሩዋንዳ

### ግንኙነት ይበልጥ ለማሳደግ እየተሠራ ነው

**- 3ኛው የኢትዮጵያና ሩዋንዳ የጋራ የሚኒስትሮች ኮሚሽን ስብሰባ ተከፈተ**

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- ወደ እህትማማችነት ያደገውን የኢትዮጵያና ሩዋንዳ ግንኙነት ይበልጥ ለማሳደግ እየተሠራ መሆኑ ተገለጸ፡፡

3ኛው የኢትዮጵያና ሩዋንዳ የጋራ የሚኒስትሮች ኮሚሽን ስብሰባ በትናንትናው ዕለት ተከፍቷል፡፡ የሚኒስትሮች ኮሚሽን አካል የሆነው የከፍተኛ ኃላፊዎች ስብሰባም የተካሄደ ሲሆን፤ የሁለቱ ሀገራት የተለያዩ ተቋማት ተወካዮች ተገኝተዋል፡፡

በስብሰባው ላይ ንግግር ያደረጉት በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የአፍሪካ ጉዳዮች ዳይሬክተር አምባሳደር ፍስሐ ሻውል እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ ከሩዋንዳ ጋር ያላትን ቀጣናዊ ትብብርን ይበልጥ ማጠናከር ትፈልጋለች፡፡

ወደ እህትማማችነት ያደገውን ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል



አምባሳደር ፍስሐሻወል

## አጀንዳ 2063፤ ምን አሳካ፣ ምን ቀረ?

**ሄለን ወንድምነው**

የአፍሪካ ኅብረት 50ኛ ዓመቱን ሲያከብር የአፍሪካውያን አንድነትና ብልጽግና መገለጫ የሆነውን አጀንዳ 2063ን ይፋ አድርጓል፡፡ አጀንዳ 2063 አፍሪካውያንን በመሠረተ ልማት የማስተሳሰር፣ የሥራ አጥ ቁጥርን የመቀነስ፣ አፍሪካውያን ተመሳሳይ መገበያያ ገንዘብ እንዲኖራቸው የማድረግ፣ የአፍሪካ ኅብረትን ማጠናከር፣ ነፃ የንግድ ቀጣናዎችን መመሥረት እና ሌሎች በርካታ ግቦችን የሰነቀ ነው፡፡

አጀንዳ 2063 ይፋ ከተደረገ ጀምሮ ምን ምን እቅዶች ተሳኩ፣ ቀሪ ሥራዎች ምንድን ናቸው፣ ከኢትዮጵያስ ምን ይጠበቃል?

የፖለቲካ ሳይንስ መምህርና የፖሊሲ ጉዳዮች አማካሪ ቆስጠንጢኖስ በርኸተስፋ(ዶ/ር) እንደሚሉት አጀንዳ 2063 ለአፍሪካውያን እድገትና ይህ ካልሆነ

አጀንዳ 2063፤ ምን ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል






ወ/ሪት ስንዱ መኩሪያ

# የእናትነት ወር

## ለቅድመ ወሊድ ክትትል ትኩረት ሰጥቶ ተከብሯል

ዮርዳኖስ ፍቅሩ

አዲስ አበባ፡- በሀገራችን ለ18ኛ ጊዜ የተከበረው የእናትነት ወር ለቅድመ ወሊድ ክትትል ትኩረት የሰጠ እንደነበር የአዲስ አበባ አስተዳደር ጤና ቢሮ አስታወቀ።

በቢሮው የእናቶችና ሕፃናት ጤና ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ወይዘሪት ስንዱ መኩሪያ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ የእናትነት ወሩ ከጤና ሚኒስቴርና ከአጋር ድርጅቶች ጋር በመሆን በከተማዋ በሚገኙ 11 ክፍለ ከተሞችና 11 የመንግሥት ሆስፒታሎች ተከብሯል።

“ፍትሐዊ ተደራሽነትና ጥራት ያለው የቅድመ ወሊድ ክትትል በማስጀመር ጤናማ እናትነትን እናረጋግጥ” በሚል መሪ ቃል በተደረገው ንቅናቄ የቅድመ ወሊድ ክትትል ጠቀሜታ ላይ ሰፊ ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ ተሠርቷል።

እናቶች ካረገዙበት ሰዓት ጀምሮ ወይም ነፍሰ ጡር መሆናቸውን ካወቁበት ጊዜ ጀምሮ የቅድመ ወሊድ ክትትል መጀመር እንዳለባቸውም ተመላክቷል።

የቅድመ ወሊድ ክትትል የት ማግኘት እንደሚችሉና እናትና ልጅ ደህና መሆን እንዲችሉ ምን ያህል ጊዜ የቅድመ ወሊድ ክትትል ማድረግ እንደሚያስፈልግ እንዲሁም የወሊድ ክትትል አስቀድሞ መጀመር ምን ጥቅም አለው በሚሉት ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች ተሠርተዋል።

የሕይወት አጋር ወይም ባል እና ሌሎችም የቤተሰብ አባላት በቤት ውስጥ ነብሰ ጡር እናት በምትኖርበት ጊዜ የእሷም ሆነ የልጇ ጤና የተጠበቀ እንዲሆን በምን መልኩ በሐሳብና በተግባር ማገዝ እንዳለባቸውም ግንዛቤ ለመጨመር ጥረት ተደርጓል።

አንዲት እናት ለወሊድ ክትትል ወደ ጤና ተቋም ስትሄድ የትዳር አጋር አብሯት መሆኑ ለትዳር አጋሮችም ሆነ ወደፊት ለሚወለደው ልጅ ሊኖረው ስለሚችል ጠቀሜታም ግንዛቤን ለመፍጠር ጥረት ተደርጓል።

የቅድመ ወሊድ ክትትሉ ለእናቲቱና ለሚወለደው ጨቅላ ሕጻን ወሳኝ መሆኑን ያነሱት ዳይሬክተሯ በእናትና ልጅ ላይ ሊኖር የሚችልን የጤና እክልን መከላከል የሚቻለው የቅድመ ወሊድ ክትትል ማድረግ ሲቻል ነው ብለዋል።

ዳይሬክተሯ እንዳሉት፣ ሆስፒታሎች በአሁኑ ጊዜ የተሟላ የቅድመ ወሊድና የድረ ወሊድ የጤና አገልግሎት እየሰጡ የሚገኙ ሲሆን፣ አንዲት እናት ካረገዘችበት ወይም ነብሰ ጡር መሆኗን ካወቀችበት ጊዜ ጀምሮ የሕክምና ክትትል ማድረግ ይኖርባታል።

የቅድመ ወሊድ ክትትል የጨቅላ ሕጻናትን ሞት ለመቀነስ ትልቅ አስተዋፅዖ እንዳለው የጠቆሙት ዳይሬክተሯ በጤና ተቋማት በየጊዜው የሚሰጡ የግንዛቤ ማስጨበጫዎችን በሚገባ መከታተል ከማኅበረሰቡ የሚጠበቅ እንደሆነም መክረዋል።

በተሠራው የንቅናቄ ሥራ የመጣው ለውጥ በቀጣይ ወደ ጤና ተቋም የሚመጡ እናቶችን ቁጥር በማየት የሚገመገም ነው ያሉት ዳይሬክተሯ፣ የጤናማ እናትነት ወር ግን በጥር ወር ብቻ የሚከበር እንዳልሆነ ተናግረዋል።

የእናቶችና ሕጻናትን ጤና መጠበቅ የሁሉም ጤና ጣቢያዎችና ሪፈራል ሆስፒታሎች የሁልጊዜም ሥራና ኃላፊነት መሆኑን በመጠቆም የጤና ባለሙያዎች የቅድመ ወሊድ ክትትል ፋይዳን አስመልክቶ ለእናቶች በማስገንዘብ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ አደራ ብለዋል።

# በዞኑ ከ300 በላይ የገጠር ትምህርት ቤቶች ‘ቡኡረ ቦሩ’ ከፍተዋል

ውብሸት ሰንደቁ

ወሊሶ፡- በደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን 305 የገጠር ትምህርት ቤቶች ቡኡረ ቦሩ (የገጠር ትምህርት ቤቶች መዋዕለ ሕፃናት) ከፍተው አገልግሎት እየሰጡ መሆናቸውን የዞኑ አስተዳደር ገለጸ፡፡ በተያዘው በጀት ዓመት ብቻ 85 የገጠር ትምህርት ቤቶች ቡኡረ ቦሩ ከፍተዋል፡፡

በደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ቶሎሳ ተፈራ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በገጠር ትምህርት ቤቶች የቅድመ መደበኛ ትምህርት አለመሰጠቱ በትምህርት ጥራት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሲያመጣ ቆይቷል፡፡ የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ እንደመንግሥት ትኩረት ተሰጥቶ የሕፃናት ትምህርትን ባካተተ መልኩ የትምህርት ቤቶችን ደረጃ የማሻሻል ሥራ ተሠርቷል፡፡

በዚህም ዞኑ በገጠር ትምህርት ቤቶች የመዋዕለ ሕፃናት አገልግሎት የሚሰጡ ቡኡረ ቦሩ የሚሰኙ ማዕከላትን በማስፋፋት ላይ እንደሚገኝ አቶ ቶሎሳ ተናግረዋል፡፡

ይህ ርምጃ በገጠር አካባቢ የሚኖሩ ሕፃናት በከተማ ከሚኖሩት እኩል ፊደል ቆጥረው እንዲገቡ ያስቻለ መሆኑን ጠቅሰው፤ የትምህርት ጥራት ላይም አወንታዊ አስተዋፅዖ ይኖረዋል ብለዋል፡፡



አቶ ቶሉሳ ተፈራ

ዞኑ ባለፈው ዓመት ከ220 በላይ ትምህርት ቤቶች ቡኡረ ቦሩ ከፍተው ሕፃናትን እንዲያስተምሩ ማድረጉን ገልጸዋል፡፡

በዘንድሮው ዓመት ቀሪ 94 ትምህርት ቤቶች የቡኡረ ቦሩ ፕሮግራም እንዲከፍቱ ሲሠራ መቆየቱን ጠቅሰው፤ እስካሁን ድረስ 85 ያህሉ ተጠናቀው ሥራ መጀመራቸውን አብራርተዋል፡፡

በአጠቃላይ በደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን በገጠርና በከተማ የሚገኙ ከ400 በላይ ትምህርት ቤቶች የመዋዕለ ሕፃናትና የቡኡረ ቦሩ አገልግሎት እየሰጡ መሆናቸውንም አብራርተዋል፡፡

አቶ ቶሎሳ እንደተናገሩት፤ አርሶ አደሩ በሚገኝበት በገጠር አካባቢ መዋዕለ ሕፃናት አለመኖራቸው የአርሶ አደር ልጆች ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ ለፊደል አዲስ ሆነው ወደ መደበኛ ትምህርት ይገባሉ፡፡ ይህ የትምህርት ጥራቱ ላይ እክል ሲፈጥር ከመቆየቱም ባሻገር የተማሪዎች ሥነ ልቦና ላይ ጫና ነበረው፡፡

በዞኑ ከ450 በላይ ከመዋዕለ ሕፃናት እስከ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ያሉ ሲሆን ከ300 ሺህ በላይ ተማሪዎች ትምህርት እየተከታተሉ ነው፡፡

በተጨማሪም የዞኑ ተማሪዎች በትምህርታቸው ጎበዝ የሆኑት ተመርጠው በኢፋ ቦሩ ትምህርት የሚሰጣቸው መሆኑን አንስተዋል፡፡

በዞኑ ሦስት ቦታዎች ላይ የኢፋ ቦሩ ትምህርት ቤቶች እንዳሉ ጠቅሰው፤ በአጠቃላይ የኢፋ ቦሩ ትምህርት ቤቶች ከአንድ ሺህ በላይ ተማሪዎች እየተማሩ እንደሚገኙ አያይዘው ጠቅሰዋል፡፡

የትምህርት ጥራት በአንዴ የሚስተካከል ባይሆንም የእነዚህ ሥራዎች ድምር ለትምህርት ጥራት አወንታዊ አስተዋፅዖ ይኖረዋል ብለዋል፡፡



# በጋምቤላ የበጋ መስኖ ስንዴ ምርት የመሰብሰብ ሥራ በየካቲት መጨረሻ ይጀመራል

አመለወርቅ ከበደ

አዲስ አበባ፡- በጋምቤላ የበጋ መስኖ ስንዴ ምርት የመሰብሰብ ሥራ በተያዘው የየካቲት ወር መጨረሻ ሳምንት እንደሚጀመር የክልሉ እርሻና ተፈጥሮ ሃብት ልማት ቢሮ አስታወቀ፡፡

የክልሉ እርሻና ተፈጥሮ ሃብት ልማት ቢሮ ኃላፊ አቶ ኡጁሉ ሉአል ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በዘንድሮ የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ወደ 14 ሄክታር መሬት በዘር ተሸፍኗል፡፡

በአንድ ሄክታር መሬት 35 ኩንታል የስንዴ ምርት እንደሚጠበቅ የጠቆሙት አቶ ኡጁሉ፤ የደረሰውን ምርት ከማሰባሰብ በተጨማሪ 41 ሄክታር መሬት ላይ ተጨማሪ ስንዴ ለመዝራት ዝግጅት መደረጉን አመላክተዋል።

ለአካባቢው የሚስማማ የስንዴ ምርጥ ዘር ከግብርና ምርምር ተቋምና ከግብርና ኮርፖሬሽን ለማግኘት ጥረት እየተደረገ ነው ብለዋል።

በዘንድሮ የበጋ መስኖ ስንዴ ሥራ በክልሉ ሰፊ መሬት በስንዴ ምርት ለመሸፈን መታቀዱን የተናገሩት አቶ ኡጁሉ፤ ከአካባቢው ጋር የሚስማማ የምርጥ ዘር እጥረት በመኖሩ በሁለት ወረዳዎች ብቻ ስንዴው እንደተዘራና በሌሎች ሁለት ወረዳዎች ላይ ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ከአፈር ማዳበሪያ ጋር ተያይዞ አርሶ አደሮችን የማላመድ ሥራ እየተሠራ መሆኑን የቢሮ ኃላፊው አመላክተዋል።

በግብርና ሥራው የኤክስቴንሽን ሥራ የተዳከመ መሆን፣ ወጣቱ ለግብርና ሥራ ያለው አሉታዊ አመለካከት፣ ከምርጥ ዘር ጋር ተያይዞ ለአካባቢው ተስማሚ አለመሆን እና በአካባቢው ዘር የሚያባዙ ተቋማት አለመኖር በሥራው ላይ ተግዳሮት እንደሆነባቸው አንስተዋል፡፡

ይህንንም ችግር ለመቅረፍ እንደ ግብርና ቢሮ፤ የኤክስቴንሽን ሥራ አመራር ማጠናከር፣ የሥራ ባሕልን ለማምጣት የንቅናቄ ሥራ እንደሚሠራ ገልጸው፤ ለአካባቢው ተስማሚ የምርጥ ዘር ለማግኘት ከምርምር ተቋማት ጋር በመሥራት ላይ እንደሚገኙ አብራርተዋል፡፡

ኃላፊው እንደገለጹት፤ የግብርና ሥራን ከማዘመን አንጻር አርሶ አደሮች ትራክተር ተጠቅመው እንዲያመርቱ እየተደረገ ይገኛል፡፡ ከሠላም ሚኒስቴር የተበረከቱ 16 ትራክተሮች ድጋፍ ተደርጓል፡፡ በተያዘው ወር ትራክተሮቹ ወደሥራ እንዲገቡ ተደርጓል፡፡

ባለፈው ዓመት 36 ትራክተሮች በክልሉ የተለያዩ ወረዳዎች ለሚገኙ አርሶ አደሮች ተደራሽ መደረጋቸውን አመላክተዋል።

በአጠቃላይ በቅርቡ በክልል ደረጃ ድጋፍ የተደረገውን ጨምሮ፤ የኢንቨስተሮችን ሃብት ሳያካትት ከ52 በላይ ትራክተሮች በጋምቤላ መኖራቸውንና አሁን ላይ በተለያዩ የክልሉ አካባቢዎች የሚገኙ አርሶ አደሮች በስፋት እየተጠቀሙባቸው መሆኑን አስረድተዋል፡፡

ምርታማነትን ለማምጣት አርሶ አደሩ የሚሰጠውን የግንዛቤ ማስጨበጫ በአግባቡ ተከታትሎ ወደ ሥራ እንዲገባ ተጨማሪ ጥረት ያስፈልጋል ሲሉም ተናግረዋል።



አምባሳደር ሙክታር መሐመድ

# ሶማሊያ እንደሀገር ጸንታ እንድትኖር ኢትዮጵያ በርካታ ታሪካዊ ኃላፊነቶችን ተወጥታለች

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- ሶማሊያ እንደሀገር ጸንታ እንድትኖር ኢትዮጵያ በርካታ ታሪካዊ ኃላፊነቶችን እንደተወጣች በሶማሊያ የኢትዮጵያ አምባሳደር ሙክታር መሐመድ ገለጹ።

እንደ አምባሳደር ሙክታር መሐመድ ገለፃ፤ ኢትዮጵያ በሶማሊያ የእርስ በእርስ ጦርነት ሲከሰት በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሶማሊያውያንን ተቀብላ አስተናግዳለች። በዚህም በርካታ ሶማሊያውያን ኢትዮጵያን እንደሁለተኛ ሀገራቸው ቆጥረው ለብዙ ጊዜ በኢትዮጵያ ኖረዋል።

ኢትዮጵያ በሶማሊያ ሰላምና መረጋጋት እንዲፈጠር በርካታ የሰላም ድርድሮችን በአዲስ አበባ፣ በሐዋሳ እና በሌሎችም አካባቢዎችም ማዘጋጀቷን ጠቁመዋል፡፡

በዚህም ዓለም አቀፍ እውቅና ያለው የሽግግር መንግሥት ሞቃዲሾ ላይ ሊቋቋም ችሏል። የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊትም መስዋዕት ሆኗል። ይህ ባይሆን ኖሮ ሶማሊያ የአልቃይዳ መፈንጫ እና የሌሎች አሸባሪዎች መጠለያ ትሆን ነበር። ከዚህም በላይ ለሌሎች ሀገራት የፀጥታ ስጋት ትሆን ነበር ነው ያሉት።

እንደ አምባሳደር ሙክታር ገለፃ፤ በሶማሊያ የሽግግር መንግሥት በማቋቋም ሂደት ኢትዮጵያ የተለያዩ ተግባራትን አከናውናለች። ከዚህ ውስጥ ዓለም አቀፍ ሠላም አስከባሪዎች የሶማሊያን ሠላምና ደህንነት እንዲያስጠብቁ ረድታለች። በሶማሊያ ሕጋዊ መንግሥት ከተቋቋመ በኋላም የመጀመሪያውን ኤምባሲ የከፈተችውም ኢትዮጵያ ናት።

በዚህም ኢትዮጵያ የሶማሊያ አጋር ሀገር እንደሆነች ለዓለም ገልፃለች። ይህም ሌሎች የዓለም ሀገራት በሶማሊያ ኤምባሲ እንዲከፍቱ ተምሳሌትና አርዓያ መሆኗን የገለጹት አምባሳደር ሙክታር፤ ኢትዮጵያ ሶማሊያ እንደሀገር ጸንታ እንድትኖር በርካታ ታሪካዊ ኃላፊነቶችን ተወጥታለች ብለዋል።

አሁንም በሶማሊያ የኢትዮጵያ ሠላም አስከባሪ ሠራዊት እንደሚገኝ የጠቆሙት አምባሳደሩ፤ የባይደዋ ከተማ፣ የሂር ሸበሌ ግዛት ሥር ያሉ ከተሞችና የደቡብ ምዕራብ ግዛት ሥር የሚገኙ የሶማሊያ ከተሞች በኢትዮጵያ ሠራዊት እየተጠበቁ ነው። ቦታዎቹም አደገኛ ናቸው ብለዋል።

የኢትዮጵያ ሠራዊት በሶማሊያ ሠላም ከማስከበር ባለፈ የሶማሊያ ወታደሮችን የማሠልጠን ተግባር ሠርቷል። የሶማሊያ ወታደሮች ኢትዮጵያ መጥተው ሠልጥነዋል። ይህም ተግባር የሶማሊያ የሽግግር መንግሥት ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ እየተከናወነ የመጣ ነው ሲሉ አምባሳደር ሙክታር ገልጸዋል፡፡

እንደ አምባሳደር ሙክታር ገለፃ፤ ኢትዮጵያ የሶማሊያን ሉዓላዊነት የሚጋፋ ጥቅም ኖሯት ሳይሆን ከብሔራዊ ጥቅም አንፃር እንደሆነ ለማስረዳት ተሞክሯል። ይህም በአፍሪካ ኅብረት፣ በኢጋድ እና በሌሎችም ዓለም አቀፍ ተቋማት ተጠናክሮ ይቀጥላል። ሆኖም በዚህ ጉዳይ የአንዳንድ ሀገራት ጣልቃ ገብነት ይስተዋላል።

ነገር ግን ይህ ጣልቃ ገብነት የሶማሊያን ችግር ከማባባስ ባለፈ አንዳችም ጥቅም የለውም ያሉት አምባሳደሩ፤ እነዚህ ኃይሎችም ድብቅ አጀንዳቸውን ለማስፈጸም የሚጥሩ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡ ሶማሊያ ከብዙ መስዋዕትነት በኋላ ወደመረጋጋት እየመጣች ያለች ሀገር መሆኗንም አስረድተዋል።

# ‹‹ዓውደ ርዕዩ ኢትዮጵያ በዓለም የዲፕሎማሲ ዘርፍ ሰፊ አበርክቶ እንዳላት ያሳየ ነው››

*- አምባሳደር ሂሩት ዘመነ*
*በብራሰልስ የኢትዮጵያ አምባሳደር*

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- ዲፕሎማሲያችን ለብሔራዊ ጥቅማችን ዓውደ ርዕይ ኢትዮጵያ በአፍሪካ ብቻ ሳይሆን በዓለም ላይ በዲፕሎማሲው ዘርፍ ሰፊ አበርክቶ እንዳላት ያሳየ መሆኑን በብራሰልስ የኢትዮጵያ አምባሳደር ሂሩት ዘመነ ገለጹ ።

አምባሳደር ሂሩት ዘመነ ለኢፕድ እንደገለፁት፤ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር በመተባበር የተዘጋጀው ዓውደ ርዕይ ኢትዮጵያ በአፍሪካ ብሎም በዓለም መድረክ በዲፕሎማሲው ዘርፍ ያበረከተችውን አስተዋፅዖ ያሳየ ነው።

ኢትዮጵያ በዴሞክራሲው መስክ በርካታ እሴቶች ያላት ሀገር እንደመሆኗ ይህንን የበለጠ ውጤታማ ለማድረግ በዲፕሎማሲው ዘርፍ በርካታ ሥራዎችን እያከናወነች ትገኛለች ብለዋል።

ሀገሪቱ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት፣ በሊግ ኦፍ ኔሽን፣ በአፍሪካ አንድነት ድርጅት በኋላም በአፍሪካ ኅብረት፣ በኢጋድ እንዲሁም በርካታ ተቋማት ሲመሠረቱ የራሷን አስተዋፅዖ ያበረከተች መሆኗን የገለጹት



አምባሳደር ሂሩት፤ ይህም በታሪክ ተሰንዶ በዚህ መልኩ መቅረቡ ኢትዮጵያ በአፍሪካ ብቻም ሳይሆን በዓለም ላይ በዲፕሎማሲው ዘርፍ ሰፊ አበርክቶ እንዳላት ያሳየ መሆኑን አስረድተዋል።

እንደ አምባሳደሯ ገለፃ፤ ኢትዮጵያ ለረዥም ዓመታት በዲፕሎማሲው ዘርፍ ልትናገራቸው የምትችላቸውን በርካታ ታሪኮችን የከወነች ናት። ዓውደርዕዩም የተከወነውን ታሪክ ከማሳየት እና በገፅታ ግንባታ ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያበረክታል።

ኢትዮጵያ በዲፕሎማሲው መስክ ያልተቋረጠና ተከታታይ የሆነ እንቅስቃሴ እያደረገች ትገኛለች ያሉት አምባሳደሯ ፤ በቅርቡ ኢትዮጵያ የተቀላቀለችው ብሪክስ ተጠቃሽ መሆኑን ተናግረዋል። የብሪክስ አባል መሆን ማለት የቀድሞ ወዳጅ ሀገራትን ወደ ጎን መተው ሳይሆን ሁሉንም ያቀፈ የዲፕሎማሲ ሥራ በመከተልና ካለው ነባራዊ ሁኔታ ጋር አብሮ የሚሄድ ሥራ እየተከናወነ መሆኑን አብራርተዋል።

እንደ አምባሳደሯ አባባል፤ በዚህ ዓውደ ርዕይ በዋናነት የታየው ታሪክን ሰንዶ ማስቀመጥ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ነው። በዚህም የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ከውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ይህን ዓውደርዕይ ማዘጋጀቱ ምስጋና ይገባዋል።

“ዲፕሎማሲያችን ለብሔራዊ ጥቅማችን” በሚል በሳይንስ ሙዚየም የተከፈተው ዓውደርዕይ በተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች እየተጎበኘ ይገኛል። ዓውደ ርዕዩ እስከ ጥር 24 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ ክፍት ሆኖ የሚቆይ ይሆናል።

# “የዓድዋ ድል መታሰቢያ ኢትዮጵያውያን የጋራ ጥቅማቸው የሚከበረው በመተባበር እንጂ በመለያየት እንዳልሆነ ያሳየ የወል ምልክታችን ነው”

*- የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት*

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የዓድዋ ድል መታሰቢያ ኢትዮጵያውያን የጋራ ጥቅማቸው የሚከበረው በመተባበር እንጂ በመለያየት እንዳልሆነም ያሳየ የወል ምልክታችን ነው ሲል የኢፌዴሪ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት አስታወቀ።

የመንግስት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት የዓድዋ ድል መታሰቢያ ምርቃትን አስመልክቶ ትናንት ባወጣው መግለጫ እንዳስታወቀው፤ ታላቁ የዓድዋ ድል መታሰቢያ በዚህ መልኩ መጠናቀቅና ለምርቃት መብቃት ለጊዜያዊ ችግሮች እጅ ሳንሰጥ ትላልቅ ሀገራዊ ትልሞቻችንን እንደምናሳካ አስረጂ ድላችን ነው።

ለከፋፋይ ትርክቶች ሳንረታና ሳንበረከክ የወል ትርክቶቻችንን አፅንተን በዓድዋ ድል ዕሴቶች በጋራ ተንቀሳቀስን ጠንካራና የበለፀገች ኢትዮጵያን እውን ከማድረግ የሚያስቆመን ምድራዊ ኃይል እንደሌለ የዓድዋ ድላችን ማሳያ ነው ያለው መግለጫው፤ የዓድዋ ድል መታሰቢያ ፕሮጀክትም ይሄንን ታላቅ ድል የምንዘክርበት እና ለትውልድ የምናሻግርበት ታሪካዊ መዛግብታችን ነው ብሏል።

መግለጫው እንዳተተው፤ ኢትዮጵያ ጠንካራ ሥርዓተ መንግሥትና የጥንታዊ ሥልጣኔ ማዕከል ከነበሩ ሀገራት መካከል በግንባር ቀደምትነት ትጠቀሳለች። በዚህ ረዥም የታሪክ ጉዞ ኢትዮጵያ ሀገራችን ባሳለፈቻቸው የታሪክ ምዕራፎች ሁሉ ነፃነቷንና ሉዓላዊነቷን ለመጣስ ተከታታይ ወረራዎች ተፈጽመውባታል።

ይሁን እንጂ የተቃጡባትን ወረራዎችና ጦርነቶች በአኩሪ ተጋድሎና መስዋዕትነት በመመከት የዓለማችን የነፃነት ቀንዲል ለመሆን በቅታለች። ሕዝቦቿ የሰውን ሀገር ግዛት ወርረው የማያውቁና የራሳቸውንም ስንዝር መሬት ሳያስደፍሩ በአያሌ መስዋዕትነት ውስጥ አልፈዋል።

ዓድዋ ኩሩ ሕዝብ እና ነፃ ሀገር ያስረከበን የነፃነትና የድል ሰንደቅ ነው። ዓድዋ በሁሉም ኢትዮጵያውያን ደምና አጥንት የተገነባ የተጋድሎና የአይበገሬነት ዓርማ ነው። የዓድዋ ድል አባቶቻችን ለሀገራቸው ክብር ያለአንዳች ልዩነት በጋራ ደማቸውን አፍስሰው፣ አጥንታቸውን ከስክሰው ድል ያጎናፀፉን ብቻም ሳይሆን የወል እውነቶቻችንን በጠንካራ አለት ላይ እንዲገነቡ ያደረጉበት ድል ነው። በመሆኑም ዓድዋ ለእኛ ድልም ቅርስም ነው ሲል አትቷል።

ዓድዋ በኅብር የጸናች ሀገርን ለመፍጠር መሠረት የጣለና አሁንም የትውልዱ አሻራ ሆኖ የታላቋን ሀገር ትልቅ ስዕል የሚያሳይ የታሪካችን ዋነኛ ምዕራፍ ነው ያለው መግለጫው፣ ዓድዋ የማይደፈረውን የቅኝ ገዥዎችን የበላይነትና ፍላጎት መና ያደረገ፣ የታሪክ አንጓ ነው። ዓድዋ የጥቁር ሕዝቦች ኩራት፣ የአፍሪካውያን የትግል ዓርማና የመንፈስ ጥንካሬ ምንጭ በመሆኑ አስተሳሳሪ ቅርሳችን ነው ሲልም ዘርዝሯል።

ዓድዋ ኢትዮጵያውያንን ሁሉ በሀገር ፍቅር ገመድ ያሰናሰነ፣ የሀገር ሉዓላዊነትን ከአካባቢያዊ ልዩነት ያስቀደመ የነፃነት ብስራት ሲሆን፤ ለጠላቶቻችን ደግሞ ሀፍረትን ያከናነበ የኢትዮጵያ ኅብረብሔራዊ አንድነት የጸናበት የማዕዘን ድንጋይ ነው።

በአዲስ አበባ ከተማ በመሐል ፒያሳ የተገነባው የዓድዋ ድል መታሰቢያ ፕሮጀክትም የዚሁ የወል እውነት ዋና አካል መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል። ፕሮጀክቱ የዓድዋ ድልን በሚመጥን ደረጃ ተገንብቶ ለእይታ መብቃቱ የጋራ ድሎችንን በማጉላት፣ ከፋፋይ ትርክቶችን በዘላቂነት በማክሰም የወል ትርክቶች እንዲገነቡና ወደ ትውልድ እንዲተላለፉ በማድረግ የኢትዮጵያን ኅብረ ብሔራዊ አንድነትና ወንድማማችነት ስር እንዲሰድ በማድረግ ረገድ ከፍተኛ ፋይዳ ይኖረዋል።

የዓድዋ ድል ለኢትዮጵያውያን ብቻም ሳይሆን ለጥቁር ሕዝቦች የትግል ዓርማና የመንፈስ ጥንካሬ ምንጭ ነበር። የዓድዋ ድል መታሰቢያ የአፍሪካ መዲና በሆነችው አዲስ አበባ እምብርት መገንባቱ ለኢትዮጵያውያን መታሰቢያነት ብቻም ሳይሆን ለነፃነታቸው ለተዋደቁ አፍሪካውያን ወንድሞችም ጭምር መሆኑን ያሳያል። የአፍሪካ ኅብረት መቀመጫ የሆነችው አዲስ አበባችን፤ የአፍሪካ ድል የሆነውን የዓድዋ ድል የሚዘክር ፕሮጀክት እውን ማድረጓ ያላትን አፍሪካዊ ዕሴት የበለጠ ያጎላዋል።

ፕሮጀክቱ እንደሌሎች ሀገራዊ ፕሮጀክቶች ሁሉ የጀመርነውን እንደምንጨርስ፣ ቃል የገባነውን በላቀ ጥራት እንደምንፈፅም የሚያመላክት ሌላኛው ምስክር ነው ያለው መግለጫው፤ የፕሮጀክቱ እውን መሆን ኢትዮጵያ ትልቅ ዓልማ እንደምትፈጽም የሚያመላክት ስኬት ነው ሲል አስፍሯል።

# ኢትዮጵያ እንደ ሀገር እንድትቀጥል የውጭ ግንኙነቱና ዲፕሎማሲው ትልቅ አስተዋፅዖ አበርክቷል

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ እንደ ሀገር እንድትቀጥል የውጭ ግንኙነት ዘርፉና ዲፕሎማሲው ትልቅ አስተዋፅዖ አበርክቷል ሲሉ የአፍሪካ ቀንድ ተንታኝ በለጠ በላቸው (ዶ/ር) ገለጹ።

“ኢትዮጵያና ጎረቤቶቿ፤ የትብብርና የውዝግብ አዙሪት” የተሰኘውና በበለጠ በላቸው (ዶ/ር) የተጻፈው መጽሐፍ ሰሞኑን ተመርቋል።

የውጪ ፖሊሲ ባለሙያና የአፍሪካ ቀንድ ተንታኝ እንዲሁም የታሪክ ተመራማሪ አማካሪና ጸሐፊ በለጠ በላቸው (ዶ/ር) የመጽሐፉን ጭብጦችና ወቅታዊውን የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ ሁኔታ አስመልክተው ለኢፕድ እንደገለጹት፤ እንደ ሀገር ለመቀጠላችን የውጭ ግንኙነት ዘርፉና ዲፕሎማሲው ትልቅ አስተዋፅዖ አበርክቷል።

በለጠ (ዶ/ር) እንደገለጹት፤ በተደረገው ትግል ሀገሪቱን ከተጨማሪ ጫናዎችና ጥቃቶች መከላከል ተችሏል። ይህንን አጠናክሮ ማስቀጠሉ አዋጭነቱ አጠያያቂ አይደለም። የቀደሙ አካሄዶችን መረዳቱ ብሎም ድክመቶችንና ስህተቶችን ለማረም መዘጋጀቱም ቀጣይ እንቅስቃሴዎችን በአግባቡ ለማካሄድ ዕድል ይፈጥራል።

እንደ ባለሙያው ገለጻ፤ ኢትዮጵያ የሚገጥማት የውጭ ግንኙነት ተግዳሮት አዲስ አይደለም፤ ሁልጊዜም ቢሆን ከጎረቤት ሀገራትም ሆነ ከሌሎች የዓለም ሀገራት ጫናና ግፊት ይደርስባታል። ከአንዳንዶቹ ጋር መልካም ግንኙነት ይኖራታል፤ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ወደ ውዝግብ የሚሄዱ ጉዳዮች ያጋጥማሉ። በዚህ ውስጥ ኢትዮጵያ እንደ ሀገር እንድትቀጥል የውጭ ግንኙነቱና ዲፕሎማሲው ትልቅ አስተዋፅዖ አበርክቷል። በመሆኑም ከቀደሙት ልምድ ወስዶ አሁን ላይ እያጋጠሙ ያሉ ችግሮችን ማስተካከል ይገባል።

ዛሬ ላይ የሚሠሩ ስህተቶች እንደ ትላንቱ ሁሉ ዋጋ እንዳያስከፍሉ ማሰቡ ብልህነት ነው ያሉት ዶክተር በለጠ፤ ከውጭ ግንኙነትና ዲፕሎማሲ አንጻር የሚጠበቅብንን ብርቱ ትግል ማድረግ እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል። የእርሳቸው መጽሐፍም አካዳሚያዊና የፖሊሲ እሳቤዎችን በጣምራ ያስተናገደና ይህንኑ ጉዳይ የሚመለከት ስለመሆኑ ጠቁመዋል።

አንዳንድ የተዛቡ የሚመስሉ አካሄዶች ከተለዋዋጭ የየመንግሥታት የግንኙነት ባሕሪ እንደሚመነጩ በመግለጽ፤ የቀደሙት የሚችሉትን ያህል መጣራቸውንና የሀገራቸውን ክብርና ጥቅም ለማረጋገጥም መስዋዕትነት መክፈላቸውን ጠቅሰው፤ የአሁንና ቀጣይ ትውልዶች ይህንን በማስቀጠል፤ የቀደሙ ድክመቶችን በማሻሻል ተጨማሪ ውጤት ለማስመዝገብ ጥረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል ነው ያሉት።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እንደሚስተዋለው ፈተናውም ሆነ ትግሉ እየተወሳሰበ ከኢትዮጵያ የሚጠበቀው ዝግጁነትም እያደገ መምጣቱን ገልጸዋል። ለዚህ የሚበቃ ቁመና እና ብቃት ላይ መገኘትን መፈተሹ አጣዳፊ የቤት ሥራ መሆኑን ተናግረዋል።



ፎቶ ገበበ ገብሬ

በለጠ በላቸው (ዶ/ር)

“ችግር ውስጥ የምንገባው የውስጥ አቅማችን ደካማ በሚሆንበት ጊዜ ነው” በማለት፤ ትልቁ ሥራ የውስጥ ችግሮችን መፍታት እንደሆነ መክረዋል።

መጽሐፉ ኢትዮጵያ በተለያዩ ወቅቶችና መንግሥታት ከጎረቤት ሀገራት ጋር የነበራትን ታሪካዊና ዲፕሎማሲያዊ የግንኙነት ሂደቶችና ክንውኖችን በስፋት የዳሰሰ ሲሆን፤ አሁናዊውን የውጭ ግንኙነትና ወደፊት ልትከተላቸው ስለሚገቡ አካዳሚያዊና የፖሊሲ እሳቤዎች በጣምራ መካተታቸውንም አብራርተዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## በፍትሐዊነትና በጋራ ተጠቃሚነት መርህ የተቃኘው የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ ውጤታማ ጉዞ ተጠናክሮ ይቀጥል!

ኢትዮጵያ የቀደምትነቷ አንድ ማሳያ ከሚሆኗት ጉዳዮች መካከል አንዱ የዲፕሎማሲና የውጭ ግንኙነት ተግባሯ ነው፡፡ የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነትና ዲፕሎማሲ ጉዞ ጅማሮው ከንግሥተ ሳባ የእሥራኤል ጉዞ ታሪክ ጋር የተቆራኘ ስለመሆኑም የተለያዩ ድርሳናት ያስረዳሉ፡፡ ይሄ ማለት ዛሬ ላይ ኃያል፣ የውጭ ግንኙነትና ዲፕሎማሲውም ፊታውራሪ ነን የሚሉ አንዳንድ ሀገራት እንኳን እንደ ሀገር ከመፈጠራቸው በፊት ማለት ነው፡፡

ይሄ የውጭ ግንኙነትና የዲፕሎማሲ ጉዞዋ ታዲያ እንደየዘመኑ እና እንደ ሀገሪቱ የሥርዓተ መንግሥታት እሳቤ በልኩ እየተመራ እና በውጤት እየታገዘ ዘልቋል፡፡ ይሄ ጉዞም በአንድ በኩል ኢትዮጵያ በተናጠል ከሀገራት ጋር ተባብራ የምትሠራበትን አቅም ሲሰጣት፤ በሌላ በኩል ቀጣናዊ፣ አህጉራዊ እና ዓለምአቀፋዊ ጉዳዮች ላይ ከተናጠል ይልቅ በባለ ብዙ ወገን ትብብር ታግዛ መሥራት የሚያስችላትን ዕድል ሰጥቷታል፡፡

ለዚህ ደግሞ ከኢጋድ እስከ ተመድ ያሉ የባለ ብዙ የትብብር መድረክን የሚሰጡ ተቋማት እንዲፈጠሩ በማድረግ ሂደት ውስጥ የላቀ አበርክቶን ያደረገች ሲሆን፤ በእነዚህ ተቋማት አማካኝነት የሚከወኑ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊም ሆኑ የሰላምና ፀጥታ ጉዳዮች ፍትሐዊነትን የተላበሱ፤ የጋራ ተጠቃሚነትን ያሰፈኑ እንዲሆኑም የበኩሏን ተወጥታለች። በተለይ ገለልተኛ የሆነው የውጭ ግንኙነትና ዲፕሎማሲ አካሄዷ ከነባሮቹ ባለፈ እንደነ ብሪክስ ካሉ አዳዲስና ሚዛን አስጠባቂ ኃይሎች ጋር በትብብር የምትሠራበትን የተፈላጊነት ገጽ ፈጥሮላታል፡፡

በባለብዙ መድረክነቱም፣ በሁለትዮሽ የትብብር መድረክም ሆኖ ከሚገለጸው የውጭ ግንኙነትና ዲፕሎማሲ አውድ ደግሞ፤ ኢትዮጵያ ከአፍሪካውያን ጋር የሚኖራት አሕጉራዊ፣ ቀጣናዊ እና ተናጠላዊ (ከሀገራት ጋር በተናጥል የምታደርገው) የትብብር ግንኙነቷ አንዱ ነው፡፡ በዚህ ረገድ ኢትዮጵያ በአንድ በኩል ከአፍሪካውያን ጋር በማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ ብሎም ሰላምና ጸጥታ ጉዳዮች ላይ በጋራ መሥራትን፤ በሌላ በኩል አፍሪካውያን በአንድ ተደምረው በሚፈጥሩት ኃይል ዓለምአቀፍ ተጽዕኖ ፈጣሪነታቸውን ማሳደግን ታሳቢ ያደረጉ ሥራዎችን እያከናወነች ትገኛለች፡፡

ለምሳሌ፣ አፍሪካውያን አጀንዳ 2063ትን ተልመው እየተገበሩ ይገኛሉ፡፡ ይሄ ደግሞ ሰላምን፣ ልማትንና ሰብዓዊ ልማትን፣ በጥቅሉ ሁለንተናዊ ብልጽግናን እውን የማድረግ ዓላማን የያዘ ነው፡፡ ኢትዮጵያም ይሄንን ታሳቢ ያደረጉ በርካታ ተግባራትን እያከናወነች ትገኛለች፡፡ ለምሳሌ፣ አፍሪካን በሁሉም መልክ በመሠረተ ልማት የማስተሳሰር ተግባሯ አንዱ ሲሆን፤ ይሄ ትስስርም የአህጉሪቱን ሀገራት የጋራ ተጠቃሚነትን እውን በሚያደርግ መልኩ እየተፈጸመ ያለ ነው፡፡

የዚህ ተግባሯ ማሳያ ሆነው ከሚገለጹት መካከል፣ የትራንስፖርት (የመንገድ፣ የባቡር፣ የአየርና ሌሎችም)፣ የኤሌክትሪክ ኃይል፣ የመጠጥ ውሃና መሰል ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ያላቸው መሠረተ ልማቶች ተጠቃሽ ናቸው። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ከሰሞኑ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተገኝተው እንደተናገሩት ታዲያ፣ ይሄ ከጎረቤት ሀገራት ጀምሮ ቀጣናዊም ሆነ አህጉራዊ ትስስር፣ ትብብርና የጋራ ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጠው ጉዞዋ ቀጥሎ የኤሌክትሪክ ሽያጭ ስምምነት ከታንዛኒያም ጋር በቅርቡ ይፈረማል። ይሄ ደግሞ ቀጣይ ወደ ደቡብ አፍሪካ ቀጣና ለመራመድ ዕድል ይሰጣል። በዚህ መልኩም የአፍሪካውያንን ልማትና የጋራ ጥቅም ለማሳደግ ያግዛል።

ከዚህ በተጓዳኝ ኢትዮጵያ አፍሪካውያንም ሆኑ ሌሎች በማደግ ላይ ያሉ ሀገራት አህጉር ዘለልና ዓለምአቀፋዊ በሆነው የሁለትዮሽና የባለብዙ ወገን ዲፕሎማሲያቸው ፍትሐዊነት የሰፈነበት፣ የጋራ ተጠቃሚነትን ማዕከል ያደረገ እንዲሆን የማይተካ ሚናዋን እየተወጣች ትገኛለች፡፡ በዚህም የራሷን የዲፕሎማሲና የውጭ ግንኙነት መሥመር ከወገንተኝነት የጸዳ ሆኖ እንዲጓዝ ከማድረጓ ባሻገር፤ አፍሪካ ዓለምአቀፍ ተደማጭነትና ተጽዕኖ ፈጣሪነቷ እንዲያድግ፤ ሌሎች አዳጊ ሀገራትም እንደ ሀገር የራሳቸው ጥቅምና ፍላጎት ተከብሮላቸው እንዲጓዙ ከፍ ያለ ሥራን ስታከናውን ቆይታለች፤ እያከናወነችም ትገኛለች፡፡

ይሄ ገለልተኛ ሆኖ የመሥራት አቋሟ እና የጋራ ተጠቃሚነት ላይ የተመሠረተው የዲፕሎማሲ መሥመሯ ታዲያ፤ ለራሷ ዘርፈ ብዙ ጥቅምን፤ ለአፍሪካም መልካም ዕድልን፤ ለታዳጊ ሀገራትም በጎ እይታን ፈጥሯል፡፡ ምክንያቱም፣ ይሄ አካሄዷ ለኢትዮጵያ እንደ ሀገር ዘርፈ ብዙ ችግሯቿን የምትሻገርበት የዲፕሎማሲ አቅም ሲሰጣት፤ ለአፍሪካ እንደ አህጉር ሊጠበቅላት የሚገባው ጥቅም እንዲከበር የሚያስችል መንገድ አስጀምሯል፡፡ አዳጊ ሀገራትም የራሳቸው ጥቅምና ፍላጎት የሚከበርበትን የዲፕሎማሲ መንገድ እንዲመለከቱ አስችሏቸዋል፡፡

በዚህም ኢትዮጵያ ከሀገራት ጋር ያላት የሁለትዮሽ ትብብር ከዕለት ዕለት ከፍ እያለ እና በላቀ የወዳጅነትና የተባባሪነት መንፈስ እንዲቃኝ ሆኗል፡፡ ከኢጋድ እስከ ተመድ፤ ከአፍሪካ ልማት ባንክ እስከ የዓለም ባንክ፤ ከዓለም የምግብ ድርጅት እስከ የዓለም የገንዘብ ድርጅት፣... ሁሉም ኢፍትሐዊነት እየታገሉና እየቀረፉ ከሁሉም ለሁሉም የሚሆኑበትን መንገድ እንዲመለከቱ ለማድረግ እየሠራች ትገኛለች፡፡ የዚህ ሥራዋን ፍሬም ማጣጣም ጀምራለች፡፡

እነዚህና መሰል በትብብር እና በጋራ ተጠቃሚነት ላይ የተቃኙ፣ የተቋማት አሠራር ፍትሐዊነትን ለመፍጠር የሚደረጉ የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት እና ዲፕሎማሲ ፍሬዎች ከትናንት የቀጠሉ፤ ዛሬም በውጤት የታጀቡ ሆነው ተገልጠዋል። በመሆኑም ይሄ የትናንት ወረት፤ የዛሬ ውጤት የሆነው ጉዞ፤ ለነገው መንገድ ወረቱንም ውጤቱንም አቅም አድርጎ ሊጠቀም፤ ለውጭ ግንኙነትና ዲፕሎማሲው የፍትሐዊነትና የጋራ ተጠቃሚነት መርህ መጠናከር መትጋት ከሁሉም ይጠበቃል!


## አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ዲፕሎማሲ እና አሁናዊ የኢትዮጵያ ሁኔታ

ክብረ መንግስት

ዲፕሎማቶችና የፖለቲካ ምሁራን እንደሚሉት፤ የዲፕሎማሲው ዘርፍ በዋናነት የሚያተኩረው ወዳጅና ጠላት የሚለውን ሳይሆን ብሔራዊ ጥቅም እና ሉዓላዊነትን ነው። ከዚህ አንጻር ለሀገር ክብርና ጥቅም ሲባል የሚደረሱ ስምምነቶች እና ውሳኔዎች አሉ ፤ ወደፊትም ይኖራሉ፡፡

ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ሀገራት ያላቸውን ፀጋዎች ለመጋራት፤ የጎደላቸውን ለማሟላት አስተዋጽአው የማይተካ ነው፡፡ ከዚህ የተነሳም ሁሌም ዘመኑን የዋጀ ሁነኛ የዲፕሎማሲያዊ ስትራቴጂዎችንና መርሆችን ነድፎ በአግባቡ መጓዝ ከምንም በላይ ለዛሬው ሆነ ለነገው የሀገር ኃያልነት ወሳኝ ነው፡፡

ዲፕሎማሲ በሀገራትና መንግሥታት እንዲሁም በዓለም አቀፍ ተቋማት መካከል የሚካሄድ ዘርፈ ብዙ የውጭ ግንኙነቶች የሚከወኑበት ሁነኛ ጥበብ ነው፤ የዲፕሎማሲ ዋና ተግባርም በሀገራት መካከል ዓለም አቀፍ ግንኙነቶችን ማስተዳደር እና ሰላማዊ ግንኙነትን ማረጋገጥ ነው፡፡

የንግድ ስምምነት ድርድሮችን፣ በጋራ ችግሮች ዙሪያ ውይይትን፣ አዳዲስ ፖሊሲዎች መተግበርን እና አለመግባባቶችን በሰላማዊ መንገድ መፍታትን የመሳሰሉ አንኳር የዲፕሎማሲ መርሆችን ተከትሎ መሥራት ነው። ይህ ደግሞ ለኢትዮጵያ አዲስ ሥራ አይደለም፡፡ የሺህ ዓመታት ጉዞ ነው፡፡

በዲፕሎማሲ ግንኙነት ውስጥ ተጋግዞ የመለወጥ መርህ፤ የተሻለውን መምረጥና መያዝ የተለመደ ነው። ከዚህም ባለፈ ወዳጅን ማብዛት፣ «የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው ...» የሚሉ በዲፕሎማሲያዊ ግንኙነቶች ውስጥ ትልቅ ስፍራ የሚሰጣቸው፤ ሀገራት ትኩረት ሰጥተው የሚንቀሳቀሱባቸው ጉዳዮች ናቸው፡፡

ሀገራችን ኢትዮጵያ ከቀደመው ዘመን ጀምሮ ገለልተኛ እና ወዳጆችን በማስፋት ላይ የተመሠረተ ዲፕሎማሲ ብትከተልም፤ የዓድዋን ድል ተከትሎ የራሷን ነፃነት ከማስጠበቅ ባለፈ የአፍሪካውያን ነፃነት ጭምር አንቀሳቃሽ ሞተር መሆን መቻሏ፤ በበርካታ የምዕራቡ ዓለም ሀገራት ባልተገባ ዓይን እንድትታይ፤ ከፍ ባለ ያልተገባ ዲፕሎማሲ ጫና ውስጥ እንድትገባ እንዳደረጋት ብዙዎች ይስማማሉ፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ያላት የተፈጥሮ ሀብትና የምትገኝበት ጂኦፖለቲካል አቀማመጥም ፤«የዝሆን ሞት ምክንያቱ የራሱ ጥርስ ነው፡፡» እንደሚባለው በዓለም አቀፍ ደረጃ /ዲፕሎማሲያዊ ጫና እንዲበረታባት፤ በየዘመኑ ላጋጠማት ሀገራዊ ፈተናዎች ምክንያት እየሆነባት ነው፡፡

ሀገሪቱ የዓለም 60 በመቶ ንግድ በሚንቀሳቀስበት የቀይ ባሕር ቀጣና የምትገኝ፤ የረጅም ዘመናት የሀገረ መንግሥት ታሪክ ባለቤት መሆኗም፤ እድገቷን በማይፈልጉ ታሪካዊ ጠላቶቿ እና የነሱን ፍላጎት በማሟላት ተጠቃሚነታቸውን ለማጽናት በሚፈልጉ ኃይሎች በጥርጣሪና በጠላትነት ለመታየት ተገዳለች።

በዚህም ሀገሪቱ እንደ አንድ ሉአላዊት ሀገር አንድ የሆነ ፕሮጀክት ነድፋ ተግባራዊ ለማድረግ ስትነሳ ከተለያዩ አቅጣጫዎች የተለያዩ ጫናዎች ሲደረጉባት መመልከት የተለመደ ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ የዓባይን ወንዝ በተመለከተ በሀገሪቱ ላይ እየደረሰ ያለውን ጫና ማየት በቂ ነው።

በኢትዮጵያ እና በግብጽ መካከል በዓባይ ወንዝን ውሃ አጠቃቀምን አስመልክቶ ያለው አለመግባባት ምን እንደሚመስል፤ አሁን ባለንበት የሰለጠነው ዓለም አለመግባባቶቹ ለዘለቄታው በምን መፈታት እንዳለባቸው ዓለም አቀፉ ኅብረተሰብ ባእድ ይሆናል ተብሎ አይታሰብም።

ይህም ሆኖ ግን የስዊዝ ካናል ከተከፈተ ማግስት ጀምሮ አንዳንድ ምዕራባውያን ግብጽን በማስደሰት የካናሉ የተሻለ ተጠቃሚ ለመሆን በኢትዮጵያ ላይ በሕግም በሞራልም አግባብነት የሌላቸው የተለያዩ ጫናዎችን ሲፈጥሩ ይስተዋላሉ፡፡ ኢትዮጵያ የራሷ የተፈጥሮ ሀብት በሆነው የዓባይ ወንዝ እንዳትጠቀም ለዘመናት ስታሴር ለኖረችውና ዛሬም እያሴረች ላለችው ግብጽ ሲወግኑ ማየትም የተለመደ ነው፡፡

> **ሁሌም ዘመኑን የዋጀ ሁነኛ የዲፕሎማሲያዊ ስትራቴጂዎችንና መርሆችን ነድፎ በአግባቡ መጓዝ ከምንም በላይ ለዛሬው ሆነ ለነገው የሀገር ኃያልነት ወሳኝ ነው**

ኢትዮጵያ የዓባይን ወንዝ በመጠቀም የዜጎቿን ሕይወት የመለወጥ ሙሉ መብት አላት፤ ይህንን የተፈጥሮ ፀጋዋን በፍትሐዊነት መርህ አልምታ እንዳትጠቀም የሚከለክላት የሕግ ሆነ የሞራል ክልከላ የለባትም። በዚህ ጉዳይ የሚመጡ ተጽእኖዎች የጊዜ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር በአዲስ ዘመን እሳቤ ብዙ የሚያራምዱ አይደሉም።

በርግጥ ሀገሪቱ የተፈጥሮ ፀጋዎቿን በማልማት ልትፈጥረው የምትችለው ተፅእኖ ፈጣሪነት ስጋት ለሚሆንባቸው ኃይላትና ሀገራት፤ ጉዳዩን በዝምታ ያዩታል ተብሎ የሚታሰብ አይደለም፤ የማልማት/መልማት አስተሳሰቡ በራሱ ሊያመጣ የሚችለው ተግዳሮትም ቀልሎ የሚታይ አይደለም ።

ኢትዮጵያ እነዚህን ጫናዎች ባላት የዘመናት የዲፕሎማሲ ተሞክሮ ለማርገብ ረጅም መንገዶችን ተጉዛለች፤ በዚህም በየዘመኑ ያስመዘገበቻቸው ስኬቶች፤ ዛሬም በዲፕሎማሲው ዘርፍ ዓለም አቀፍ እውቅና እንዲኖራት አስችሏታል። ብሔራዊ ጥቅሞቿን በማስጠበቅ ሂደትም ዋነኛ አቅም ሆኗታል።

አሁን አሁን «ለአፍሪካዊ ችግር አፍሪካዊ መፍትሄ» በሚል መርህ አፍሪካዊ አለመግባባቶች /በዓባይ ወንዝ ውሃ አጠቃቀም ዙሪያ ያለው አለመግባባትም ጭምር /ከአፍሪካዊ ተቋም እና አፍሪካውያን እጅ እንዳይወጣ በማድረግ በአደራዳሪነት ስም ገብተው ጉዳዩን ወዳልተፈለገ አቅጣጫ ሊወስዱ የሚፈልጉ አካላት ፍላጎት እንዳይሳካ አድርጋለች።

በተለይም በቀጣይ በዓባይ ወንዝ ውሃ አጠቃቀም ዙሪያ የሚደረጉ ድርድሮች ፤ ዓለም አቀፍ የድንበር ተሻጋሪ ወንዞች ውሃ አጠቃቀም መርህን እና ሕግን በተከተለ መንገድ በአፍሪካውያን እና አፍሪካዊ ተቋም ብቻ እልባት እንዲያገኝ እየሰራች ነው፡፡ ይህ ድል ዝም ብሎ የመጣ ሳይሆን የዘመናት የዲፕሎማሲያዊ ጥበብ/ተሞክሮ ውጤት ነው፡፡

ከ2010 ዓ.ም ጀምሮ የገጠሟትን ዓለም አቀፍ ጫናዎችን ለመቋቋም፣ ኢኮኖሚያዊ ግቦቿን ለማሳካት፣ ከሀገራት እና ዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር በትብብር ለመሥራት በዲፕሎማሲው ዘርፍ የፈጠረችው ስኬት ዋነኛ ተጠቃሽ ነው፡፡ በነዚህ ጊዜያት እንደ ሀገር በርካታ ዲፕሎማሲያዊ ሁነቶች ተከስተዋል፡፡ በዘርፉ የውጭና የውስጥ ተግዳሮቶችን በመቋቋም በርካታ ውጤታማ ሥራዎች ተከናውነዋል፡፡

# ኢትዮጵያን ከነክብሯና...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

"አሁን ያለው መንግሥት ላይመች ይችላል፤ ግን ኢትዮጵያ ሁሌም ትመቻለች" ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ "ባለን የመንግሥት ቅሬታ ይህን የዓድዋ ድል መታሰቢያ ማጣጣል፤ ለነፃነታችን ዋጋ የከፈሉ አባቶቻችንን ሥጋና ደም ማራከስ ነው" ብለዋል።

አሁን እኛ ዓለም የደረሰበትን ቴክኖሎጂ ወርሰን ሀገራችንን የማናለማ ከሆነ፣ የአባቶቻችንን ታሪክ ለመውረስ እንቸገራለን ሲሉ ጠቅሰው ይህን አስደማሚ መታሰቢያ ሌሎች ጥቁር ሕዝቦች ሊሠሩት ቢችሉም የዓድዋ ጀግኖች ልጆች መሆን እንደማይችሉም ገልጸዋል።

ይህም ዕድልና ትግል ሲገናኙ ይሰምራል በሚለው ብሒል ኢትዮጵያዊ በመሆን ታድለን የመሥራት ልቦናና ትግል ታክሎበት መታሰቢያ መሠራቱን በመግለጽ ከ128 ዓመታት በኋላ ኢትዮጵያን መስሎ እና ኢትዮጵያን አክሎ ለትውልድ መተላለፍ በሚችል መልኩ መሠራቱን ተናግረዋል።

ይህንን አስደማሚ የዓድዋ ድል መታሰቢያ ሌሎች የጥቁር ሕዝቦች ሀገራት ሊሠሩት ቢችሉም፤ የምኒልክ ልጅ፣ የባልቻ ልጅ፣ የገበየሁ ልጅ፣ የአሉላ አባ ነጋ ልጅ መሆን ግን አይችሉም ብለዋል።

የዓድዋን መታሰቢያ ማርከስ ማለት የአባቶቻችንን አጥንትና ደም ማርከስ ማለት ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ የዓድዋን መታሰቢያው ታግለን ጥረን ሠርተን ያሳካነው ነው ብለዋል።

ከአባቶቻችን ልንወርስ የሚገባው ነፃነቱን ክብሩንና አንድነቱን እንጂ እሳቱን መውረስ አይጠበቅብንም ሲሉ ጠቅሰው አባቶቻችን ዋጋ የከፈሉበት ነፃነትና ክብር እሴት ሲሆን ነፃነትን ለማግኘት የሄዱበት መንገድ እሳት መሆኑን ገልጸዋል።

"ኢትዮጵያ በእርግጠኝነት ትበለጽጋለች፤ ከውጪና ከውስጥ የተነሱባት ጠላቶቿም እንዴት ተሳካላት ብለው ይጠይቃሉ" ሲሉ የገለጹ ጠቅላይ ሚኒስትሩ "ኢትዮጵያ የተባለችው አውሮፕላን ሞተር እያሞቀች ልታኮበኩብ ነው፤ ትበራለችም" ብለዋል።

የጀመርነውን ሥራ የሚያስቆመን ነገር የለም፤ ምክንያቱም የአባቶቻችን ልጆች ነንና ሲሉ ጠቅሰው አባቶቻችን በጦር፣ በጋሻ እና በፈረስ ሞተው ኢትዮጵያን ነፃ አውጥተው የጥቁር ሕዝቦች የነፃነት ምልክት አድርገውናልም ሲሉም ገልጸዋል።

ዓድዋ የሚያስታውሰን ለወራሪ አልገዛም ባይነትን ነው፣ ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ነፃነትን እና ክብርን የወረሰ ትውልድ ተለዋዋጭ ሁኔታን በማየት ተስፋ ሊቆርጥ አይገባም ብለዋል።

ከአባቶቻችን የወረስነውን እምቢኝ ማለትን ድህነትን እና ድርቅን እምቢኝ ሊባል እንደሚገባ በመግለጽ የዛሬ ዕለት ኢትዮጵያውያን ለልማት እና ለዕድገት በአንድነት ቃል የሚገቡበት ቀን ነው፤ ከነክብሯ እና ነፃነቷ ለልጆቿ ለማሸጋገር እንደዚህ ያለ የድል መታሰቢያ ያስፈልጋታልም ሲሉም ነው የተናገሩት።

አሁን ላይ ታሪካዊው የዓድዋ ድል መታሰቢያ ፀሐይ አውሮፕላን መኖሯን ጠቅሰው፣ የአባቶቻችን የመጀመሪያ ቴክኖሎጂ ውጤት እና ምልክትም እንደሆነች ገልጸዋል።

ሥራውን እኛ ጀምረነዋል ትውልድ ግን ይጨርሰዋል ያሉት ዐቢይ (ዶ/ር) የኢትዮጵያ ከፍታ የተገለጠለት ከፍታዋን ማየት ይኖርበታል፤ የምትጠራጠሩን ቆም ብላችሁ አስተውሉ ብለዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አዳነች አቤቤ በበኩላቸው፤ የዓድዋ ድል መታሰቢያ ታላቁ የዓድዋ የጀግንነት ገድል የደመቀበት ተበታትነው የነበሩ የታሪክ ማስረጃዎች የተሰበሰቡበትና የተረሱ የታወሱበት ነው።

በዓድዋ ጦርነት ኢትዮጵያውያን ልዩነትን ወደ ጎን በመተው በአንድነት ወደ ዓውደ ውጊያው ተምመዋል ያሉት ከንቲባዋ በዚህም የጥቁር ሕዝቦች ሁሉ የነፃነት ቀንዲል የሆነውን የዓድዋ ድልን አስመዝግበዋል ብለዋል።

የዓድዋ ድል መታሰቢያ አንዳንዴ የልዩነት ምክንያት ሆኖ የቆየው ታላቁ የዓድዋ የጀግንነት ገድል የደመቀበት ነው ያሉት ከንቲባዋ ተበታትነው የነበሩ የታሪክ ማስረጃዎች የተሰበሰቡበት፤ የተረሱ የታወሱበት ነው ብለዋል።

መታሰቢያው የታሪክና ትርክት ክፍተትን ከመሙላት ባለፈም ስብራትን የሚጠግን እንደሚሆን እናምናለን ብለዋል።

የዓድዋ ድል መታሰቢያ ጀግኖችን በሚገባቸው ከፍታ ያስቀመጠ መሆኑን ጠቅሰው ትውልዱ በአንድነት ሆኖ ማሸነፍንና የሀገር ፍቅርን የሚማርበት መሆኑንም ገልፀዋል።

የዓድዋ ድል መታሰቢያ መላ ኢትዮጵያውያን በአንድ ቋንቋ እንዲግባቡ የማድረግ ኃይል ያለው መሆኑን በመግለጽ ትናንትን ከዛሬ ዛሬን ከነገ የሚያስተሳስር ድልድያችን በመሆኑ የመጪው ትውልድ ስጦታችን ነው ብለዋል።

# ዓድዋ የሚወሳው ሀገርን...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

መሆናችንን ሊያጠራጥር የሚችል ሁኔታ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

ከታሪክ ታሪክን መዘከር ብቻ ሳይሆን ከታሪክ መማር አለብን ያሉት ፕሬዚዳንቷ ዛሬ ዓድዋን የምናወሳው ሀገርን ለማዳን የተሰዉትን ጀግኖች ለማስታወስና የሚገባቸውን ክብርና ቦታ ለመስጠት እንደሆነ በአፅንዖት ገልጸዋል።

በዓድዋ የዘመቱ ጀግኖችን ያገናኛቸው አንድ የሀገር ፍቅር መሆኑን ጠቅሰው ሀገርን ማዳን ከልዩነቶቻችን በላይ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

የዓድዋ ድል ለአፍሪካውያንና ለመላ ጥቁር ሕዝቦች የኩራት ምንጭ መሆኑንም የጠቀሱት ፕሬዚዳንቷ፤ የዓድዋ ድል መታሰቢያ ለነፃነት የታገሉ ጀግኖችን ሁሉ የዘከረ ታላቅና ድንቅ የታሪክ አሻራ መሆኑን አስረድተዋል።

የአንድ ሕዝብ ታላቅነት ከሚለካባቸው መስፈርቶች አንዱ ታሪክ ሠሪ መሆኑ ነው ያሉት ፕሬዚዳንቷ፤ የዓድዋ ድል ቅኝ አልገዛም ያለ ሕዝብ ግዙፍ ታሪክ መሆኑን ጠቁመው፤ ከኢትዮጵያ አልፎ በብዙ ሀገራት የሚከበር ታላቅ ድል ነው ሲሉ ገልጸዋል።

የዓድዋ ድል አፍሪካን በቅኝ ግዛትነት ለመቀራመት ላይ ታች ሲባል በነበረበት ጊዜ ሊወረን የመጣን ያለአቻ ወራሪ ለማሸነፍ የቻልንበት በመሆኑ፣ ድሉ የእኛ ብቻ ሳይሆን ቅኝ ግዛትን ይታገሉ ለነበሩ የአህጉሪቱ ሕዝቦች ጭምር ነው ብለዋል ፕሬዚዳንቷ።

ከታሪክ አንዳንድ ነገሮችን ብቻ መዘን እየተጨቃጨቅን ነው ያሉት ፕሬዚዳንቷ፤ ይህ ተግባር የዓድዋ ድል ባለቤት መሆናችንን የሚያጠራጥር ሁኔታ ውስጥ ይከተናል ሲሉ ኮንነዋል።

ዓድዋ ሀገር ስትደፈር ሕዝቡ ከነልዩነቱ በአንድነት የተነሳበት መሆኑን አውስተው፤ የዓድዋ ድል መታሰቢያም ይህን በተገቢው መልኩ ያሳየ መሆኑን ጠቅሰዋል።

ታሪክን መዘከር ብቻ ሳይሆን ከታሪክ መማር አለብን ሲሉም ፕሬዚዳንቷ ለመላ ኢትዮጵያውያን መልዕክት አስተላልፈዋል።

በመሆኑም ይህንን በሚመጥን መልኩ መታሰቢያ መገንባቱን በመጥቀስ ለዚህ ስኬት የላቀ ሚና ለነበራቸው ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እና ከንቲባ አዳነች አቤቤ ምስጋና አቅርበዋል።

የዓድዋ ድል መታሰቢያ የምረቃ መርሐግብር የተወካዮችና የፌዴሬሽን ምክር ቤቶች አፈ ጉባኤዎች፣ ሚኒስትሮች፣ የክልል ርዕሳነ መስተዳድሮች፣ የሀገራት አምባሳደሮች፣ አርበኞችና ሌሎች ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ተገኝተዋል።



ቆስጠንጢኖስ በርኸተስፋ (ዶ/ር)



አቶ ሸዋፈራሁ ሽታሁን

# ወደ እህትማማችነት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

እንደ አምባሳደሩ ገለጻ፤ ኢትዮጵያ በተለይ በሠላም ደህንነት ዙሪያ ሽብርተኝነትን በመዋጋት ረገድ፣ በእድገትና ልማት፣ የተፈጥሮ ሀብቶችን በጋራ መጠቀም፣ የአየርን ንብረት ለውጥን በመከላከል እና በዓለም አቀፍ መድረኮች የጋራ ፍላጎቶች ላይ ትብብርን የማጠናከር ፍላጎት አላት።

ይህ የሚኒስትሮች የጋራ ኮሚሽን ስብሰባ የቆየውን ግንኙነት ለማጠናከር የሚረዳ ስልት ነው ያሉት አምባሳደር ፍስሐ፤ ውይይቱ በሁለት እህትማማች ሀገራት መካከል የሚካሄድ በመሆኑ ውጤታማ ስብሰባ እንደሚሆን ገልጸዋል።

ሁለቱ ሀገራት በትብብር ለመሥራት የተስማሙባቸው መስኮች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየሰፉ መጥተዋል ያሉት አምባሳደሩ፤ በሁለተኛው የሚኒስትሮች ኮሚሽን ስብሰባ ላይ በርካታ የመግባቢያ ስምምነቶች መፈረማቸውን አንስተዋል።

ስምምነቶች በተለያዩ ችግሮች ከሞላ ጎደል ተፈጻሚ እንዳልነበሩ ጠቅሰው፤ ይሁን እንጂ ሦስተኛው የኢትዮ-ሩዋንዳ የሚኒስትሮች ስብሰባ ሀገራቱ በተለያዩ መስኮች የተፈራረሟቸውን ስምምነቶች ወደ ትግበራ ማስገባት በሚቻልባቸው ሁኔታዎች ላይ እንደሚሆን ተናግረዋል።

እንደ አምባሳደር ፍስሐ ገለጻ፤ ሁለቱ ሀገራት እ.አ.አ በ2012 አጠቃላይ ትብብራቸውን ለማጠናከር ስትራቴጂካዊ ትብብር ለመፍጠርና ቋሚ የጋራ የሚኒስትሮች ኮሚሽን ለማቋቋም የሚያስችላቸውን የጋራ መግባቢያ ስምምነት ተፈራርመዋል። ከዚህ በፊት ሁለት ጊዜ ሚኒስትሮች ኮሚሽን ስብሰባን ያካሄዱ ሲሆን በኮቪድ 19 ወረርሽኝ ምክንያት ሦስተኛው ሳይካሄድ ቆይቷል።

በኢትዮጵያ የሩዋንዳ አምባሳደር ሜጀር ጄኔራል ቻርለስ ካራንባ በበኩላቸው፤ ሦስተኛው የሚኒስትሮች ኮሚሽን ስብሰባ በመዘጋጀቱ ምስጋና አቅርበዋል።

ስብሰባው ለሁለቱ ሀገራት ወሳኝና ጠቃሚ ያሉት

ፎቶ ገበቦ ገብሬ



አምባሳደር ሜጀር ጄኔራል ቻርለስ ካራንባ

አምባሳደሩ፤ ሁለቱን ሀገራት የሁለትዮሽ ግንኙነት ለማጠናከር ከፍተኛ ሚናን እንደሚጫወት አንስተዋል። ኢትዮጵያና ሩዋንዳ ጠንካራ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ያላቸው እህትማማች ሀገሮች ናቸውም ብለዋል።

ጠንካራ የሆነው የሁለትዮሽ ትብብሩ ወደ ባለብዙ ወገን ትብብር እንድንገባ አድርጎናል ያሉት አምባሳደሩ፤ ስብሰባው በሁለቱ ሀገራት መካከል የተደረሱ ስምምነቶች ወደ ተግባር እንዲቀየሩ የጋራ ጥረት ያስፈልጋል ብለዋል።

ኢትዮጵያና ሩዋንዳ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነታቸውን የጀመሩት እ.አ.አ በ1970ዎቹ ነው። ሩዋንዳ በኢትዮጵያ እ.አ.አ በ1978 ሲሆን ኢትዮጵያ በኪጋሊ እ.አ.አ 2017 ኤምባሲ ከፍታ የዲፕሎማሲ ሥራዎችን በማከናወን ላይ ይገኛሉ። መደበኛ የዲፕሎማሲ ግንኙነት ከጀመሩ በኋላ በርካታ የሁለትዮሽ የትብብር ስምምነቶች በተለያዩ ዘርፎች ተፈራርመዋል። በትናንትናው ዕለት የተጀመረው ስብሰባም ለተከታታይ ሦስት ቀናት የሚቀጥል ይሆናል። የሚኒስትሮች ስብሰባ በዛሬው ዕለት ይካሄዳል።

# አጀንዳ 2063፤ ምን...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ግን አፍሪውያን ያለሙትን ብልጽግና እውን የማድረግ ጥረታቸውን ለማሳካት ይከብዳቸዋል፤ ሕዝቦቻቸውንም ከድህነትና ከኋላ ቀርነት ብሎም ከግጭት ለማላቀቅ አይችሉም። አንድነት የሚረዱ በርካታ ግቦችን የያዘ ነው። ፕሮግራሙን ለማስፈጸም በተሠሩት ሥራዎች አመርቂ ውጤቶች ተገኝተዋል። ያም ሆኖ ግን በርካታ ያልተሳኩ ጉዳዮች አሉ።

በአጀንዳ 2063 ከተገኙ ስኬቶች መካከል አንዱ የአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጣና ሥርዓት መውጣቱና ቢሮ መቋቋሙ ነው የሚሉት ዶክተር ቆስጠንጢኖስ፤ ይህም የአህጉሩን ኢኮኖሚ ለማሳደግ፣ ሥራ ፈጠራን ለማሻሻል፣ ለሸቀጦች እና አገልግሎቶች አንድ የንግድ ማዕከል በመገንባት ድህነትን በመቀነስ ለውጥ የሚያመጣ መሆኑን ያስረዳሉ።

የትራንስፖርት መሠረተ ልማት አለመሟላቱ ለግብይት ሥርዓቱ መጀመር ፈተና በመሆኑ የትራንስፖርት መሠረተ ልማት ማሻሻያ ማድረግ፣ ፖለቲካዊ ቀውሶችን በመፍታት፣ ሙስናን በመዋጋት፣ ዘመናዊ አሠራሮችን በመዘርጋት እና ተመሳሳይ የመገበያያ ገንዘብ እንዲኖር በማድረግ የሚያጋጥሙ ፈተናዎችን ማለፍ እንደሚገባም ይገልጻሉ።

አፍሪካን ሠላማዊ አህጉር ማድረግ ከአጀንዳ 2063 ግቦች መካከል ቢሆንም 31 የሚደርሱ የአፍሪካ ሀገራት ፖለቲካዊ ቀውስ ውስጥ ይገኛሉ ያሉት ዶክተር ቆስጠንጢኖስ፤ ፖለቲካዊ ቀውስ ውስጥ ከሚገኙት ሀገራት መካከል አንዳንዶቹ የመንግሥት ግልበጣ ለማድረግ የሚያደርጉትን ጥረት ሕዝቡ እየደገፈው እንደሚገኝ ያስረዳሉ።

በዚህም ሀገራቱ ከአፍሪካ ኅብረት አባልነት እየተወገዱ ሲሆን፤ ፖለቲካዊ ቀውሱ በዚህ የሚቀጥል ከሆነ የአፍሪካ ኅብረት በ2063 ሊደርስበት ካቀደው የልማት ግቦች ላይደርስ ይችላል ይላሉ።

ሁሉም ባለድርሻ አካላት የአፍሪካ ሀገራትን ከፖለቲካ ቀውስ በማውጣትና የሕዝቡን ኑሮ በማሻሻል ኅብረቱ በ2063 ሊደርስበት ካቀደው የልማት ግቦች ለማድረስ በአንድነት መበልጸግ እንደሚገባ ያስገነዝባሉ።

የአፍሪካ መንግሥታት ከሕዝባቸው ጋር በመነጋገር ሰላምን የማምጣት፣ ቀጣናዊ ልማትንና ትስስርን የማጠናከር፣ ሙስናን የመወጋት፣ መልካም አስተዳደርን የማጎልበት፣ ከአፍሪካውያን በሕገወጥ መንገድ የሚዘረፉ ሀብቶችን ማስቆም እና ሌሎች ሥራዎችን ማከናወን ለአጀንዳ 2063 ስኬታማነት የቤት ሥራዎች መሆናቸውን ያስረዳሉ።

እያንዳንዱ ሀገር የሕዝቦችን የኑሮ ደረጃ ማሻሻል፣ የትምህርትና የጤና ተቋማትን ማስፋፋት እና የጋራ ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጡ ተግባራትን ማከናወን እንደሚገባም ጨምረው ያስረዳሉ።

ናይጄሪያ፣ አልጀሪያ፣ ደቡብ አፍሪካ፣ ኢትዮጵያ፣ ግብጽ፣ ሞሮኮ እና ሌሎች የአፍሪካ ትልልቅ ሀገራት ለአጀንዳ 2063 ስኬታማነት በምሳሌነት ሊጠቀስ የሚችል ሥራ መሥራት አለባቸው ይላሉ።

የፖለቲካል ኢኮኖሚ ተንታኝ አቶ ሸዋፈራሁ ሽታሁን በበኩላቸው፤ አፍሪካ ለሕዝቧ ኢኮኖሚያዊ ልዕልና እና ነፃነት የሚረዳ የአጀንዳ 2063 እቅድ ማውጣቷ የሚደነቅ ተግባር ነው ይላሉ።

አጀንዳ 2063 አፍሪካውያንን በኢኮኖሚ፣ በፖለቲካ፣ በማኅበራዊና ሌሎች ጉዳዮች ላይ የሚያስተሳስር እና በጋራ ለማደግ መልካም አጋጣሚ በመሆኑ ለስኬታማነቱ በትኩረት መሥራት ከሁሉም የሚጠበቅ ተግባር ነው ይላሉ።

ለአፍሪካዊ ችግሮች አፍሪካዊ መፍትሔ የሚለውን ሀሳብ በመገንዘብ በአህጉሪቱ የሚፈጠሩትን ችግሮችን እርስ በእርስ በመግባባት መፍታት መቻላችን እና በጉዳዩ ጠንካራ አቋም መያዙ የአጀንዳ 2063 ስኬት መሆኑን ይናገራሉ።

በጋራ ተጠቃሚነት፣ አብሮ በማደግ እና በቀጣናዊ ትስስሮችን ለማጎልበት በጋራ መሥራት መጀመሩ እንዲሁም አፍሪካውያን በእራሳቸው ማንነት እና ሀብት መኩራታቸውም ሌላኛው ስኬት ነው ይላሉ።

የአፍሪካ መንግሥታት መተማመን እና መተባበር ላይ የተመሠረተ ግንኙነት ሊኖራቸው እንደሚገባ አስታውቀው፤ አሁን ላይ የተጀመረውን ቀጣናዊ ትስስር አመርቂ ውጤት እንዲያመጣ በትብብር መሥራት እንደሚገባ ይገልጻሉ።

አጀንዳ 2063 ስኬታማ መሆን የሚችለው በአፍሪካውያን ልሂቃን መሪነት ብቻ ሳይሆን ሕዝቡም የነቃ ተሳትፎ ሲያደርግ ነው። በተጨማሪም ዴሞክራሲና ነፃነት ለሕዝቡ መስጠት፣ ትምህርት እና ግብርና ላይ ማተኮር እንደሚጠይቅም ይገልጻሉ።

በአንዳንድ የአፍሪካ ሀገራት ሥልጣንን በኃይል ለመያዝ የሚደረጉት የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራዎች የአፍሪካን ተሰሚነት እና ተፅዕኖ ፈጣሪነት የሚቀንስ ነው። በዚህ ደግሞ አፍሪካውያን በአንድነት ሆነው ለአጀንዳው ስኬታማነት እንዳይሠሩ ምክንያት ስለሆነ ለዘላቂ ሠላም መሥራት ይገባል ይላሉ።

ኢትዮጵያ የፓን አፍሪካኒዝም እምብርት፣ የአፍሪካ ኅብረት መቀመጫ እና በዓለም አቀፍ መድረኮች ተሰሚነት ያላት ሀገር በመሆኗ ሁሉም ኢትዮጵያውያን ሀሳቡን፣ ጉልበቱን እና እውቀቱን በማቀናጀት ለሌሎች ሀገራት ምሳሌ በሚሆን ደረጃ ለአጀንዳ 2063 ስኬታማነት መሥራት ይገባቸዋል ሲሉም የፖለቲካ ኢኮኖሚ ተንታኙ ገልጸዋል።

ለአጀንዳ 2063 ስኬታማነት ፖለቲካዊ ቀውሶችን መፍታት፣ ሙስናን መዋጋት፣ መሠረተ ልማትን ማስፋፋት፣ ቀጣናዊ ትስስሮችን ማጎልበት፣ የሥራ ባሕልን ማዳበር እና ሌሎች አንኳር ጉዳዮች ላይ በትኩረት መሥራት እንደሚገባ ምሑራኑ አጽንኦት ሰጥተው ይናገራሉ።

ይህ ካልሆነ ግን አፍሪካውያን ያለሙትን ብልጽግና እውን የማድረግ ጥረታቸውን ለማሳካት ይከብዳቸዋል፤ ሕዝቦቻቸውንም ከድህነትና ከኋላ ቀርነት ብሎም ከግጭት ለማላቀቅ አይችሉም፡፡

ኢኮኖሚ

# ግብርና

# ምሥራቅ አፍሪካውያን አርብቶአደሮችን ይበልጥ ያወዳጀው መድረክ

**ማህሌት አብዱል**

ድንበርም ሆነ የፖለቲካ ልዩነት ሳይገድባቸው በአንድ መድረክ ተገናኝተው መክረዋል፤ ዘክረዋል። ሁሉም የየሀገሩን ባህል፤ ልምድና ተሞክሮ ለሌላው ለማሳየት በባህላዊ አልባሳቱ አምሮና ደምቆ በመሰየም ጉርብትናውን አጥብቆ አስተሳስሯል፡፡ የመድረኩ አዘጋጅ የሆነችው ኢትዮጵያም በማይነጥፈው ባህሏ በብሔር ብሔረሰቦች ባህላዊ ውዝዋዜ እና ጭፍራ ታጅባ በአዲስ አበባ ሚሊኒየም አዳራሽ እንግዶቿን ተቀብላለች፡፡

አፍሮዎቹ አፋሮች ባገለደሙት ሽርጥ ላይ ጊሌያቸውን እንደሰኩ ክብ ሠርተው ከታች ወደላይ እየዘለሉ ጨፍረዋል፡፡ ከወዲያ ደግሞ የቦረና ኦሮሞ ሴቶች እልልታቸውንና ማራኪ ሀገርኛ ዜማቸውን ለጉድ በሚያሰኝ መልኩ አንቆርቁረውታል፡፡ ዓይናፋሮቹ የሶማሌ ሴት አርብቶአደሮች ደግሞ ግማሽ ጨረቃ በምትመስለው የሳር ጎጇቸው ውስጥ ሆነው ጎብኚውን በሚማርክ አቀራረብ ያመጡትን ባህላዊ ቁሳቁስ እንደ ዕጣን ያሉ ምርቶችን ለዕይታ አቅርበው አስተዋውቀዋል፡፡

ይህ ሁሉ ትዕይንት የቀረበው ታዲያ ኢትዮጵያ በሀገር አቀፍ ደረጃ ለ19ኛ ጊዜ እንዲሁም የመጀመሪያውን ቀጣና አቀፍ የአርብቶአደሮች ቀን ከጥር 17 እስከ 23 ቀን 2016 ዓ.ም በሚሊኒየም አዳራሽ ባዘጋጀችበት ወቅት ነበር። ለወትሮ የኢትዮጵያ አርብቶአደሮች ብቻ ይሳተፉበት የነበረው የአርብቶአደሮች ቀን በዓል ዘንድሮ በዓይነቱም፤ በዝግጅቱም ለየት ባለ መልኩ ነው የተሰናዳው፡፡

በዝግጅቱም ቁጥራቸው ከ300 የሚልቅ የምሥራቅ አፍሪካ ሀገራት አርብቶአደሮች፤ የመንግሥት አመራሮች፤ ዲፕሎማቶችና ምሁራን ታድመውበታል። ዝግጅቱን ልዩ ካደረጉት መርሐግብሮች መካከልም በአህጉራዊና ቀጣና አቀፍ የአርብቶአደሮች ጉዳይ ላይ ያጠነጠኑ ውይይቶች፤ የየሀገራቱ አርብቶአደሮች የሚጠቀሙባቸውን ባህላዊ ምግብና መመገቢያዎች፤ የእርሻ ቁሳቁስና አልባሳትን የመሳሰሉትን የሚያሳዩበት ኤክስፖና ባዛር እንዲሁም ጥዕሙ ዜማ፤ ማራኪ ጭፈራ የሚያሳዩባቸው መድረኮች ተጠቃሽ ነበሩ፡፡

የዩጋንዳዋን ካራሞጃ የአርብቶአደሮች መንደር ማኅበረሰብ ወክለው ከተገኙ ዩጋንዳውያን መካከል ስቴባኒያ ኢማኑኤል አፓ ሎሊናኛ አንዱ ነው፡፡ እሱና የሥራ ባልደረቦቹ በኢጋድ ጋባዥነት ኢትዮጵያ ባዘጋጀችው የአርብቶአደሮች በዓል ላይ የመታደም ዕድሉን በማግኘታቸው ከፍተኛ ደስታ የፈጠረላቸው መሆኑን ይናገራል፡፡ በተለይም ደግሞ በኤክስፖው ላይ ከተለያዩ ሀገራት በመጡ አርብቶአደሮች በቀረቡት መሰናዶዎች ትልቅ ትምህርት መውሰዱን፤ ወደ ሀገሩም ሲመለስ የቀሰመውን ልምድና ተሞክሮ ተግባራዊ ለማድረግ መነሳሳት የፈጠረለት መሆኑን ያስረዳል፡፡

እንደ ዩጋንዳዊው አርብቶአደር ገለፃ፤ እሱ የሚኖርባት ካራሞጃ የተሰኘችው ቆላማ አካባቢ ከሦስት ሚሊዮን በላይ የቀንድ ከብት ሀብት ያላት ሲሆን፣ በየአመቱ 20 በመቶ የሚሆነውን የቀንድ ከብት ዩጋንዳ ለገበያ ታቀርባለች፡፡ በተጨማሪም ከ50 በላይ ማዕድናትና በርካታ የቱሪዝም መስህቦች ያሉበት አካባቢ ነው፡፡ ይሁንና ሕዝቡ ባለው የተፈጥሮ ሀብት ተጠቃሚ አልሆነም፡፡

ካራሞጃ ለደብቡ ሱዳንና ኬንያ አዋሳኝ በሆነ ሥፍራ ላይ ትገኛለች፤ ለአካባቢው ማኅበረሰብ አርብቶአደርነት መተዳደሪያ ብቻ ሳይሆን የምግብ ዋስትና ማረጋገጫና ባህላዊ ሥርዓትም ጭምር እንደሆነ ያነሳል፡፡ በኤክስፖ ላይ የዩጋንዳውያንን አርብቶአደር ባህል የሚሳዩ ቁሳቁስ ይዘው በመገኘት ለቀሪው የቀጣናው አርብቶአደር ማስተዋወቅ የሚያስችሉ መሰናዶዎችን ማቅረባቸውን ይገልፃል፡፡

‹‹በዩጋንዳ አርብቶአደርነት እውቅና አልተሰጠውም፤ ፖሊሲ የለንም›› የሚለው አርብቶአደር ስቴባኒያ፤ ከረጅም አመታት በፊት ሕጉ ቢረቅም የሀገሪቱ ምክር ቤት እንዳላፀደቀው ያስረዳል፡፡ ለበርካታ ዓመታት ሕግ እንዲፀድቅና ሥራ ላይ እንዲውል የአርብቶአደሩ ማኅበረሰብ ሲሞግት መቆየቱን ያመለክታል፡፡ ሕጉ ባለመፅደቁ ምክንያት ማኅበረሰቡ የመሠረተ ልማት ተጠቃሚ መሆን አለመቻሉን፤ ይህም ሁኔታ የመንግሥት አካላትም በቂ ትኩረት ሰጥተው ክትትልና ድጋፍ እንዳያደርጉ እንቅፋት እንደሆነባቸው ጠቁሟል።

አክሎም ‹‹በካራሞጃ 23 በመቶ የሚሆነው አርብቶአደር




ብቻ ነው የትምህርት ዕድል ያገኘው። ለዚህ ደግሞ ዋነኛው ምክንያት በአካባቢያችን በቂ መሠረተ ልማት ባለመዘርጋቱና እኛም አርብቶአደር እንደመሆናችን ውሃና ግጦሽ ፍለጋ ከቦታ ቦታ የምንንቀሳቀስ በመሆኑ ተረጋግተን መማር ስለማንችል ነው›› ሲል ያስረዳል። በበዓሉ ላይ እነሱም ሆነ የሀገሪቱ ከፍተኛ አመራሮች መሳተፍ በመቻላቸው መደሰቱን፤ በተለይም ደግሞ ከኢትዮጵያም ሆነ ከሌሎች የምሥራቅ አፍሪካ ሀገራት ተሞክሮ ለመውሰድ ያስቻለው መሆኑን ይገልፃል፡፡

ከዚህ ባሻገር ‹‹የእኛ ሀገር ከፍተኛ የመንግሥት አካላትና ውሳኔ ሰጪዎች ከዚህ በመነሳት ለዘርፉ ትኩረት እንዲሰጡ ጫና ለማሳደር ያግዛል›› ይላል፡፡ እሱ ከኢትዮጵያ ተሞክሮ በመውሰድ የዩጋንዳን አርብቶ አደር ተጠቃሚ ማድረግ ይገባቸዋል የሚል እምነት አለው፡፡ በተጨማሪም አርብቶአደር አካባቢዎች ያለውን ማኅበረሰብ ኑሮ ለማሻሻል የመሠረተ ልማት ዝርጋታዎች በስፋት ሊከናወኑ እንደሚገባ አመልክቶ፤ ይህም የገበያ ትስስሩን በማጠናከር ለቀጣናው ኢኮኖሚ እድገት የላቀ ሚና እንደሚኖረው ያስገነዝባል፡፡

በዩጋንዳም ሆነ በሌሎች የምሥራቅ አፍሪካ ሀገራት በተደጋጋሚ አርብርቶአደሮች አካባቢ ግጭቶች እንደሚከሰቱ አስታውሶ፤ ከዚህ ጋር ተያይዞ በአንዳንድ የኅብረተሰብ ክፍል አርብቶአደሩን ነውጠኛ አድርጎ የመሳል እሳቤ ፈፅሞ ከእውነታው የራቀ እንደሆነ ያስረዳል። ‹‹ብዙ ጊዜ ግጭት የሚነሳው ከግጦሽና ከውሃ ጋር ተያይዞ ነው፤ ይህ ማለት ግን ሰላም ካለመፈለግ የመነጨ አይደለም፤ እኛ ሰላማዊ ሕዝቦች ነን፤ ይህ እንዲታወቅልን እንፈልጋለን›› ይላል፡፡ ይልቁንም የውሃና መሰል የተፈጥሮ ሀብቶች በአግባቡ እንዲጠቀሙ ቢደረግና የመሠረተ ልማት ዝርጋታዎች ቢከናወኑ ወደ ግጭት የሚሄዱበት ምክንያት አለመኖሩን ነው ያመለከተው፡፡

እንደዩጋንዳዊው አርብቶአደር ገለፃ፤ እንዲህ ያሉ ቀጣና አቀፍ መድረኮች መንግሥታትም ሆነ መላው የዘርፉ ተዋናይ ለግጭት መንስኤ የሆኑ ጉዳዮችን አንስተው በመወያየት የመፍትሔ አቅጣጫ እንዲያስቀምጡ ያግዛል፡፡ መሠረተ ልማቶችን በጋራ በማልማት የጋራ ተጠቃሚነትን ለማጎልበት ዕድል ይፈጥርላቸዋል፡፡ በተለይ ደግሞ የዩጋንዳም ሆነ የአብዛኞቹ የአፍሪካ ሀገራት አርብቶአደሮች ከከተማ የወጡና ለመንግሥታዊ ሥርዓት፤ ዓለምአቀፍ ውሳኔ ሰጪ ረጂ አካላት ሩቅ በመሆናቸው በብዙ ነገር ተጎጂ ናቸው፤ በመሆኑም መድረኩ ችግራቸውን ለተቀረው ዓለም እንዲያሳውቁ ሰፊ ዕድል ይፈጥርላቸዋል፡፡

የቀጣናው አርብቶአደሮች ኅብረት ማጠናከር እንዳለባቸው ያሳስባል፤ ይህም ደግሞ በየሀጋራቱ መንግሥት ላይ ተፅዕኖ መፍጠር እንደሚያስችል ገልፆ፤ ‹‹አርብቶአደሮች ራሳቸውን ማግለል የለባቸውም፤ ለልማታቸውና ለተጠቃሚነታቸው በጋራ መቆም ይገባቸዋል፡፡ እርስ በርስ መወያየት፤ መደጋገፍ አለባቸው›› በማለት ያስገነዝባል፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ በነበረው ቆይታ አርብቶአደሮች ያላቸውን አንድነትና የሚያመሳስሏቸው ጉዳዮች በርካታ መሆናቸውን ለመገንዘብ መቻሉን ያስረዳል፡፡ በመሆኑም ሁሉም አርብቶአደር ይህንን አንድነት በመጠቀም በጋራ ለልማቱ መትጋት ይገባዋል ባይ ነው፡፡

ወይዘሮ ኩሻ ጉዮ ደግሞ ሞያሌ ወረዳ ኦብሲሴ ቡላ ቀበሌ ሴት አርብቶአደሮችን ወክለው ነው የተገኙት። እሳቸውም ከተለያዩ የምሥራቅ አፍሪካ ሀገራት ከመጡ አርብቶአደሮች ጋር የልምድ ልውውጥ ለማድረግ ተሞክሮ ለመካፈል አስችሎኛል ይላሉ፡፡ ‹‹ከሁሉም በላይ ኅብረታችንን ለማጠናከርና በጋራ እንድናድግ ትልቅ አስተዋፅኦ አለው፡፡ ተባብሮ መሥራትና በሰላም መኖር እንዴት እንደምንችል ግንዛቤ አግኝተናል›› በማለት ይገልፃሉ፡፡

ሞያሌ አካባቢ ያለው አርብቶአደር በኢትዮጵያ፤ በሱማሌና ኬንያ አዋሳኝ የሚገኝ እንደመሆኑ በባህልና በአርብቶአደር የአኗኗር ዘይቤ ተመሳሳይነት ያለው ማኅበረሰብ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ ይሁንና ከዚህ ቀደም ከግጦሽ፤ ውሃ ጋር ተያይዞ ግጭቶች ይከሰቱ እንደነበር አስታውሰው፣ ኢጋድ ከሁሉም አካባቢዎች የተውጣጣ የሰላም ኮሚቴ ካቋቋመ በኋላ ግጭቶች እንዳይከሰቱ መደረጉን ያስረዳሉ፡፡ ‹‹ያለንን ሀብት በጋራ እየተጠቀምን በሰላም ነው እየኖርን ያለነው፡፡ ከሰላም ኮሚቴዎች ውስጥ ሴቶችም ይሳተፋሉ፡፡ አዋሳኝ በሆነ ቦታ ላይ ቢሮ አቋቁሞ ማኅበረሰቡን ተጠቃሚ የሚያደርጉ ሥራዎች እየተሠሩ ነው›› ሲሉ ያብራራሉ። በተጨማሪም የእሴት ሰንሰለት ፈጥሮ በወተትና ስጋ ምርቶቻችን የላቀ ገበያ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ድጋፍ እየተደረገላቸው ስለመሆኑም ያመለክታሉ፡፡

ይሁንና ካለው ሰፊ ሕዝብና፤ የተፈጥሮ ሀብት አንፃር እንደ ትምህርት፤ ውሃ፤ ጤና የመሳሰሉ መሠረተ ልማቶች በሚገባ ባለመዘርጋታቸው ማኅበረሰቡ ከድህነት መላቀቅ አለመቻሉን ይጠቅሳሉ፡፡ በዚህም ምክንያት ድርቅ በመጣ ቁጥር ከፍተኛ ቁጥር ያለው ማኅበረሰብ ቀዬውን ለቆ መሰደድ እንደሚገደድ ያመለክታሉ፡፡ በመሆኑም የሀገራቱ መንግሥታት ከዚህ ቀደሙ የላቀ ትኩረት ለአካባቢው ሊሰጡ እንደሚገባ ነው ያሳሰቡት፡፡ ‹‹በተለይም ሴቶችና ሕፃናት የድርቁ ዋነኛ ተጎጂዎች እንደመሆናቸው እነሱን ማዕከል ያደረጉ የልማት ፕሮጀክቶች መስፋት አለበት›› ይላሉ። የሀገራቱ መንግሥታት ቀጣይነት ላለው ልማትና አስተማማኝ ሰላም የቀጣናው ሀገራት በቅንጅት እንዲሠሩ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

አቶ ኤፔኑ ጁሉ የጋምቤላ ክልል የመስኖና ቆላማ ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ ክልሉ አርብቶአደርና ከፊል አርብቶአደር ማኅበረሰብ ያለበት እንደመሆኑ የበዓሉ መከበር ለክልላችን ልማት ጠቃሚ እንደሆነ ያምናሉ። በበዓሉ ላይ አርብቶአደሩ ማኅበረሰብ እንዲሳተፍ መደረጉ ራሱን እንዲያስተዋውቅ የላቀ ሚና ይኖረዋል የሚል እምነት አላቸው፡፡ በተለይ በክልሉ ያለውን የተፈጥሮ ሀብት በማስተዋወቅ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል ይላሉ፡፡

በሌላ በኩል የክልሉ አርብቶአደር የሚከተለው የከብቶች አያያዝ ሥርዓት ባህላዊ እንደመሆኑ ከተለያዩ ሀገራት ከመጡ አርብቶአደሮች ልምድ በመቅሰም ሥርዓቱን እንዲያዘምን ያግዘዋል ባይ ናቸው፡፡ እንዲሁም በድንበር ከሚዋሰኑ እንደ ደቡብ ሱዳን ካሉ ሀገራት አርብቶአደሮች ጋር በባህልም ሆነ በቋንቋ የሚዛመዱ እንደመሆናቸው ይህንን ግንኙነት ይበልጥ ለማጠናከር ወሳኝ ሚና እንዳለውም ያመለክታሉ፡፡

‹‹በዋናነት ደግሞ በሁለቱ ማኅበረሰብ መካከል አልፎ አልፎ የሚነሱ ግጭቶችን ከወዲሁ ለማስቀረት፤ ይበልጥ ለመቀራረብ፤ ያሉ ሀብቶችን በጋራ በመጠቀም አብሮ ለማደግ ያስችላል›› ሲሉም ያስረዳሉ፡፡ የምሥራቅ አፍሪካ ቀጣና ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር ተያይዞ ተደጋጋሚ ድርቅ የሚያጠቃው እንደመሆኑ፤ በበዓሉ ላይ የየሀገራቱ ከፍተኛ አመራሮችና ፖሊሲ አውጪዎች፤ የዓለም አቀፍ ድርጅቶችና ምሁራን የታደሙ በመሆኑ ድርቅን መቋቋም የሚችል ማኅበረሰብ ለመፍጠርና ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት የሚያስችሉ ስትራቴጂዎች ላይ ለመምከር የማይናቅ አበርክቶ እንዳለው ያብራራሉ፡፡ በተለይ ደግሞ ከምሁራንና ተመራማሪዎች ድርቅን አስቀድሞ መከላከል የሚያስችሉ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በማፍለቅ ረገድ ሚናቸውን ለመወጣት ግንዛቤ ያስጨበጡ ውይይቶች መደረጋቸውን ነው የተናገሩት።

እንደ አቶ ኤፔኑ እምነት፤ በምሥራቅ አፍሪካ በተፈጥሮ ሀብት የታደለ፤ ወሳኝ የልማትና የንግድ ኮሪደርና ሰፊ የሰው ሀብት ያለበት ቢሆንም በኢኮኖሚ ወደኋላ የቀረ ቀጣና ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ በተለይ በተደጋጋሚ የሚከሰተው ድርቅና የሰላም እጦት ዋነኛ መንስኤ ናቸው፡፡ በመሆኑንም እነዚህን ችግሮች ለመፍታት የመንግሥታቱ ቁርጠኝነትና በትብብር መሥራት ወሳኝ ነው፡፡ በተለይ ደግሞ ማኅበረሰቡን ከድህነት ለማላቀቅ በመድረኩ ላይ የተገኙ የየሀገራቱ ፖሊሲ አውጪዎችና አስፈፃሚዎች፤ ምሁራንና የኢጋድ አመራሮች ትልቅ ኃላፊነታቸውን ሊውጡ ይገባል።

ማህበራዊ

# አስኳላ

# ትምህርት በአፍሪካ

ግርማ መንግሥቴ

ከሰባቱ የዓለማችን አህጉራት አንዱን ብቻ ይዞ የተነሳው ርዕሳችን “አንዱን” በሚለው ምክንያት ጠባብ ይምሰል እንጂ ሰፊ ነው። ለስፋቱ ምክንያቶቹ ብዙ ቢሆኑንም፣ አህጉሪቱ ከዓለም በስፋት 2ኛዋ፤ በሕዝብ ቁጥርም ከእስያ ቀጥሎ 2ኛዋ፤ በስፋት የ30.3 ሚሊዮን ኪሎሜትር (km²)፤ ከአጠቃላይ የዓለም መሬት ሃያ በመቶን (20% land area)፤ ከአጠቃላይ ስፋት (total surface area) ስድስት በመቶን (6%)፤ የ1.4 ቢሊዮን ሕዝቦች መኖሪያ (ይህ የ2021 ጥናት ያሰፈረው ነው)፤ ከአጠቃላይ የዓለም ሕዝብ አስራ ስምንት በመቶን የያዘች የጥቁር ሕዝቦች ምድር፤ ከ1250–3000 የሚሆኑ የራሷ ቋንቋ (native languages) ያሏት (አንባቢ የማዕድን ሀብቷን ሊጨምርበት ይችላል) በመሆኗ ከሰባቱ አህጉራት አንዱ ትሁን እንጂ በብዙ ነገሯ ብልጫ ስላላት ርዕሳችንን ጠባብ ከመሆን ይታደገዋል።

ሌላውና ርዕሳችንን ከጠባብነት ወደ ሰፊነት ያዘነብል ዘንድ ግድ የሚለው የዘንድሮው (37ኛው) የአፍሪካ ኅብረት የመሪዎች ጉባኤ ዐቢይ የመወያያ ርዕሰ ጉዳይ ትምህርትና ሥልጠናን የተመለከተ መሆኑና የአፍሪካ አህጉር የትምህርት አቅጣጫ 21ኛውን ክፍለ ዘመን እንዲመስል የማድረግና በይዘትም አፍሪካዊ ገጽታን እንዲላበስ፤ በሂደቱም በተለይ ወጣቱን ተደራሽ፤ ተጠቃሚና ተሳታፊ የማድረጉ ሥራ ልዩ ትኩረትን ያገኘ መሆኑ ነው።

**በቀጥታ ወደ ርዕሰ ጉዳያችን እንሂድና አህጉሪቱ ያለችበትን ወቅታዊ ሁኔታ እንመልከት።**

በራቸውን ለበርካታ አሉታዊ ጉዳዮች በርግደው ከሰጡ የዓለማችን አህጉራት ያለ ምንም ተፎካካሪ አፍሪካ ቀዳሚዋ ናት።

አፍሪካ በእድገት ኋላ ቀር፤ በሥልጣኔ ጭለማ፤ በኢኮኖሚ ያልበለፀገች፤ ከምርትና ምርታማነት አኳያ ደሃ፤ በዲሞክራሲው (ዝም ነው)፤ በሰብዓዊ መብቶች አያያዝ (አሁንም ዝም ነው)፤ በተማረ የሰው ኃይል ቁጥር አናሳ በመሆኗ ወዘተርፈ ሁሉ ከመታማትም አልፋ ትወቀሳለች።

እናት አፍሪካ ሁሉ በእጇ፤ ሁሉ በደጇ ሆኖ ሳለ በረሀብ አለንጋ እምትጠበጠብ ብቸኛ አህጉር ነች እየተባለ በውስጥም፤ በውጭም እምትተች ቀዳሚት አህጉር መሆኗ አገር ያወቀው፤ ፀሐይ የሞቀው ጉዳይ ነውና ከመሪዎቿ ሁሌም ብዙ ስለ መጠበቁ የሚያከራክር አይደለም።

ከትምህርት አኳያ ያለውን ስንመለከትም ያውና ተመሳሳይ እንጂ ሌላ አይደለም። አህጉሪቱ “ትምህርት ሚኒስቴር ምን ያደርግላታል?“ እስከሚለው ዘለፋና ወቀሳ ድረስ ትወረፋለች። በዝርዝር እንየው።


ከትምህርት ጋር በተያያዘ ከመነሳት የማያመልጡና በዓለም አቀፍ ደረጃ (ስታንዳርድ) የተቀመጡ በርካታ ጉዳዮች ያሉ ሲሆን፣ ተደራሽነት፣ አካታችነት፣ ጥራት ወዘተ ቀዳሚዎቹ ናቸው።

ትምህርት ከሕግ ማዕቀፍ አኳያም የራሱ የሆኑ መደላድሎች ያሉት ሲሆን ከሰብዓዊ መብት አኳያ መሠረታዊ ትምህርት ማግኘት የሰው ልጅ ሁሉ መብት መሆኑ፤ በአፍሪካ ደረጃ (አጀንዳ 2063) ተግባራዊ ይሆን ዘንድ በሚሊኒየሙ የልማት ግቦች (MDGs) ውስጥ ተካትቶ መገኘቱ፤ በየሀገራቱ ከሕገመንግሥት ሰነዶች ጀምሮ፣ በተቋም ደረጃ መመሪያቱና የመሳሰሉት ትምህርትን በሚገባውና በሚፈለገው ደረጃ ሁሉ ለማስኬድ የሚያስችሉ ናቸው። ይሁኑ እንጂ ወደ እኛይቱ አፍሪካ ሲመጣ እንቅፋቱ ብዙ ነው።

እነዚህን ሁሉ ስንል በአፍሪካ ደረጃ ጉዳዩ ምን ይመስላል በማለት ለመወቃቀስ ሳይሆን፣ ምን መደረግ አለበት በሚለው ላይ የተወሰኑ ሀሳቦችን ለማከል ነው።

ሰሞኑን ጀምሮ በመገናኛ ብዙኃን ደረጃ በተደጋጋሚ ሲሰራጭ እንደ ሰነበተው የዘንድሮው የአፍሪካ ኅብረት የመሪዎች ጉባኤ መሪ ሀሳብም ሆነ ቀዳሚ የመወያያ አጀንዳ የትምህርት ጉዳይ ሲሆን፤ በተለይም ትምህርትን ለወጣቱ ተደራሽ ከማድረግ፣ ጥራትን ከመጠበቅ፣ ይዘቶችን አፍሪካዊ መሠረት ከማስያዝ፣ በአህጉሪቱ የሚሰጠው ትምህርት ክፍለ ዘመኑን የመሰለ ከማድረግ አኳያ በመሪዎቹ ተገቢው ውይይት እንደሚደረግበትና ውሳኔዎችም እንደሚተላለፉ ይጠበቃል።

በበርካታ ጥናቶች ላይ ስንመለከት እንደኖርነው፣ የአፍሪካ የትምህርት ሁኔታም ሆነ ይዞታ ደረት የሚያስነፋ አይደለም። ከመጀመሪያው ደረጃ ጀምሮ እስከ ላይኛው




**አፍሪካ በእድገት ኋላ ቀር፤ በሥልጣኔ ጭለማ፤ በኢኮኖሚ ያልበለፀገች፤ ከምርትና ምርታማነት አኳያ ደሃ፤ በዲሞክራሲው (ዝም ነው)፤ በሰብዓዊ መብቶች አያያዝ (አሁንም ዝም ነው)፤ በተማረ የሰው ኃይል ቁጥር አናሳ በመሆኗ ወዘተርፈ ሁሉ ከመታማትም አልፋ ትወቀሳለች**

የከፍተኛ ደረጃ የትምህርት ተቋም ድረስ ክፍተቶች አሉበት። ክፍተቶች ይኑሩበት እንጂ ሁሌም (እየዳኸም ቢሆን) ለውጥ ከማስመዝገብ ቦዝኖ አያውቅም። በተለይ የአፍሪካን የትምህርት ታሪክ በሁለት (ቅድመ እና ድረ ቅኝ አገዛዝ) ከፍለው ያጠኑ ሰዎች እንደሚሉት ከፊተኛው የኋለኛው እንደሚሻልና እየተሻሻለ ነው የመጣው። (ለምሳሌ "Literacy-the World Factbook"፣ 2021ን ተመልከት።)

ለምሳሌ ያህል በ1999 58% የነበረው ሽፋን፤ በ2010 77% ደርሷል። በ1999 19% የነበረው የሁለተኛ ደረጃ የትምህርት ሽፋን በ2009 26% ደርሷል። ከሥርዓተ ፆታ ተመጣጥኖ (Gender disparity) አኳያ ሲታይ ከሰሐራ በታች ባሉ ሀገራት፣ በ1999 100፡85 የነበረው፣ በ2010 100፡93 ደርሷል። (የTIMSS ጥናት እንደሚያሳየው) ከሴት ተማሪዎች ተሳትፎ አናሳነት የተነሳ የአፍሪካ ሀገራት እዚህ ግባ የሚባል ፕሮግራም እንኳን እንደሌላቸው “most African countries lack programs to empower girls holistically” ተብለው እንደሚወቀሱም ዩኔስኮ እና የአፍሪካ ኅብረት ለመጀመሪያ ጊዜ በጋራ ካጠኑት ጥናት (Education in Africa: placing equity at the heart of policy; continental report) መመልከት ይቻላል።

እንደዚህ ጥናት (ሴፕቴምበር 2023 ወቅታዊ የተደረገ) ከሆነ ከሰሐራ በታች ባሉት ሀገራት ከ58% በላይ ለትምህርት የደረሱ ልጆች ወደ ትምህርት ቤት አይሄዱም። ወደ ትምህርት ቤት የሄዱትም ቢሆኑ) ጥራት ያለው ትምህርት ከማግኘት አኳያ ዓለም አቀፍ መስፈርትን ያሟላ ትምህርትን አያገኙም። በመሆኑም፣ ማንበብና መፃፍ መቻል ባለባቸው ደረጃ እንኳን ያንን ማድረግ ሲችሉ አይታዩም።

እንደ አህጉር ከታየ ደግሞ በአጠቃላይ አፍሪካ ከአምስት ልጆች አንዱ ወደ ትምህርት ቤት አይሄድም። ከአስር ወጣቶች ስድስቱ የትምህርት ቤቶችን ደጃፍ መርገጥ አልቻሉም። ለእነዚህ እና ሌሎችም ምክንያቶቹም መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ፣ ሥርዓተ-ፆታዊ (ኢ) እኩልነት፣ የከፋ ድህነት፣ አካል ጉዳተኝነት፣ ቅጣንባሩ የጠፋ ቀውስ፣ የከፋ የእርስ በርስ ግጭት፣ መፈናቀል ወዘተርፈ በማለት ይኸው፣ የላይኛው ጥናት ያስቀምጣል።

እነዚህ፣ የላይኛዎቹ ሰው ሠራሽ እንቅፋቶች ደግሞ የአህጉሪቱን መሪዎች ጠንካራ አሠራርና ውሳኔን የሚፈልጉ በመሆናቸው በዘንድሮው የአፍሪካ የመሪዎች ጉባኤ ላይ ተገቢውን የውይይት መድረክ ያገኛሉ ተብሎ በጉጉት ይጠበቃል። የአፍሪካ ኅብረትም ከዩኔስኮ ጋር በመሆን ጥናቱን ያቀረበው ያለ ምክንያት አይደለምና ለውጥ ይኖራል የሚለው ሚዛን ደፍቶ ይገኛል።

እንደዚሁ ጥናት የአፍሪካ ትምህርት አካታችነትን በነቢብ ሳይሆን በተግባር (inclusion through action) የማሳየት ችግር አለበት። በመምህራን ልማት በኩልም የከፋ ችግሮች አሉ። ደረጃቸውን የጠበቁ የትምህርት ተቋማት የመገንባት ችግሮችም በብዛት ይስተዋላሉ። ሥርዓተ ትምህርት ቀረፃው በራሱ በተገቢው መንገድ የተሠራ አይደለም። የፋይናንስ አቅም የሌላቸውን ወገኖች የረሳ ነው፤ ምንም አይነት እገዛ አይደረግላቸውም። በመሆኑም፣ ባለ 256 ገፁ የጋራ ጥናት (WWW.UNESCO.ORG ላይ ያገኙታል) የአፍሪካ መሪዎች ለጉዳዩ ትኩረትን በመስጠት በአፋጣኝ ችግሩን ሊፈቱት ይገባል።

ይህ፣ መሪዎቹ በ2016፣ በ26ኛው መደበኛ ጉባኤያቸው ያፀደቁትን ሰነድ (“The Continental Education Strategy for Africa 2016-2025 (CESA 16-25)) የሚያስታውሰው ጥናት፣ ሙሉ በሙሉ ወደ ተግባር መቀየር ያስፈልጋል።

በተለይ አዲስ የለውጥ ኃይል መፍጠር ካስፈለገ፤ አዲስ ተነሳሽነት የግድ ከሆነ፤ የምትፈለገውና አፍሪካውያን የሚፈልጓት አፍሪካ እውን ትሆን ዘንድ ፍላጎት ካለ ይህንን ሰነድ ወደ መሬት በማውረድ ተግባራዊ ማድረግ የግድ ይሆናል።

ዓለም አቀፍ አጀንዳ 2030፣ Sustainable Development Goal on Education (SDG 4) የሚለውን ለማሳካት፤ Pan-African High-level Conference on Education (PACE) ውሳኔዎች ለመተግበር ያለው ምርጫ ወደ ሥራ መግባት ከመሆኑ አኳያ ጉዳዩ የአፍሪካ መንግሥታትን እንቅልፍ ሊነሳ ይገባል።

እንደ ሌላኛው የዩኔስኮ (UNESCO, 2020a: 21) ጥናት ከሆነ፣ በዓለም ላይ ያለ ምንም ተወዳዳሪ ከመጀመሪያ ደረጃ 18.8%፤ ከመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ 36.7%፤ ከመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ 57.5% ትምህርት ቤት ውጪ የሆኑ ወጣቶች (OOSY) ያሉባትን ከሰሐራ በታቿን አፍሪካ የያዘች አህጉረ አፍሪካ፤ ጥናት በተደረገባቸው 25 የአህጉሪቱ ሀገራት ለሙያ ትምህርት የተመዘገበው ከ5% (ከ25ቱ በአብዛኞቹ ከ1% በታች) በሆነባት አፍሪካ የትምህርትን ጉዳይ ቸል ብሎ የትም ሊደርስ አይቻልም እና ጊዜው አሁን እና አሁን መሆኑን ደግሞ ደጋግሞ ማስታወስ፤ አላርሙን ደግሞ ደጋግሞ (መንቃት ያለበት እስኪ ነቃ ድረስ) ማጮህ ይገባል።

በአንድ ሀገር (ማሊ) ብቻ ከ51,000 በላይ የመጀመሪያ ደረጃ ተማሪዎችን በማኅበረሰብ አቀፍ ማስተማሪያ ማዕከላት አማካኝነት መድረስ እንደተቻለው ሁሉ፤ ሌሎች የአፍሪካ አገራትም ተመሳሳይ ተግባራትን ሊያከናውኑ ይገባ ዘንድ በጥናት (2018) ተመልክቷል። ይህን መሰል እርምጃ በመላዋ አፍሪካ ስለ ማስፈለጉ እዚህ መጠያየቅ አያስፈልግምና እንቀጥል።

መሪዎች ቃላቸውን፣ በተለይም በ2030 እናሳካዋለን ያሉትን፣ የትምህርት ተደራሽነት፤ ጥራት፣ ተሳትፎ ወዘተ እናረጋግጣለን በማለት ቃል የገቡትን ለአፍታም ሊረሱት የሚገባ ባለ መሆኑ፣ እንደ አንድ የዓለም አካል ሁሉ የአፍሪካ መሪዎችም ዳግም ቃላቸውን ሊያድሱና ተግባራዊ ሊያደርጉ ይገባል።

ምንም እንኳን፣ የአፍሪካ ሀገራት ከነጭ የበላይነት ነፃ ሲወጡ ከነበሯቸው የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና ተማሪዎቻቸው አኳያ ሲታይ (ለምሳሌ በ1961 ኬኒያ 400 የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ፤በ1963 ታንዛኒያና ዛምቢያ እያንዳንዳቸው 300 የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ብቻ ነበሩ የነበሯቸው) አሁን በማይገናኝ መልኩ ያደጉ ቢሆንም፤ ጥራት፣ ተደራሽነትና አካታችነት ላይ ምንም የሠሩት ሥራ እንደ ሌለ ነው የተመራማሪዎችን የጥናት ይሁንታ አግኝተው በመረጃነት እያገለገሉ ያሉ ጥራዞች የሚያመለክቱት።

የአፍሪካ የትምህርት ተደራሽነት ችግር የትምህርት ተቋማት በከተሞች ብቻ የመታጨቃቸው ጉዳይ ሲሆን፣ ትምህርትን ለሁሉም እኩል ተደራሽ ማድረግ ላይ ጠንክሮ መሥራት እንደሚገባ ሁሌም እንደ ተመከረ ነውና በዚሁ የአፍሪካ የመሪዎች ጉባኤ ላይም በለሆሳስ ሊታለፍ እንደማይገባ ጉዳዩን ከስሩ አስምሮ ማለፍ ይገባል።

እንደ ተመራማሪዎች ምሑራዊ ምክር ከሆነ የአፍሪካ ሀገራት መንግሥታት መሥራት ያለባቸውን ሁሉ አሁኑኑ መሥራት ካልቻሉ መጪው ዘመን ለሀገራቱ (በተራዛሚው ለአህጉሪቱ) የከፋ ይሆናል። በተለይም በፈጣን ሁኔታ እያሻቀበ ያለውን የሕዝብ ቁጥር በተመለከተ ጊዜ ወስደው፣ ከሌላ ሌላው ነገር ሰብሰብ ብለውና አስበው እማይሠሩ ከሆነ አደጋው የከፋ ይሆናል። ለዚህ ስጋታችን ደግሞ በ2020 ያለውን ብቻ እንኳን ብንወስድ ጉዳዩን ግልፅ ያደርግልናል።

እዚህ እንደተጠቀምንባቸው መረጃዎች በ2020 በአፍሪካ ከ25 ዓመት እድሜ በታች ያው ወጣት ብቻ 800 ሚሊዮን ሲሆን፤ 677 ሚሊዮኖች ደግሞ እድሜያቸው ከሦስት እስከ 24 ያሉ ናቸው። ይህንን ይዘን የአሁኑን፣ የ2024ን ስናክልበት ውጤቱና ስጋቱ የት ሊደርስ እንደሚችል ለማንም ግልፅ ነውና ጥናቶቹ Africa’s population is not only young but also growing fast ያሉትን በመጥቀስና በመግቢያ አንቀፃችን ላይ ያሰፈርነውን በማስታወስ እዚሁ ላይ እናቆማለን።

**መልካም የአፍሪካ ሕብረት የመሪዎች ጉባኤ!!!**

# ‹‹በምሥራቅ ሐረርጌ በ93 ሺህ ሄክታር መሬት ላይ የስንዴ ልማት ተከናውኗል››

**የምሥራቅ ሐረርጌ ምክትል አስተዳዳሪ**
**አቶ አያሌው ታከለ**

ስምስም መንግሥቱ



ፎቶ:- ዳኜ አበራ

የምሥራቅ ሐረርጌ ዞን በከፍተኛ ሁኔታ የቡና እና የጫት ልማት የሚካሄድባትና ለልማትም ምቹ የሆነ ሥነምህዳርና የአየርፀባይ እንዳላት ይታወቃል። ልማቷም በሀገሪቱ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ ያለው ሲሆን፤ በግብርና ዘርፍ የተለያዩ የሰብል ልማቶች ይከናወናሉ፡፡ እንደሀገር የበጋ ቆላ መስኖ የስንዴ ልማት ከተጀመረ ወዲህ ደግሞ፤ ከዚህ ቀደም በአካባቢው ባልተለመደ ሁኔታ የስንዴ ልማቱ ተጠናክሯል፡፡

በማዕድን ሀብትም የምድር ፀጋ እንዳላት የሚነገርላት ምሥራቅ ሐረርጌ፤ በቱሪዝም ኢንዱስትሪውም እንዲሁ የቱሪስት መስህብ የሚሆኑ ሀብቶችን በውስጧ ይዛለች። ይህን ሀብት ወደ በለጠ የኢኮኖሚ ጥቅም ለማሸጋገር በማኅበራዊ ዘርፍ በጤና፣ በትምህርት ተደራሽነት ላይ እየተከናወኑ ስላሉ ተግባራት እንዲሁም የአካባቢ ሰላምን ማረጋገጥ በፀጥታ ዙሪያ እየተሠሩ ስላሉ ሥራዎች የምሥራቅ ሐረርጌ ምክትል አስተዳዳሪ አቶ አያሌው ታከለ ጋር ቆይታ አድርገን እንደሚከተለው አቅርበንላችኋል መልካም ንባብ፡-

**አዲስ ዘመን፡- ምሥራቅ ሐረርጌ በስፋት በምትታወቅባቸው የቡና እና የጫት ልማትን በተመለከተ ቀድመው ማብራሪያ ቢሰጡን?**

**አቶ አያሌው፡-** እርግጥ ነው፤ በምሥራቅ ሐረርጌ ቡና በስፋት ይለማል፡፡ የሐረር ቡና በሀገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን፤ በዓለም ላይ ይታወቃል፡፡ የአካባቢው አርሶ አደር የኢኮኖሚ ምንጭም ነው። በመሆኑም በቡና ልማት ላይ በትኩረት እየተሠራ ይገኛል፡፡ በተለይም ሐረርጌ ቡና የሚባለውን ለማስቀጠል የሚያስችሉ ሥራዎች በመሥራት ላይ ናቸው፡፡ ለአብነት ያረጁ የቡና ተክሎችን በአዲስ እንዲተኩ የማድረግ፣ የቡና ችግኞችንም የማፍላት ሥራ ከተግባራቶቹ መካከል ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ ምርታማነትን ለመጨመር እየተሠሩ ባሉ ሥራዎች የአካባቢው የቡና ምርታማነትም ከአመት አመት እንዲጨምር አስችሏል፡፡

በአካባቢው ከቡና ልማት ቀጥሎ በስፋት የሚለማው ጫት ነው፡፡ ለሀገር የውጭ ምንዛሪ ገቢ በማስገኘትም በምጣኔያዊ እድገት ላይ ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛል። በሌላ በኩል የጫት ንግድ ሕገወጥነት ጋር በተያያዘ ያለውን ችግር ለመፍታት ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ነው፡፡ ሕገወጥ ንግድን ለመከላከል አንድ አካል ብቻ የሚወጣው አይደለም፡፡ ሥራዎች መሠራት ያለባቸው በቀጥታ ልማቱ ላይ ያለው አርሶአደር፣ አርብቶአደር፣ ዞኑ፣ አልፎም የኦሮሚያ ክልልና የፌዴራል መንግሥት የፀጥታ ኃይል አካላት በጋራ የሚንቀሳቀሱበትን ሁኔታ በመፍጠር ነው ፡፡

በዚህ መንገድ ጥረት እየተደረገ ሲሆን፤ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት የተውጣጡ አባላት የተካተቱበት ዐብይ ኮሚቴ ተቋቁሞ ወደ ሥራ ተገብቷል። በተደራጀና በተቀናጀ መልኩ ሕገወጥ ንግድን መከላከል ካልተቻለ ለሀገር እድገት ጠንቅ እንደሚሆን አረጋግጠናል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በሰብል ልማት በኩል ያለውን እንቅስቃሴ ደግሞ ቢገልጹልን?**

**አቶ አያሌው፡-** በሰብል ልማትም እንዲሁ የተለያዩ የልማት ሥራዎች ተሠርተዋል፡፡ በዞኑ ከሚመረቱት የሰብል ምርቶች መካከልም ስንዴ፣ በቆሎ፣ ከቅባት እህል ደግሞ ለውዝ፣ ሰሊጥ ይጠቀሳሉ፡፡ በአካባቢው በተጨማሪ እንደ አዲስ የተጀመረው የሩዝ ልማት ነው። ከ2013 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ የቆላ በጋ መስኖ ልማት ሥራ እንደ ተሞክሮ ተወስዶ ልማቱ በዞኑ ተጠናክሯል፡፡

በስንዴ ልማቱ በ2013 ዓ.ም በስድስት ሺህ ሄክታር መሬት ላይ የተጀመረ ሲሆን፤ በየአመቱ ግን በስንዴ ልማት የሚሸፈነው መሬት እየጨመረ ነው፡፡ በ2014 ዓ.ም ወደ 14 ሺህ ሄክታር መሬት፣ በ2015ዓ.ም 30 ሺህ ሄክታር መሬት ላይ ስንዴ በማልማት ሽፋኑን መጨመር ተችሏል። በተያዘው በጀት አመት በ2016 ዓ.ም ደግሞ ወደ ልማቱ የገባነው ሽፋኑን ማሳደግ ብቻ ሳይሆን፤ ፈጠራም የታከለበት መሆን አለበት ብለን ነው፡፡ በዚሁ መሠረት 93 ሺህ ሄክታር መሬት ላይ የስንዴ ልማት ተከናውኗል፡፡

በምርታማነት በኩልም ውጤት ተመዝግቧል። በ2013 ዓ.ም በሄክታር የተገኘው ወደ 13 ሺህ ኩንታል ምርት ነበር፡፡ በተያዘው በጀት አመት በተከናወነው ልማት ደግሞ በሄክታር ወደ 85 ኩንታል ምርት ለማግኘት አቅደናል፡፡ በአጠቃላይ ወደ ሁለት ነጥብ ሦስት ሚሊዮን ኩንታል ምርት እንደሚገኝ ይጠበቃል፡፡ ይህን ያህል ምርት የሚጠበቀው በ2015 በጀት አመት በሄክታር ወደ 58ሺ ኩንታል ማግኘት በመቻሉ ነው፡፡ በየአመቱ ያለው ውጤትም አበረታች በመሆኑ ጭምር ነው፡፡

የምሥራቅ ሐረርጌ ነዋሪ ስንዴን የሚያውቀው ወይም የሚያገኘው በልማት ሳይሆን፣ በእርዳታና በተለያየ መንገድ ነበር፡፡ አሁን ግን የአካባቢው አርሶአደር እራሱ አልምቶ ተጠቃሚ ለመሆንና የሀገርንም ኢኮኖሚ ለማሳደግ ወገቡን ጠበቅ አድርጎ ታጥቆ ተነስቷል፡፡ ጥቅሙንም በተግባር እያረጋገጠ በመሆኑ ከዚህ በኋላ ከልማቱ ወደኋላ የሚመልሰው አይኖርም፡፡ አርሶ አደሩ ዝናብ ካናዳ ሀገር ከሚዘንብ ምሥራቅ ሐረርጌ በተለይም ቁምቢ ወረዳ ውስጥ ይዝነብልን እስከማለት ደርሷል። ይህም ለልማቱ ያለውን ፍላጎትና ተነሳሽነት ያሳያል፡፡

አርሶ አደሩ ከእርዳታ ወጥቶ የምግብ ዋስትናውን ለማረጋገጥ ብሎም ለውጭ ገበያ በማቅረብ በሀገር ምጣኔ ሀብት እድገት ላይ የድርሻውን ለመወጣት በሚያስችል እንቅስቃሴ ላይ ነው፡፡ ልማቱንም በሙሉ ፍቃደኝነት እያከናወነ ይገኛል፡፡ አርሶአደሩ በቁርጠኝነት የልማቱ ተሳታፊ በመሆኑም ምሥጋና ይገባዋል፡፡

ሌላው በግብርና ሥራ በከፍተኛ ሁኔታ እየተከናወነ ያለው የተፋሰስና የአረንጓዴ ዐሻራ ልማት ሥራ ነው። በዚህም ሰፊ ሥራ ተሠርቷል። የአካባቢ ጥበቃ ሥራ በአፈር መሸርሸርና በመሬት መጎዳት የተራቆተው ተራራማው አካባቢ ሁሉ መልሶ እንዲያገግም ትልቅ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

በ2016 በጀት አመት ብቻ የምሥራቅ ሐረርጌ ነዋሪ በአንድ ጀንበር ወደ 45 ሚሊዮን የተለያዩ የዛፍ ችግኞችን ተክሏል፡፡ የተፋሰስ ሥራ ወይም የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር፤ የአካባቢ ሥነምህዳር እንዲመለስ፣ በአካባቢ ገጽታ ላይም ካበረከተው አስተዋጽኦ በተጨማሪ ለአካባቢው ወጣቶች የሥራ ዕድል በመፍጠር ዘርፈ ብዙ ጥቅሞችን አስገኝቷል። አርሶ አደሩም የምግብ ዋስትናው እንዲያረጋግጥ መልካም የሆነ ዕድል ፈጥሯል፡፡

የተጠናከረ የአካባቢ ጥበቃ ሥራ መሠራቱ ሌላው ያስገኘው ጥቅም፤ ለ17 አመታት መሬቱ ደርቆ ሜዳ ሆኖ የነበረው የሃሮማያ ሐይቅ መልሶ ማገገም መቻሉ ነው፡፡ የአካባቢ ጥበቃ ሥራው በየአመቱ እየተጠናከረ በመሆኑ፤ ከዚህ በኋላ የሃሮማያ ሐይቅ ይደርቃል የሚል ስጋት አይኖርም። ሃሮማያ ዩኒቨርሲቲ በበላይነት ይዞ ክትትል እያደረገ የሚገኝ በመሆኑ ዘላቂነቱን የሚያረጋግጡ በምርምርና ጥናት የታገዘ ተግባራት በዩኒቨርሲቲው በኩል እየተሠራ ይገኛል፡፡

የአካባቢ ጥበቃ ሥራው ምርትና ምርታማነት እንዲጨምርም ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከተ ነው፡፡ ተራራማ አካባቢዎችም በደን ተሸፍነዋል። የአካባቢው የደን ሽፋን ከነበረበት በ14 ነጥብ 5 በመቶ ጨምሯል። ይህ ሁሉ ውጤት የተመዘገበው በምሥራቅ ሐረርጌ አርሶአደር፣ አርብቶአደር፣ እንዲሁም የልማት ሠራተኞችና ሌሎችም ባለድርሻ አካላት ያደረጉት የጋራ ጥረት ነው፡፡ መንግሥት ለተፋሰስ ልማት የሰጠው ትኩረትም ጭምር ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የበጋ ቆላ የመስኖ ልማት በቂ የውሃ አቅርቦት እንደሚያስፈልገው ይታወቃል። ከዚህ አንጻር ልማቱን ለማረጋገጥ በአካባቢው ያለው የውሃ ሀብት ሁኔታ ምን ይመስላል?**

**አቶ አያሌው፡-** በምሥራቅ ሐረርጌ ውስጥ የተለያዩ የውሃ ሀብቶች ያሉ ሲሆን፣ ከከርሰ ምድርና ከወንዞች የሚገኙ ናቸው፡፡ በቂ የውሃ ሀብት አካባቢው ላይ እንዳለም በተለያየ ጊዜ በተደረጉ የጥናት ሥራዎች ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ አሁን ላይ ሥራዎች መሠራት ያለባቸው ያለውን ሀብት በአግባቡ በማስተዳደር ጥቅም ላይ በማዋል ነው። ለዚህም ዘመናዊ የአሠራር ሥርዓት ለመዘርጋት እንቅስቃሴዎች ተጀምረዋል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ምሥራቅ ሐረርጌ ውስጥ ያለው ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ እና በማኅበራዊ ዘርፍ በተለይ በትምህርት እና ጤና ዙሪያ ስላለው ተደራሽነት ቢያብራሩልን?**

**አቶ አያሌው፡-** ምሥራቅ ሐረርጌ ውስጥ ሰፊ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ አለ፡፡ ኢኮኖሚውን የሚያንቀሳቅሱትም በአካባቢው ላይ ያሉ ብሔር፣ ብሔረሰቦች ናቸው፡፡ በአካባቢው ላይ እየኖረ ያለው አንድ የሆነ የተጋመደ ማኅበረሰብ ነው። አካባቢያቸውን ለመለወጥ እየተንቀሳቀሱ ያሉት እነዚህ የኅብረተሰብ ክፍሎች ናቸው፡፡

በልማት፣ በንግድና በተለያየ እንቅስቃሴ ብቻ ሳይሆን፤ የዜግነት አገልግሎት በመሥጠትም ለውጥ ለማምጣት ሥራዎች ተሠርተዋል፡፡ በዚሁ መሠረት ከ2012 ዓ.ም እስከ 2016 ግማሽ አመት ድረስ በተሰጠው የዜግነት አገልግሎት ወደ 53 ነጥብ 7 ቢሊዮን ብር የሚገመት ሥራ ተሠርቷል፡፡

በዚህ የዜግነት አገልግሎት 1ሺህ 533 ቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤቶች ግንባታ፣ ለአቅመ ደካሞችም 11ሺህ 972 ቤቶች ተሠርተዋል፡፡ እነዚህ

**ወደ ገጽ 10 ዞሯል**

# ‹‹በምሥራቅ ሐረርጌ በ93 ሺህ ሄክታር መሬት...

**ከ9ኛው ገጽ የዞረ**

የልማት ሥራዎች ዘርና ኃይማኖት ልዩነት ሳይደረግ በአካባቢው ለሚኖር ማኅበረሰብ የተሠራ ሥራ ነው፡፡ ተጠቃሚውም ሆነ በልማቱ የተሳተፈው ኢትዮጵያዊ ነው፡፡ ማኅበረሰቡ እያደረገ ያለው ተሳትፎ በተለያየ መንገድ ይገለጻል፡፡

ለታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ የሚውል ቦንድ በመግዛት በተሠራው ሥራም አበረታች ውጤት ታይቷል፡፡ በያዝነው በጀት አመት ብቻ በ53ሚሊዮን ብር ቦንድ ግዥ ተከናውኗል፡፡ ለሀገር መከላከያ ሰራዊትም ከሕዘቡ ወደ 42ሚሊዮን ብር ተሰብስቦ ድጋፍ ተደርጓል። በአጠቃላይ በአካባቢና በሀገር ኢኮኖሚ ግንባታ ላይ አስተዋጽኦ ያላቸው ሥራዎች ተሠርተዋል ማለት ይቻላል፡፡ በተለያየ መንገድ እየተደረገ ያለው እንቅስቃሴ ሲታይ፤ የዞኑ ሕዝብ ለሀገረ መንግሥት ግንባታ የቆመ ማኅበረሰብ ነው ማለት ይቻላል፡፡

የጤና እና የትምህርት ተደራሽነትን ለማስፋት በተሠራው ሥራም በተለይም ኅብረተሰቡ የጤና መድን ፈንድ ተጠቃሚ እንዲሆን ሥራዎች ተሠርተዋል፡፡ የጤና አገልግሎት መስጫዎችን በመገንባት፣ ያሉትንም በማጠናከር፣ ተጠቃሚ ለመሆን የተሻለ አገልግሎት እንዲያገኙ ሆስፒታሎችና የጤና ኬላዎች ተናብበው የሚሠሩበትን ምቹ ሁኔታ በመፍጠር የተለያዩ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በቱሪዝም ኢንዱስትሪ ዘርፍም አካባቢው ላይ ሲያሠሩ የሚችሉ ምቹ ሁኔታዎች ምን እንደሆኑና መዳረሻዎቹንም ቢገልጹልን?**

**አቶ አያሴው፡-** በዞኑ በትላልቅ ደረጃ ሊጠቀሱ የሚችሉ ሦስት የቱሪዝም መዳረሻዎች አሉ፡፡ አንዱ የባቢሌ ዝሆን ሲሆን፣ ሁለተኛው ጋራቁንዱዶ፣ ሦስተኛ ሁልቃ የሚባል ዋሻ ነው፡፡ ከእነዚህ ሦስቱ በተለይም የዱር ፈረስ በሚገኝበት በጋራቁንዱዶ ብዙ ሥራዎች እየተሠሩ ናቸው። ፈረሱ የሚገኘው ምሥራቅ ሐረርጌ፣ ጃርሶና ጉሩሱም ወረዳ መካከል ነው፡፡ ከሦስት አመት በፊት የነበሩት ዘጠኝ ፈረሶች ብቻ ናቸው፡፡ አሁን ላይ ቁጥራቸው ወደ 33 ከፍ ብሏል፡፡

የዱር ፈረሶቹ የሚገኙበት ስፍራ ወደ ኢኮ ቱሪዝም እንዲቀየር፣ በኦሮሚያ ክልል ፕሬዚዳንት እውቅና ተሰጥቶታል፡፡ በመሆኑም ሰፊ የሥራ እንቅስቃሴ እየተደረገ ነው፡፡ የባቢሌ ዝሆኖችም ብዛታቸው ከ300 በላይ ሆኗል፡፡ እነዚህ ሀብቶች የቱሪዝም መስህብ ሆነው የኢኮኖሚ ጥቅም እንዲያስገኙ በልዩ ትኩረት እየተሠራ ይገኛል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በምሥራቅ ሐረርጌ ኢንቨስትመንት ለመሳብ የሚያስችል ምን ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል? ከዚህ ቀደም በአካባቢው በኢንቨስትመንት ላይ የተሰማሩ ካሉም ቢገልጹልን?**

**አቶ አያሴው፡-** በአካባቢው ላይ ኢንቨስተሮችን ሊስቡ የሚችሉ ሀብቶች ይገኛሉ። ለኢንቨስትመንት የሚሆኑ በተለይም በግብርና ላይ ለመሰማራት ለሚፈልግ ሰፋፊ የእርሻ መሬት አለ፡፡ በምድር ውስጥ ፀጋም በማድን ላይ መሰማራት የሚችሉበት ዕድል አለ፡፡ ኢንቨስተሩ በአካባቢው ላይ ለመሰማራት ቢፈልግ በጥሩ ሁኔታ ለመቀበል ፍላጎት መኖሩን ላረጋግጥ እወዳለሁ፡፡

በዞኑ የሚኖረው ማኅበረሰብ አካባቢው ላይ ልማት ለማከናወን ፍላጎት ያለውን ለመቀበል ዝግጁ ነው፡፡ ኢንቨስተሩ ፍጹም ሰላምና የተረጋጋ አካባቢ እንደሚፈልግም ይታወቃል፡፡ በዚህ በኩልም በአካባቢው አስተማማኝ ሰላም ስላለ ስጋት እንዳይገባችሁ ስል መልዕክቴን አቀርባለሁ። በዞኑ ቀደም ብለው በተለያየ የኢንቨስትመንት ዘርፍ ላይ የተሰማሩ ኢንቨስተሮች አሉ፡፡ አብዛኞቹም የተሰማሩት በግብርና ሥራ ላይ ነው።



**አዲስ ዘመን፡- ለአካባቢው ወጣቶች የሥራ ዕድል ለመፍጠር ምን ያህል ሥራዎች ተከናውነዋል?**

**አቶ አያሴው፡-** በዞኑ በተለያየ የትምህርት ደረጃ ላይ የሚገኙ፣ የትምህርት ዕድልም ያላገኙ ወጣቶች አሉ፡፡ እንዲህ በተለያየ ደረጃ ላይ ለሚገኙ ወጣቶች እንደየችሎታቸው የሥራ ዕድል ለመፍጠር በዞኑ በኩል የተለያዩ ተግባራት ሲከናወኑ ቆይተዋል። በተለይም ላለፉት ሦስት አመታት በልዩ ትኩረት ተሠርቷል፡፡

ሰፊ የሥራ ዕድል የሚፈጥረው የግብርናው ዘርፍ በመሆኑ በግብርና ከፍተኛ ቁጥር ላለው ወጣት የሥራ ዕድል መፍጠር ተችሏል፡፡ በማር ልማት፣ በከብት ማድለብና በሌሎችም የግብርና ሥራዎች ላይ ተሰማርተው እያደረጉት ባለው እንቅስቃሴ ብዙዎች ውጤታማ መሆን ችለዋል። የአካባቢው የኢኮኖሚ ምንጭ ቡና፣ ጫትና ሌሎችም የግብርና ውጤቶች በመሆናቸው በእነዚህ ላይ ትኩረት ይደረጋል፡፡

በአሁኑ ጊዜም ወጣቱ በበጋ ቆላ መስኖ ልማት በስፋት ተሰማርቶ እያለማ ይገኛል። አንዳንዶችም ያለሙትን ስንዴ ለገበሬዎች ኅብረት ሥራ ማኅበራትና ለተለያየ ገበያ በማቅረብ ተጠቃሚ መሆን ጀምረዋል፡፡ ሌላው የሥራ ዕድል ደግሞ የግንባታው ዘርፍ ነው፡፡ በሌሎችም የሥራ ዘርፎች እንዲሰማሩ ተደርጓል፡፡

አሁን ላይ የአካባቢው ወጣት ሥነልቦናም ሆነ የአስተሳሰብ ሁኔታ ተቀይሯል፡፡ ወይም እየተሻሻለ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ሰው ጠባቂ ወይንም የቅጥር ሥራ ፈላጊ ከመሆን ይልቅ የራስን ሥራ ፈጥሮ የተሻለ ገቢ አግኝቶ ለራስም ለሀገርም ጥቅም የሚያስገኝ ሥራ መሥራት የሚለው ፍላጎት በወጣቱ በኩል እየተፈጠረ ነው፡፡

ይህን ለማለት የሚያስችለው አሁን ወጣቱ እያቀረበ ካለው ጥያቄ በመነሳት ነው፡፡ አሁን ወጣቱ እየጠየቀን ያለው በተፋሰስ ልማት ሥራ የለማ ተራራ እንድንሰጠው እንጂ ቅጥር አይደለም። ይሄ አንዱ ማሳያ ነው፡፡

ወጣቶች የበለጠ እንዲበረታቱ ለማድረግ ከተከናወኑት ተግባራት መካከልም ኑሯቸውን በተለያዩ የውጭ ሀገራት ያደረጉ የምሥራቅ ሐረርጌ ዞን ተወላጆች በገንዘባቸው ያደረጉት ድጋፍ ፤ የዞኑና የወረዳው መዋቅር ደግሞ ለሥራ የሚሆን የመሬት አቅርቦትን ምቹ ማድረግ፣ እንዲሁም የመሥሪያ ሼዶችን ሠርቶ ማቅረብ ይጠቀሳሉ፡፡

በዚህ መልኩ ለወጣቶች የሥራ ዕድል እንዲፈጠርላቸው ሥራዎች ቢሠሩም ሁሉንም ወጣት ተደራሽ አድርገናል፣ ችግሮችም ተቀርፈዋል ብለን አፋችንን ሞልተን ለመናገር አንደፍርም። የበለጠ መሥራት ይጠበቅብናል። ወጣቱ በትምህርት ላይ ካልሆነ ወይንም ሥራ ካልሠራ ወዳልተፈለገ ነገር ውስጥ እንደሚገባ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም ወጣቱ ወደ መጥፎ ድርጊት እንዳያመራ መታደግ ይኖርብናል።

**አዲስ ዘመን፡-በምሥራቅ ሐረርጌ ያለውን ተጨባጭ የሰላም እና የፀጥታ ሁኔታ ጋር አያይዘው ምን ይላሉ?**

**አቶ አያሴው፡-** በልማቱ እንደተደረገው እንቅስቃሴ ሁሉ የአካባቢ ፀጥታን በመጠበቅ ረገድም ሥራዎች እየተሠሩ ይገኛሉ፡፡ በሰላም በፀጥታ ዙሪያ ላረጋግጥ የምፈልገው በምሥራቅ ሐረርጌ የሚገኙ 583 ቀበሌዎችና 23 ወረዳዎች ውስጥ ነዋሪው ቀርቶ ነዋሪ ያልሆነው ሁሉ ያለስጋት ሊንቀሳቀስ ይችላል። እንደፈለገውም እየተንቀሳቀሰ ነው፡፡ ነዋሪው የአካባቢውን ሰላም ለማስጠበቅና የፀጥታ መደፍረስና ስጋት እንዳይኖር ቀድሞ የመከላከል ሥራ በነዋሪው በኩል ሌትከቀን እየተሠራ ይገኛል፡፡

ማኅበረሰቡ በፀጥታ ዙሪያ እየሠራ ያለው ጠብቀኝ፤ እጠብቅሀለሁ የሚል መርህ ይዞ ነው። እንቅስቃሴ እየተደረገ ያለው ሁሉንም ኅብረተሰብ ባካተተ መልኩ በጋራ ወጣቶች፣ ሴቶች፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ አባገዳዎች፣ የሃይማኖት አባቶች፣ የፀጥታ ኃይሎችን በመያዝ ነው፡፡

የዞኑ ነዋሪ እጅና ጓንት ሆኖ ለአካባቢው ደህንነት እየሠራ ያለው ‹‹ይሄ መንግሥት የእኔ መንግሥት ነው፡፡ በራሴ ድምጽ የመረጥኩት መንግሥት ነው፡፡ እየተሠራ ያለው የልማት ሥራም የእኔ ነው፡፡›› እያለ ነው፡፡ ምሥራቅ ሐረርጌ ዞን 23 ወረዳዎችና 583 ቀበሌዎች ይገኛሉ፡፡ በእነዚህ ሁሉ አካባቢዎች የሚኖሩትም ሆኑ በአካባቢዎቹ ለተለያየ ምክንያት የሚንቀሳቀሱ እና ገብተው የሚወጡ ሰዎች ደህንነታቸው የተጠበቀ በመሆኑ ምንም ዓይነት ሥጋት የለም፡፡ በዚህ በኩል እየተሠራ ያለው ሥራ እንደሀገርም ቢሆን ለሌሎች አካባቢዎችም ተምሳሌት ሊሆን የሚችል ነው። እንዲህ ያለው የተሳካ ሥራ ያለ ማኅበረሰብ ተሳትፎ የሚመጣ ባለመሆኑ አሁንም ምስጋናውን መውሰድ ያለበት የአካባቢው ነዋሪ ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በመጨረሻ የሚያስተላልፉት መልዕክት ካልዎት ?**

**አቶ አያሴው፡-** የምሥራቅ ሐረርጌ ዞን ነዋሪ አንተ ማነህ ሳይል ሰው፣ ሰው በመሆኑ ብቻ በፍቅር፣ በመከባበርና በመረዳዳት አብሮ የሚኖር እንደሆነ ይታወቃል፡፡ እንደአዲስ የምንነግረው አይደለም። አሁንም ቢሆን ሀገራችን በገጠማት የውስጥ አለመረጋጋትና ግጭት ምክንያት በአንዳንድ የኢትዮጵያ ክፍሎች እያጋጠመ ያለው አለመረጋጋት፣ የሰላም እጦትና ስጋት በአካባቢው በተመሳሳይ እንዳይፈጠር በሰላም ዙሪያ አንድነቱን አጠናክሮ እያከናወነ ያለውን ተግባር አጠናክሮ እንዲቀጥል መልዕክቴን አስተላልፋለሁ፡፡

በልማቱ በኩል አጠናክሮ በመቀጠል በተለይም የተጀመረውን የበጋ ቆላ መስኖ ስንዴ ልማት በተሻለ ሁኔታ በማምረት ከዚህ ቀደም ከሌሎች ይጠብቅ የነበረውን እርዳታ እንደሚያስቀርም እምነቴ ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ በዝግጅት ክፍሉ ስም እናመሰግናለን፡፡**

**አቶ አያሴው፡-** እኔም አመሰግናለሁ፡፡

**የምሥራቅ ሐረርጌ ነዋሪ ስንዴን የሚያውቀው ወይም የሚያገኘው በልማት ሳይሆን፣ በእርዳታና በተለያየ መንገድ ነበር፡፡ አሁን ግን የአካባቢው አርሶአደር እራሱ አልምቶ ተጠቃሚ ለመሆንና የሀገርንም ኢኮኖሚ ለማሳደግ ወገቡን ጠበቅ አድርጎ ታጥቆ ተነስቷል**

ስፖርት እና መዝናኛ

# ፋሽን

## ሴቶችን ከውበት ሳሎን ያዋለው የጥፍር ሥራ

**ሰሚራ በርሀ**

«የሴት ልጅ ውበቷ ጸጉሯ ነው» እንደሚባለው ሁሉ አሁን አሁን ደግሞ ሴቶች ለእጆቻቸውና ለእግሮቻቸው ጥፍር አብዝተው ሲጨነቁና ሲጠበቡ ማስተዋል ተለምዷል፡፡ የእጅም ሆነ የእግር ጥፍሮችን በንጽህና መጠበቅ ወንዱንም የሚመለከት ጉዳይ ቢሆንም፣ ሴቶችን ግን የጥፍራቸው ጉዳይ በእጅጉ ያሳስባቸዋል። ከንጽህና አለፍ ብሎም የእጅና የእግሮችን የጥፍር ውበትን መጠበቅና ማስዋብ ለሴት ልጅ የውበት መገለጫ መሆን ከጀመረ ቆይቷል፡፡

ለዚህም ነው አብዛኞቹ ሴቶች ጊዜ ባመጣቸው የተለያዩ የመዋቢያ ቁሳቁሶች ጥፍራቸውን ሲያስውቡ የምንመለከተው፡፡ ሴቶች ጥፍራቸውን ለማስዋብ ከሚጠቀሟቸው ቁሳቁሶች መካከል «ጥፍር ቀለም» ቀዳሚው ነው፡፡ ቀደም ሲል ጥፍራቸውን አሳድገው በሚፈልጉት ቅርጽ ሞርደው በማሾል ይዋቡበትም ነበር፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ከተለያዩ ግብዓቶች እና ንጥረነገሮች ውህድ የሚሠራው ሰው ሠራሽ (አርቴፊሺያል) ጥፍር ዋነኛው የሴቶች መዋቢያ ሆኖ መጥቷል። በመሆኑም ሴቶቹ ተፈጥሯዊ ጥፍራቸውን ማሳደግ ሳይጠበቅባቸው በሚፈልጉት የጥፍር ቅርጽ ዓይነትና ርዝመት ጥፍራቸውን ለተለያዩ ፕሮግራሞች ይሠራሉ፡፡

በአሁኑ ወቅትም በየውበት ሳሎኑ ጥፍር የሚሠሩ እንስቶች ቁጥር በርክቷል፡፡ ይህን አገልግሎት የሚሰጡ ባለሙያዎች እንዲሁም ሙያውን የሚያስተምሩ ማሰልጠኛዎች እየተበራከቱ ይገኛሉ፡፡ አገልግሎቱ ጫን ያለ ዋጋ የሚጠይቅ መሆኑ ብዙዎች ወደ ሥራው እንዲያዘነብሉ እያደረጋቸውም ነው፡፡ በሌላ መልኩ ለሥራ ዕድል ፈጠራም አስተዋጽኦ እያደረገ ይገኛል፡፡

ከዚህ ቀደም ጸጉራቸውን ብቻ ለመሠራት ወደ ውበት ሳሎን ያቀኑ የነበሩ አብዛኞቹ እንስቶች አሁን ላይ ጥፍራቸውን ለመሠራት ጭምር ወደ ውበት ሳሎን ያቀናሉ፡፡ የሴቶች የውበት ሳሎን ሰፊ ጊዜ የሚወስድ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ብዙዎች አገልግሎቱን ማግኘት የሚችሉት አስቀድመው በሚይዙት ቀጠሮ መሠረት እንደሆነ የሙያ ባለቤቶች ይናገራሉ፡፡

ፍላጎት አብርሃም (ስሟ የተቀየረ) የጥፍር ሥራ ትምህርት ተምራ በሥራ ውስጥ የምትገኝ ወጣት ናት፡፡ ሙያውን ለመማር የሁለት ወር ተኩል ጊዜ ወስዶባታል። በጥፍር ሥራ ላይ ከባዱ ነገር አገልግሎቱን ፈልገው የሚመጡ ደንበኞችን ስሜት ጠብቆ ማስተናገድ እንደሆነም ተናግራለች፡፡ ትምህርቱ መሠረታዊ የሚባሉ የጥፍር ሥራዎችን ሲያካትት በቶሎ ለመልመድና ብቁ ለመሆን እንደሰው አቀባበል የሚወሰን መሆኑን አስረድታለች፡፡

በሥራው ላይ ለአምስት አመት ያህል የቆየችው ወጣት ፍላጎት፤ የጥፍር ሥራው ዓይነት እንደ ፕሮግራሙ ዓይነት ይለያያል ትላለች፡፡ ደንበኞች ወደ ውበት ሳሎኑ ሲመጡ መሠራት የሚፈልጉትን ዲዛይን ከተለያዩ ገጾች ላይ ተመልክተው እንደሚመጡ ጠቅሳ፣ እሷ ግን በፎቶ ተመልክተው የመጡትን ሥራ ከመሠራታቸው አስቀድሞ ሙያዊ ምክር ትሰጣቸዋለች፡፡ የጥፍር ዲዛይን እና የምንጠቀመው የጥፍር ቀለም እንደየ ጥፍራችን ቅርጽና ቆዳ እንዲሁም ቀለማችን ይለያያል ብላ ታስረዳቸዋለች፡፡

በመሆኑም ጠቆር ያለ የቆዳ ቀለም ላላቸው ደንበኞች ፍክት ያለ የጥፍር ቀለም፣ ነጣ ያለ የቆዳ ቀለም ላላቸው ደግሞ ደብዘዝ ያሉ የጥፍር ቀለሞችን በመጠቀም እነ ፍላጎት የደንበኞቻቸውን ፍላጎት ለማሟላትና ለማስደሰት ይጥራሉ፡፡ እሷ እንዳለችው፤ በአሁኑ ሰዓት በብዙዎች ዘንድ የተለመደው የጥፍር ሥራ ዲዛይን ዓይነት «ፍሬንች» ዲዛይን የተባለው ነው፤ ይህም ለሁሉም የቆዳ ቀለም ዓይነት የሚሆን እና ለፕሮግራምም ሆነ ለአዘቦት ቀን ቢደረግ ቀለል ያለና ልዩ ውበትን የሚያላብስ የብዙዎች ምርጫ ነው፡፡

ሌላኛዋ የጥፍር ሥራ ባለሙያ ናርዶስ ከበደ (ስሟ የተቀየረ) በሥራው ሁለት አመት ቆይታለች፡፡ ናርዶስ የጥፍር ሥራ ይስባት ነበርና ለአንድ ወር ከ15 ቀን የሚሰጠውን ሥልጠና ከወሰደች በኋላ ሥራውን ተቀላቅላለች፡፡ የጥፍር ሥራ ዓይነቶች የተለያዩ እንደሆኑ ስትገልጽ ፊትለፊቱ ላይ የአራት ማዕዘን ቅርጽ ያለው «ስኩዌር»፣ የእንቁላል ቅርጽ ያለው ደግሞ «አቫል» እንደሚባሉ ጠቅሳ፤ የጥፍር ዲዛይኖቹ ቁመትም እንደ ደንበኛዋ ፍላጎት እንደሚወሰን ነው የተናገረችው፡፡

«ጥፍሮቹ ሰው ሠራሽ እንደመሆናቸው ቆይታቸውም ውስን ነው» የምትለው ናርዶስ፤ ለአጭርና ለረጅም ጊዜ መቆየት የሚችሉ የጥፍር ዓይነቶች እንዳሉም ገልጻለች። እሷ እንዳብራራችው፤ ልጥፍ የሚባለው በሰዎች የጥፍር ልክ ተመሳስሎ የተሠራ ሲሆን፣ በራሱ ለጥፍር መለጠፊያ ተብሎ በተዘጋጀ ማጣበቂያ ጥፍራቸው ላይ ከተለጠፈ በኋላ በሚፈለገው ቅርጽ እና ቁመት ተሞርዶ ይሠራል። ሌላኛው ሰው ሠራሽ ጥፍር ጄል ሲሆን በእንስቷ ጥፍር ላይ ተሞልቶ ለዚህ ተብሎ በተዘጋጀ ማድረቂያ ማሽን ውስጥ ይደርቃል፡፡ በተለያዩ ኬሚካሎች እና ፓውደሮች ተቀላቅሎ የሚዘጋጀው ደግሞ አክሌሪክ ይባላል፡፡

አክሌሪክ የጥፍር ዓይነት ከባድ የኬሚካል ሽታ ስላለው ለነፍሰ-ጡር ሴት የማይመከር ሲሆን ባለሙያዎችም ሲሠሩ የራሳቸውን ጥንቃቄ ያደርጋሉ። ይህም ለረጅም ጊዜ የሚቆይ የጥፍር ዓይነት ነው፤ የጥፍሩ ዓይነት ከተመረጠ በኋላ የሚቀባው የጥፍር ቀለምም እንዲሁ ተመሳሳይ ነው፡፡

የጥፍር ቀለሞቹ በውበት መጠበቂያ ሱቆች ይገኛሉ፤ ቀለሞቹን በቤታቸው መቀባት ይችላሉ፡፡ ሌላኛው ደግሞ ሺላክ ለውበት እና ዲዛይን ለማድረግ የሚውል ነው፡፡ ይህ የጥፍር ቀለም ዓይነት ለማስለቀቅ የራሱ ጥንቃቄ ማድረግ ይፈልጋል፤ ረጅም ጊዜ ሳይለቅ የሚቆይ በመሆኑ ሴቶች በራሳቸው ጥፍር ላይ ለመቀባትም ቢሆን ወደ ውበት ሳሎን ጎራ እንደሚሉ ናርዶስ ትናገራለች፤ «ጥፈራቸውን የተሠሩ እንስቶች ለማስለቀቅ ሲፈልጉም ጥንቃቄ ቢያደርጉና ወደ ውበት ሳሎኑ ቢያመሩ መልካም ነው» ትላለች፡፡

ሌላኛዋ ባለሙያ ገሊላ አስራት ትባላለች፡፡ አንድ እንስት ጥፍሯን ለመሠራት ወደ ውበት ሳሎን ስትመጣ የሚወስደው ጊዜ፣ የምታልፈው ሂደት እንደምትሠራው የጥፍር ዓይነት የሚወሰን መሆኑን ጠቅሳ፤ ልጥፍ ከሆነ አጭር ጊዜን ይወስዳል ትላለች፡፡ ለዚህም በመጀመሪያ ተፈጥሯዊ ጥፍርን የማጽዳትና መቁረጥ እና የመሞረድ ሂደቶች አሉት፡፡ ሙሌት እና ጄል ደግሞ ለማድረቅ ጊዜ ከመውሰዱ ባሻገር የሚቀባው እንደ ዲዛይኑ ከአንድ ሰዓት በላይ ይወስዳል፡፡ ጥፍር ቀለምን በመጠቀም ብቻ ከሚሠራው ዲዛይን ውጪ የተለያዩ አብረቅራቂ ፈርጦች እንደየፍላጎታቸው የሚደረግ መሆኑን አስረድታለች፡፡

ለእያንዳንዱ አገልግሎት የሚኖረው ክፍያም እንደየ አካባቢው የሚለያይ ሲሆን፤ ሺላክ ጥፍር ቀለምን ለመቀባት ከ150 ብር ጀምሮ እስከ ሦስት መቶ ብር፣ ልጥፍ ከሺላክ ጥፍር ቀለም ጋር ዘጠኝ መቶ ብር፣ ሙሌት ደግሞ ከአንድ ሺህ እስከ አንድ ሺህ ሁለት መቶ ብር፣ አክሌሪክ የጥፍር ሥራ ከሁሉም ከፍ ያለ እንደመሆኑ ከ1500 ብር በላይ መሆኑን ገልጻለች፡፡

በመጨረሻም መዋቢያ ቁሳቁሶቹ የራሳቸው የሆኑ የጎንዮሽ ጉዳት እንዳላቸው የምትገልጸው ገሊላ ጥፍራችን አየር የሚፈልግ በመሆኑ ጥፍራቸውን አብዝተው የሚሠሩ ሴቶች በተደጋጋሚ ባይሠሩ እና ተፈጥሯዊ ጥፍራቸውን በማይጎዳ መልኩ የጊዜ ልዩነት እየጠበቁ ቢሠሩ የተሻለ እንደሆነ ሙያዊ አስተያየቷን በመስጠት ሃሳቧን ቋጭታለች፡፡

# ትዝብት/ ማረፊያ

## ወጣት ጡረተኞች

**ቃልኪዳን አሳዬ**

ጡረተኝነት መልኩ ብዙ ነው፤ ሰዎች ረጅም እድሜ ከኖሩ፣ ከተማሩ፣ ከሠሩና የቻሉትን ያህል በጉብዝናቸው ዘመን ከሮጡ እና ከታተሩ በኋላ እድሜ ሲገፋ ወደ ጡረተኝነት ይሸጋገራሉ፡፡ ታዲያ ይህ ማለት ሁሉም በእድሜ ዘመኑ የሚያገኘውና በተፈጥሮ ዑደት ውስጥ የሚጎናጸፈው ከእግዜሩ የተቸረ ጸጋ ነው፡፡

ይህ የጡረተኝነት ዘመን ምንም እንኳን እንከን የሌለበት ሂደት ቢሆንምና የራሱ የሆነ ጣዕም እና ሂደት ቢኖረውም፣ ምናልባት የጡረተኝነትን ዘመን በጥቂቱ ጎዶሎ የሚያደርገው ጡረተኞቹ ከዚህ በፊት ራሳቸውን ችለው ተንቀሳቅሰው ማድረግ የሚችሉትን ነገር እየቀነሱ በመሄዳቸው መደገፊያ ምርኩዝ የመሻታቸው ጉዳይ ነው፡፡

ይህ የሚሆንበት ዋነኛ ምክንያት ቀድሞ የነበራቸው አቅም በአሁን ወቅት ስለማይኖራቸው እንዳሻቸው መሆን የማይችሉ በመሆኑ ነው፤ ታሪክ ራሱን ይደግማል እንደሚባለው ሰዎች ልክ እንደ ልጅነታቸው ጊዜ ለመዳህ፣ ለመብላት፣ ለመጠጣት እና አያሌ ተግባራትን ለማከናወን የእናትና የአባታቸው ድጋፍ እንደሚያስፈልጋቸው ሁሉ የሌሎችን ሰዎች ድጋፍ የሚሹበት ወቅት ሲሆን፤ ይህም ጸጋውና ምሕረቱ ከበዛው ከእግዜሩ የሚቸር ነው፡፡

በኢትዮጵያ በየዓመቱ ከግልና ከመንግሥት ዩኒቨርሲቲዎች አያሌ ቁጥር ያላቸው ወጣቶች በተለያዩ የትምህርት መስኮች በብዙ ልፋትና መከራ ይመረቃሉ። ታዲያ ከእነኝህ ወጣቶች መካከል ወደ ሥራ የገቡት ምን ያክሎች ናቸው? በሥራ ማጣት፣ ላይ ታች እየዳከሩ ጊዜያቸውን የሚያሳልፉትስ? የሚለው የዘወትር ጥያቄዬ ነው። ምስጋና ይግባትና ይሄን ጽሑፍ እንድፅፍ በማነሳሳት ሀሳቤን እንድገልጽ በር ለከፈተችልኝ ለአንዲት ውድ ወዳጄ።

ወላጅ ከተረፈው ሀብቱ ቀንሶ ሳይሆን ከእለት ጉርሱ አሳንሶ ልጆቹን ሲያስተምር ልጄ ተምሮ፣ እውቀት ቀስሞ ሰው ይሆንልኛል የሚለውን በጎ እሳቤ በመያዝ ነው፡፡ ከምንም በላይ ወላጅ ልጁ በደከመበት እና ባረጀበት ወቅት ምርኩዝ እንደሚሆንለት ያስባል፤ ታዲያ ነገሩ የተገላቢጦሽ ሆኖ በብዙ መስዋዕትነት የተማረው ልጅ ገና በለጋነቱ ከወላጆቹ ጥገኝነት መላቀቅ ተስኖት የእናቱን መቀነት ያስፈታል፡፡ ነገር ግን በሩብ፣ በመንፈቅና በበጀት ዓመቱ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዜጎችን ሥራ አስያዝን የሚሉ ሪፖርቶችም በየወቅቱ መውጣታቸው አልቀረም፡፡

ብዙ በመሥራት ራስን፣ ቤተሰብን እና ሀገርን መቀየር በሚቻልበት በዚህ የብርቱነት ወቅት ቁጭ ብለው ጊዜያቸውን በማባከን የኋሊት የሚጓዙ ወጣቶችን ቤቱ ይቁጠራቸው፡፡ ታዲያ በዚህ ጊዜ ወጣቶች ገና በለጋነት እድሜያቸው በቤተሰቦቻቸው ጫንቃ ላይ ጥገኛ በመሆን የወጣት ጡረተኞች ሆነዋል።

ኢትዮጵያ ካሏት ዜጎች ውስጥ አብዛኛው ወጣት እንደሆነ ይታወቃል፡፡ በዚህም በአፍሪካም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ በሰው ሀይል ከበለጸጉ ሀገራት አንዷና ተጠቃሽ ናት፡፡

ዜጎቿም በሥራ አጥነት እና በድህነት መኖሩን ለመሸሽ በሕጋዊም ሆነ በሕገወጥ መንገዶች ባሕር ማዶ በመጓዝ በተለያዩ ሀገራት እንጀራ ፍለጋ ተሰማርተዋል፡፡ በዚህም ምንም እንኳን ተሳክቶላቸው ሕይወታቸው የተቀየረላቸው ጥቂት ዜጎች ቢኖሩም ነገር ግን ቤተሰቦቻቸው ረብጣ ዶላር ሲጠብቁ አስከሬናቸው የተላከላቸው ብዙ ናቸው። ይህ ጉዳይ እስከ መቼ ይቀጥል ይሆን? ኃላፊነቱስ የማን ይሆን?

ወጣትነት ሲደመር ጡረተኝነት ውጤቱ ከባድ ነው፤ እኔም እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ ከዩኒቨርሲቲ ተመርቄ ከወጣሁ በኋላ ለጥቂት ጊዜያት ወጣት ጡረተኝነትን በሚገባ አጣጥሜዋለሁ፤ በወቅቱም ነገሮችን የማድረግ ፍላጎቱና ምኞቱ እያለኝ አቅም የማጣት ስሜት ይጫጫነኝ ነበር፡፡

አባቴ ለበርካታ ዓመታት በመንግሥት ሠራተኝነት ጊዜውን አሳልፏል፤ አሁንም በዚሁ ሥራ ላይ ይገኛል፤ ተማሪ እያለሁ ሁሌም አንድ የሚናገረኝ ነገር ነበር «እኔ የማወርስህ ጋሻ መሬትም ሆነ ሀብት የለኝም፤ አንተን አስተምሮ ለቁምነገር ከማብቃት በስተቀር ስለዚህ ጎብዘህ ተማር» ይለኝ እንደነበር እስካሁን ይታወሰኛል፤ እኔም ቁርጤን አውቄ ከመመረቅ በዘለለ ያለኝን አቅም አሟጥጬ በመጠቀም ተወዳዳሪ ዜጋ መሆን እንዳለብኝ ይሰማኝ ነበር፡፡

የሆነው ሆኖ ትምህርቴን በከፍተኛ ማዕረግ ካጠናቀቅኩ በኋላ ምንም እንኳን ስሜቱ መራርና ከባድ ቢሆንም ደከመኝ ሰለቸኝ ሳልል የአንድ ዓመት ከመንፈቅ ጊዜዬን የወጣት ጡረተኛ በመሆን አሳልፌያለሁ፡፡

በአሁኑ ወቅት ምንም እንኳን እራሳቸውን እና ቤተሰቦቻቸውን ለመቀየር ቀን ከሌት የሚታትሩ ጥቂት ወጣቶች ቢኖሩም፤ በሌላ በኩል ስለነገ ዓላማና ራዕያቸው ከማሰብና ከማቀድ ይልቅ ቁጭ ብሎ ስለ ትናንትናው ታሪክ በማሰብና በመጻጻት መኖሩን የተያያዙም አልጠፉም፡፡ ይህንን ጉዳይ ትኩረት ሰጥቶ በመሥራት የወጣቱን ዕጣ ፈንታ ከመቀየር ይልቅ ያለፈን ታሪክ ስቦ አውጥቶ ለወጣቱ በማቀበል የግጭት ነጋዴ የሆኑም አልጠፉም፡፡

በሀገራችን የፍላጎት እና የአቅርቦት አለመመጣጠንን ተከትሎ የኑሮ ውድነቱ እያደገ ቢሄድም፤ ሀይ ባይ በማጣቱ በቀን ሶስት ጊዜ መመገብ ቅንጦት እየሆነ በመጣበት በዚህ ወቅት ከዓመት ወደ ዓመት እየጨመረ የመጣውን ሥራ አጥ የሰው ኃይል ቁጥር ከመንግሥትም ሆነ ከግሉ ዘርፍ መፍትሔ የሚሻ አንገብጋቢ ጉዳይ እንደሆነ እስካሁን ቀጥሏል።

ምንም እንኳን እኔም ከእናንተ ያልተሻልኩ ሰነፍ ቢጤ ወንድማችሁ ብሆንም ይህንን የወጣትነት ዘመን በፍጹም ዳግም የማታገኙበት ዓመታቶች ሩቅ አይደሉምና ካላችሁበት የጭንቅ ጊዜያቶች ውስጥ በመውጣት ተንቀሳቀሱ አስቡ አቅዱ ሥሩ ከማንም ሰው ውጪ መኖር እንደምትችሉ ራሳችሁን በማሳመን በፈጣሪችሁ እርዳታ ራሳችሁን አሳድጉ እንጂ አትዳከሙ፡፡

ራስን መምራት የሚጀምረው ራስን ከማወቅ፣ ማንነታችንን ከመገንዘብ፣ ያለፉት ልምምዶቻችን በእኛ ላይ ያስከተሉትን ተፅዕኖዎች በመለየት እና ያሉንን መልካም ዝንባሌያችን ምን እንደሆኑ አውቆ ከማዳበር ነው፡፡ ስለራሳችን በሚገባ በማወቅና ፍላጎታችንን በመለየት ለሕይወታችን ግብ ካላስቀመጥን የመጣውንና ያጋጠመንን ነገር ሁሉ እንደግብ በመቁጠር እድሜያችንን እናባክናለን፡፡

ሕይወት የምርጫና የውሳኔ ጉዳይ ናት፤ አሁን ያለንበት የእያንዳንዳችን የኑሮ ሁኔታ የቀደም ውሳኔዎቻችን ውጤቶች ናቸው፤ ካሳለፋችሁት ዓመታቶች ይልቅ ገና ያልኖራችሁባቸው ዓመታቶች ይበዛሉና ወደ ፊት እያያችሁ በብርታት ተራመዱ እላለሁ፡፡

# ነፃ ሃሳብ

# ከከተማ እስከ ሀገር በሚዘልቀው ቀጣዩ የኢኮኖሚ ባቡር ለመሳፈር

ታምራት ተስፋዬ

ዓለማችን በ20ኛው ክፍለ ዘመን ከተመለከተቻቸው እጅግ ተፅዕኗቸው ጎልቶ ከሚታይ የከተማ ፕላነሮችና አንዱ ለመሆኑም በርካቶች በአንድ ድምፅ ይስማሙበታል፡፡ አሜሪካዊ ነው፡፡ ሮበርት ሞሰስ ይባላል፡፡ ‹‹ዘ ማስተር ቢልደር /Master Builder›› በሚል ቅፅል ስሙ ይበልጥ ይታወቃል፡፡

እኤአ በ1888 የተወለደው ይህ ሰው አንድ ከተማ በርካታ ሰማይ ጠቀስ ሕንፃዎች ከመደርደር ይልቅ በዛፍ የተከበቡ ምቹ ጎዳናዎች፣ ፓርኮችንና ስር ነቀል ለውጥ ሊያመጡ የሚችሉ የከተማ ልማት ሜጋ ፕሮጀክቶች ሊኖራት እንደሚገባ በማመንና በማሳመን የአሜሪካዋን ኒውዮርክ ከተማ በሃሳብና በራዕዩ ልክ ገልብጦ እንደሠራት ብሎም ለክቶ እንደሰፋት ይታመናል፡፡

ሞሰስ ኒውዮርክ ከተማን የግል ሃሳቡንና ፍልስፍናውን በሚያንፀባርቅ መንገድ መገንባት ሲያስብ አንስቶ በግንባታ ሂደት ላይ እያለም የበርካቶች የቅሬታ አስተያየት ተለይቶት አያውቅም። ፓርክ ‹‹ምን ያደርጋል›› የሚሉም በርካቶች ነበሩ። ሰውየው ግን ሠርቶ ማሳየትን ብቻ ምርጫው በማድረግ የሚወረወርበትን ድንጋይ እንደጡብ በመደርደር ኒውዮርክ ከተማን በሃሳብና በራዕዩ ልክ እውን ከማድረግ ያስቆመው አልነበረም፡፡

ከትናንት እስከ ዛሬ በከተማ መሃል የሚገኙ መናፈሻ ፓርኮችና አረንጓዴ ስፍራዎች ከሚሸፍኑት መሬት አንፃር በተለይ የመሬት ጥበብ ባለባቸው ሀገራት ‹‹መተግበር የሌለበትና ቅንጦት ነው›› በሚል የሚነሱ ጥያቄዎች ብሎም ቅሬታዎች እዚህም እዚያም ማድመጥ የተለመደ ነው፡፡

የዘርፉ ምሁራን እንደሚገልፁት ከሆነ ግን፣ በአሁኑ ወቅት ዓለም ጥግግቱ ከፍ ያለ ወደ ጎን ከማስፋት ይልቅ ወደ ላይ የሚሰፋ ከተማን በማዋቀር በትንሽ ቦታ ላይ ብዙ ሕዝብ ማስፈርን አማራጭ አድርጋለች፡ ይህ አማራጭ ደግሞ ከተሞች ለመናፈሻ ፓርኮችና አረንጓዴ ቦታዎች ሰፊ ቦታ ቢሰጡም እንዳይጨናነቁ አድርጓቸዋል፡፡ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ደግሞ ከኒውዮርክ በላይ አይገኝም፡፡ ዓለም ላይ ኒውዮርክ ከተማ በጥግግት ከሚታወቁ ከተሞች ግንባር ቀደም ሆና ትጠቀሳለች፣ ይሁንና በዓለማችን ትልቁ ሴንትራል ፓርክና 341 ሄክታር የሚሆን ክፍት ስፍራ የሚገኘው በዚህች ከተማ ነው፡፡

‹‹የፓርኮችና አረንጓዴ ስፍራዎችን ፋይዳ ከሚሸፍኑት መሬት አንፃር መመልከት ከባድ ስህተት ነው›› የሚሉት የዘርፉ ምሁራን፣ ይህን በቅጡ መረዳት የሴንትራል ፓርኩን አመታዊ ጉብኚዎችና ገቢ ማወቅ በቂ ስለመሆኑ ይጠቁማሉ፡፡ Central Park. Com በሚል ገፅ ላይ እንደተመላከተውም፣ ሴንትራል ፓርክ እኤአ በ2023 ከዓለማችን ድንቅ 50 መዳረሻዎች መካከል በሦስተኛ ደረጃ ላይ የተቀመጠ ሲሆን በአመቱም 37 ነጥብ 5 ሚሊዮን ጎብኚዎችን አስተናግዷል፡፡

በእርግጥም መናፈሻ ፓርኮችና አረንጓዴ ስፍራዎች ጨምሮ አንድን ከተማ ትራንስፎርም የሚያደርጉ ሜጋ ፕሮጀክቶች ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚዊና ፖለቲካዊ ትርጉም እጅጉን ግዙፍ ነው፡፡ ከማኅበራዊ መስተጋብር አንፃር በተለይ በአሁኑ ወቅት ግላዊነት የጎላበትን የማኅበራዊ ግንኙነት ፈር በማስያዝ የጋራ ማኅበራዊ እሴትን ለማጠናከር የሚኖራቸው ፋይዳ በቀላሉ ሊታይ የሚገባው አይደለም፡፡ ከሕፃን እስከ አዛውንት ለሁሉም ክፍት እንደመሆናቸውም በአጠቃላይ ጤናማና ደስተኛ ማኅበረሰብ ለመፍጠር ሁነኛ አስተዋፅኦ ያበረክታሉ፡፡

የከተማ መናፈሻና ክፍት ስፍራዎች የመዝናኛ አማራጭ ብቻ ሳይሆኑ የሁለንተናዊ ሃሳብ መነሾ ስለመሆናቸውም በርካቶችን የሚያስማማ ሃቅ ነው። ‹‹ግሪካውያን ለዓለም ያበረከቷቸውን በርካታ የፍልስፍናና ሌሎች እውቀቶች የፈለቁት በአረንጓዴ ክፍት ስፍራና መናፈሻዎች ተሰባስበው በመወያየት በመማማራቸው እንደሆነ የሚመሰክሩም ቁጥራቸው ቀላል የሚባል አይደለም፡፡

ከኢኮኖሚ አንፃር በተለይ ከመስህብነት አንፃር የበርካታ ቱሪስቶች መናኸሪያ በመሆን ለቱሪዝም ኢንዱስትሪ መነቃቃት ብሎም እድገት፣ ለቋሚና ጊዜያዊ የሥራ ዕድል ፈጠራ፣ ለተደራጀ የመሠረተ ልማት ዝርጋታ ጨምሮ ለሁለንተናዊ እድገት ፋይዳቸው ጉልህ ነው፡፡ ከፖለቲካ መስተጋብር አንፃርም ‹‹ለኑሮ የምትመች ከተማ›› የሚል ስምና ዝናን ከፍ በማድረግ ተፅእኖ ፈጣሪነትን የማግዘፍ አቅማቸው እጅጉን ከፍተኛ ስለ መሆኑም የማይካድ ነው፡፡

ባለፉት አመታት በርካታ የዓለማችን ከተሞች እድገት ሕንፃ መደርደር አለመሆኑን ከሮበርት ሞሰስ ራዕይና አላማ እንዲሁም ስኬት በመረዳት እድገትና ፕላናቸውን ከፓርኮችና አረንጓዴ ስፍራዎች መስተጋብር ጋር አስተሳስረው ለመሄድ ብዙ ሠርተዋል፡፡ የተቀናጀ የከተማ ክልል ልማትን እውን ለማድረግ ብዙ ለፍተዋል፡፡ በጥረታቸው ልክ የተሳካላቸውም ቁጥራቸው ቀላል የሚባል አይደለም። አንዳንዶች በተለይ በማደግ ላይ ያሉ የአፍሪካ ሀገራት በአንፃሩ መሰል ዘርፈ ብዙ ትሩፋት ካለው የከተማ ልማት ትግበራ ጋር በአግባቡ ለመተዋወቅ አመታትን መጠበቅ ግድ ሆኖባቸዋል፡፡ አንዳንዶቹ ደግሞ ጨርሶ አልተዋወቁም፡፡

የአፍሪካ መዲና የሆነችውና በርካታ አህጉራዊና ዓለም አቀፍ ስብሰባዎችን የምታስተናግደው መዲናችን አዲስ አበባም ስሟን፣ ዝናዋንና የዕድሜ ርዝማኔዋ በሚመጥን መልኩ መናፈሻ ፓርኮችና አረንጓዴ ስፍራዎች ጨምሮ አንድን ከተማ ትራንስፎርም የሚያደርጉ ሜጋ ፕሮጀክቶች አላት ከማለት የላትም ለማለት ቀላል ሆኖ አመታት አስቆጥራለች፡፡ የመዲናዋ ነዋሪዎች ሆነ እንግዶች ውስጣዊ ስሜታቸውን የሚያዳምጥበትና አዕምሯዊ ዕረፍት የሚያገኙበት ብሎም የሚዝናኑበት ውብና ንፁሕ መናፈሻዎችና አረንጓዴ ስፍራዎችን ማግኘት ተቸግረው ረጅም አመታት ለማሳለፍ ተገደው ቆይተዋል፡፡

በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የሚመራው መንግሥት በአንፃሩ ስሟ ብቻ አዲስ ሆኖ መቶ ዓመታትን የዘለቀችን አዲስ አበባ፣ ስሟን በሚመጥን መልኩ ተወዳዳሪና ለነዋሪዎች ተስማሚ፣ ለጎብኚዎች አማላይ ከተማ ለማድረግም የተለያዩ ፕሮጀክት እውን አድርጓል፡፡ እውን ከሆኑት ባሻገር በሂደት ላይ የሚገኙ የተለያዩ ፕሮጀክቶችም ከተማዋን ዳግም የሚወልዱ ናቸው፡፡

በመዲናዋ እውን የሆኑ ፕሮጀክቶች፣ አሁን ላይ በማኅበራዊ፣ በኢኮኖሚም ሆነ በፖለቲካ አውድ ጉልህ አስተዋፅኦ ማምጣት እንደሚችሉ በተጨባጭ እያስመሰከሩ ናቸው፡፡ በኢኮኖሚ ረገድ በአግባቡ ከተሠራባቸው የገቢ ምንጭ ሊሆኑ እንደሚችሉም አያጠያይቅም፡፡ በሥራ ፈጠራው ወቅታዊውን የሀገሪቱ ራስ ምታት እያቃለሉም ናቸው፡፡

ሜጋ ፕሮጀክቶቹ የሀገሪቷንና የአፍሪካ መዲና እንዲሁም የዓለም አቀፍ ተቋማት መቀመጫ የሆነችውን አዲስ አበባ ገጽታ ለውጠዋል፡፡ ሁሌም እነዚህን ሥፍራዎች የሚያይ ዓይን (Eyes on the Street) አለና ለመዲናዋና ለእንግዶቿ ቀዳሚ አማራጭና መዳረሻ ከመሆን ባለፈ ባለፈ ቱሪዝምን ከማጐልበት አኳያ በገሃድ የሚታይ ትሩፋት አምጥተዋል፡፡

ከኢኮኖሚ አበርክቶ አንፃር ባለፉት ስድስት ወራት በቱሪዝሙ ዘርፍ ከሀገር ውስጥና ከውጭ ቱሪስቶች በተለያዩ መንገዶች ከ55 ነጥብ ስምንት ቢሊዮን ብር በላይ ወደ ከተማዋ ኢኮኖሚ ፈሰስ መሆኑን የአዲስ አበባ ከተማ ባሕል፣ ኪነ-ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ከቀናት በፊት ‹‹አወቁልኝ›› ብሎናል፡፡

ሜጋ ፕሮጀክቶቹ የውጭም ሆነ የሀገር ውስጥ ጎብኚዎች ምርጫና መዳረሻ በመሆን የከተማነት ሁለንተናዊ እድገት የሚያሳልጡ ብሎም የሚያደምቁ ሆነው እያየናቸው ነው፡፡ በተለይ ማታ ላይ እንቅስቃሴ የምታቆመውንና ወደ ጭለማ የምትቀየረውን ከተማ፣ 24 ሰዓት የደመቀች እንድትሆን አስችለዋታል፡፡ የተለያዩ ጥበባዊ የሆኑ አውደ ራእዮችን ኮንሰርቶችና የቲያትሮች ዝግጅቶች የሠርግ ፕሮግራሞችን ለማካሄድ የከተማዋ ቀዳሚ ተመራጭ ስፍራ ሲሆኑ እያየን ነው፡፡

ስመጥር የምጣኔ ሀብት ምሁራን እንደሚያስረዱት፣ ሕዝብን ተጠቃሚ ማድረግ የሚችልና የሚያድግ ኢኮኖሚ የመገንባት ተስፋ በተጨባጭና በእጅ ባለ እምቅ ሀብት ላይ መመስረት ይኖርበታል። በእጅ የሌለ የማይጨበጥ ነገር የሀገርን ኢኮኖሚ ለመመስረት መሞከር ባሕር በሌለበት ዓሣ ለማጥመድ ከመመኘት አይለይም።

ይህ በአምራች ዘርፉ ካየነው የአግሮ ፕሮሰሲንግስ ወይንም የግብርና ምርቶች በማቀነባበር ሁለንተናዊ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ የሚሹ ሀገራት በግብርና ዘርፍ በእንስሳትም ሆነ በአትክትልና ፍራፍሬው በተጨባጭ እጅ ያለ ዕምቅ በተለይም ሊለማ የሚችል ሰፊ መሬት፣ ብቁ ሙያተኛና ፣ ተስማሚ የአየር ንብረትና የውሃ ሀብት ሊኖራቸው ግድ ይላል እንደ ማለት ነው፡፡

ኢትዮጵያ ከግብርናው ባሻገር በተጨባጭ እጅዋ ላይ ያሉ የብልፅግናዋ መሠረት የሆኑ ሀብቶች አላት፡፡ ከእነዚህ አንዱም ቱሪዝም ነው፡፡ የኢትዮጵያን ቱሪዝም ዘርፍ ከግብርናው የሚለየው ሊለማ በሚችልበት ልክ ያልለማና ዘርፉ ሊሸከመው በሚችለው ልክ ዜጎች ተሰማረተው እየኖሩበት ያለመሆኑ ነው።

የኢትዮጵያ ቱሪዝም እንደዘርፍ ትኩረት ስቦ በተቋም መመራት ከጀመረ ከግማሽ ክፍለ ዘመን በላይ ያስቆጠረ ቢሆንም አሁንም ገና ያልተነካና በእምቅነት ደረጃ ያለ ነው ማለት ይቻላል። አጠቃላይ ኢኮኖሚውንም ትራንስፎርም የማድረግ አቅም ግዙፍ ስለመሆኑ አጠያያቂ አይደለም፡፡

እንደሚታወቀው በርካታ ሀገራት በተፈጥሮ የታደሉ ከሆኑ፣ ለዓለም የሚያሳዩት እጅግም ሰፊ ታሪክ አይኖራቸውም፡፡ አንዳንድ የድንቅ ታሪክ ባለቤት የሆኑ ሀገራት ደግሞ፣ እዚህ ግባ የሚባል የተፈጥሮ ሀብትና ውበት ባለቤቶች ሆነው አይገኙም፡፡ ኢትዮጵያችን ግን በዓለማችን ድንቅ ታሪክን፣ ተፈጥሯዊ ውበትንና ባህላዊ ፀጋዎችን በገፍ ታድለው ከተጎናፀፉ ውሱን ሀገራት መካከል የምትመደብ ናት፡፡

ኢትዮጵያ ውበት ተመልካች አጥቶ ገረጣ እንጂ አልሞተም፡፡ አቧራ ተጭኖት ደበዘዘ እንጂ ከነጭራሹ አልጠፋም፡፡ ኢትዮጵያ አሁንም ሊወጡ የሚችሉ ብዙ አስደማሚ የውበት ፀጋዎችን ታድላለች፡፡ ሀገራችን ጥበበኞች በአድናቆት የሰላ ብዕራቸውን ቀለም የሚያንቆረቁሩባት፣ ተአምራትን መፍጠር የሚያስችል እምቅ ውበት ባለቤት ናት፡፡

ሀገሪቱ ወደ ሀብት ሊቀየሩ የሚችሉው በርካታ ሀብቶች ቢኖራትም፣ ሀብቶቿን ከተደበቁበት የሚያወጣላት ግን ሳታገኝ ቆይታለች፡፡ ‹‹ይህን መቀየርና ኅብረተሰቡንም ሀገርንም ተጠቃሚ ማድረግ ይቻላል›› የሚሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድም (ዶ/ር) ከሸገር ፕሮጀክት፣ የአንድነት ፓርክንና የእንጦጦ ፓርክን እውን ለማድረግ ቀጥለው በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች የተለያዩ ሜጋ ፕሮጀክቶችን አስተዋውቀዋል፡፡

የሸገር ፕሮጀክቶችን ወደ ክልሎች ለማስፋፋት፣ ሁሉም ከኢትዮጵያ ሀብቶች ተቋዳሽ የሚሆንበትን ዕድል ለማመቻቸት ያለመና ‹‹ገበታ ለሀገር›› የተሰኘ ፕሮጀክት በሀገሪቱ በተለያዩ ሥፍራዎች የቱሪዝም መዳረሻዎችን የማልማት ሥራ ተግባራዊ አድርገዋል። በመልክአ ምድር አቀማመጡና በተፈጥሯዊ ውበቱ፣ መንፈስን በሚያድሰው ምቹ አየሩ እና አፍን በእጅ የሚያስይዝ ምትሃታዊ የውበት ጥግነቱ የሚታወቀው የወንጪ ሐይቅ፣ በመንግሥት የገበታ ለሀገር ከለሙ ፕሮጀክቶች መካከል አንዱ ነው፡፡

ኢትዮጵያ ከሚገኙ መስሕቦች ሁሉ በመልከዓ ምድራዊ ውበቱ፣ ልብን በሐሴት በሚሞላው አስገራሚ የተፈጥሮ ፀጋና ሀብቱ በቀዳሚነት የሚቀመጠውና ‹‹የአፍሪካ ስዊዘርላንድ›› በሚል ቅፅል ስሙ በጎብኚዎች ዘንድ የሚታወቀው የወንጪ ሐይቅ፣ በቅርቡ ተመርቆ አገልግሎት መሥጠት መጀመሩ የሚታወስ ነው፡፡

የእነዚህና ሌሎች ፕሮጀክቶች መጠናቀቅ ታዲያ የሀገሪቱን የቱሪዝም ዘርፍ አቅም ይበልጥ በማጎልበት ከዘርፉ የሚገኘውንም ጥቅም ከፍ ለማድረግ ሁለንተናዊ ፋይዳው ከፍተኛ መሆኑ የሚያከራክር አይሆንም። ይሁንና የቱሪዝም ተስፋ እንዲሰምር የመዳረሻ ስፍራዎች በማልማት፣ በማስተዋወቅ፣ ጎብኚዎችን በመሳብና አዳዲስ መዳረሻዎችን ከመፍጠር ባሻገር መሰል ድንቅ ሀብቶችን ከተደበቁበት እንደማውጣት ሁሉ ከሀብቱ በሚፈለገው መጠን ተጠቃሚ ስለመሆን መጨነቅም የግድ ነው፡፡

ቀጣዩን የሀገሪቱ የቱሪዝም ኢኮኖሚ የተሸከመው ባቡር እጅጉን ግዙፍ መሆኑ እየታየ ነው፡፡ እንደ መነሻው ሁሉ መድረሻው ከፍ ያለ ስፍራ ስለመሆኑን ከወዲሁ እያስመለከተ ይገኛል፡፡ ይህ እስከሆነም በትንሹ ሳይሆን በትልቁ ማሰብና ማቀድ እንዲሁም መሥራት የግድ ይላል፡፡

በእነዚህ ሜጋ ፕሮጀክቶች ምክንያት የባህልና የቱሪዝም ቁሳቁሶችን ለገበያ በማቅረብ ላይ የተሰማሩ፣ ጉዞ ወኪሎች እና አስጎብኚ ድርጅቶችን ጨምሮ በርካታ የዘርፉ ተዋናዮች ከፊታቸው ትልቅ መና እየጠበቃቸው ነው፡፡ ስለሆነም ይህን መና በአግባቡ ስለመቋደስ ከወዲሁ ዝግጅታቸው ጨርሰው ወደ ሥራ መግባት ይኖርባቸዋል፡፡ በተለይ የሀገርም ሆነ የውጭ ሀገራት ጎብኚዎች እነዚህን መዳረሻዎች ቀዳሚ ምርጫ ከማድረግ ባለፈ የቆይታ ጊዜያቸውን እንዲያራዝሙ ተግቶ መሥራት ይገባል፡፡ ይህ ግን ቀላል ሥራ አይደለም። መስጠትን አቅዶ ማልማትን ይጠይቃል።

የክልልና የከተማ አስተዳደሮችና በተለይ የቱሪዝምና የኢንቨስትመን፣ የመሠረተልማትና ሌሎችም ተቋማት ይህን ግዙፍ ኢኮኖሚ ተሸክሞ የመጣ ባቡር በአግባቡ ስለመጠቀም በፅኑ መትጋት ይኖርባቸዋል፡፡ ይህ የቤት ሥራም ከነገ ሳይሆን ከዛሬ የሚጀምር መሆኑም ጠንቅቀው መረዳት ግድ ይላቸዋል፡፡ የሥራ ዕድል ፈጠራ ላይ የሚሠሩ ባለድርሻ አካላትም ዘርፉ እንደ ቀድሞው በልምድ ሳይሆን በእውቀት የሚመራበትን መንገድ መቀየስ እና የሰለጠኑ ሙያተኞች ዘርፉን የሚቀላቀሉበት ብሎም ለሁለንተናዊ ለውጥና አበርክቶቱ አጋዥ የሚሆኑበትን ድልድይ መሥራት ይኖርባቸዋል፡፡

ጉዳዩ ከብሔራዊ ጥቅም National Interest ጋር የሚቆራኝ እንደመሆኑ ከፖሊሲ ማዕቀፍ እስከ ትግበራ እነዚህን የቱሪዝም አቅሞች የበለጠ ለመጠቀምና ሀገርን ለተቀረው ዓለም ይበልጥ ለማስተዋወቅ ዘርፉን የሚመሩ ተቋማት ብሎም የግልም ሆነ የመንግሥት መገናኛ ብዙኃንም ትልቅ ኃላፊነት እንዳለባቸው መዘንጋት አይኖርባቸውም፡፡

በመንግሥት በኩል ሰላምን ማረጋገጥ ጨምሮ የመሠረተ ልማት፣ የተፈጥሮና የባህል ቅርሶችን መንከባከብና ማልማት፣ የአገልግሎት አሰጣጥን የላቀ ማድረግ፣ የባህልና የቱሪዝም የመረጃ ሥርዓትን ማሻሻልን ጨምሮ የልማት አጋሮችን በማቀናጀት የተለያዩ ተግባራት መከወን ሊዘነጋ አይገባም፡፡

በቱሪዝም ዘርፍ ለመሰማራት ለሚፈልጉ የግል ባለሀብቶች የመንግሥትም ይሁኑ የግል ባንኮች ብድር የሚያመቻቹበት ሁኔታም ሊፈጠር ይገባል፡፡ ከከተማ እስከ ሀገር በሚዘልቀው ቀጣዩ ግዙፍ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ ባቡር ለመሳፈርና ከምንሻው እድገት ለመድረስም፣ ሁሉም አካላት ከወዲሁ እጅ ለእጅ በመያያዝ በቅንጅት ሊሠሩ የግድ ይላል፡፡

# ዓለም አቀፍ



## በሶማሊያ በተፈጸመ የሽብር ጥቃት የኤምሬትስና ባሕሬን ወታደሮች ተገደሉ

በጋዜጣው ሪፖርተር

በሶማሊያ ሞቃዲሾ በተፈጸመ ጥቃት ሦስት የዓረብ ኤምሬትስ እና አንድ የባሕሬን ወታደሮች ተገደሉ።

የኤምሬትስ መከላከያ ሚኒስቴር እንዳስታወቀው በመዲናዋ ሞቃዲሾ በሚገኝ ወታደራዊ ማሠልጠኛ ጣቢያ በተፈጸመው "የሽብር ጥቃት" ሁለት ወታደሮችም ቆስለዋል።

ጥቃቱን ያወገዘው ሚኒስቴሩ ከሶማሊያ መንግሥት ጋር በመሆን መንስዔውን እንደሚመረምር መግለጹንም የኤምሬትስ የዜና ወኪል ዋም ዘግቧል።

የኤምሬትስ ወታደሮች የሶማሊያ መንግሥት ጦርን በማሠልጠን ላይ መሆናቸው የሚታወቅ ሲሆን፥ ጥቃቱም ይህንኑ ወታደራዊ ትብብር የሚገታው አይሆንም ብሏል የኤምሬትስ መከላከያ ሚኒስቴር።

የሶማሊያው ፕሬዚዳንት ሀሰን ሼክ መሐመድ ወታደሮቿ ለተገደሉባት ኤምሬትስ የኀዘን መግለጫ መላካቸው ተሰምቷል።

ከአልቃይዳ ጋር ግንኙነት ያለው የሽብር ቡድን አልሸባብ በዛሬው እለት ባወጣው መግለጫ አራት ወታደሮች ለተገደሉበት ጥቃት ኃላፊነቱ እንደሚወስድ መግለጹን አሶሼትድ ፕሬስ ዘግቧል።

በጄኔራል ጎርደን የጦር ሰፈር በሚገኙት የኤምሬትስ እና ባሕሬን ወታደሮች ላይ ጥቃቱን ያደረሰውም ሀገራቱ የሸሪዓ ሕግን በመተላለፍ የሶማሊያ መንግሥትን በመደገፋቸው መሆኑን ነው ያስታወቀው።

የሶማሊያው ፕሬዚዳንት ሀሰን ሼክ መሐመድ ዳግም ወደ ሥልጣን ከመጡ ወዲህ በአልሸባብ ላይ ጦርነት ማወጃቸውና በርካታ ከተሞችን ከቡድኑ ማስለቀቃቸውን መግለጻቸው ይታወሳል።

ቡድኑ ይህን እንቅስቃሴ በሚደግፉ ሀገራት ላይም በተለያየ ጊዜ ጥቃት ማድረሱ አይዘነጋም።

የሶማሊያ መንግስት በአልሸባብ ላይ የሚወስደውን እርምጃ የምትደግፈው ኤምሬትስ የሶማሊያ የባሕር ላይ ወንበዴዎች የኤደን ባሕረሰላጤ እና የዓረቢያን ባሕር ደህንነት ስጋት ውስጥ እንዳይጥሉት ስጋት አላት።

አልሸባብ በ2019 የዱባይ ፒ ኤንድ ኦ ፖርትስ ሠራተኛን መግደሉን ማሳወቁም ኤምሬትስን እንደ "ጠላት" መፈረጁን ያሳያል ብሏል አሶሼትድ ፕሬስ በዘገባው።

## ትራምፕ ሩሲያ የኔቶ አባል ሀገራትን እንድታጠቃ "እንደሚያበረታቱ" ተናገሩ

በጋዜጣው ሪፖርተር



**ዋይትሃውስ በበኩሉ የዶናልድ ትራምፕ አስተያየት "አስደንጋጭና ወረራን የሚያበረታታ" ነው ብሎታል**

የአሜሪካው የቀድሞ ፕሬዚዳንት ዶናልድ ትራምፕ ሩሲያ ለኔቶ ዓመታዊ መዋጯቸውን በሚገባ የማይከፍሉ ሀገራትን እንድታጠቃ አበረታታለሁ አሉ።

ትራምፕ በሳውዝ ካሮሎና በምርጫ ቅስቀሳ ሲያደርጉ 31 አባል ያለውን ቡድን ተቀላቅለው ነገር ግን መዋጮ በሚገባ የማይከፍሉ ሀገራትን "ወንጀለኛ" ናቸው ሲሉ ተደምጠዋል።

በአንድ የኔቶ ስብሰባ ላይ ስማቸውን ካልጠቀሷቸው መሪ "መዋጮ ካልከፈልን እና በሩሲያ ከተወረርን ትከላከሉልናላችሁ?" የሚል ጥያቄ ተነስቶላቸው "አንዋጋላችሁም፤ እንደውም (ሩሲያ) የፈለገችውን እንድታደርግ አበረታታለሁ" ማለታቸውንም አውስተዋል።

የሰሜን አትላንቲክ ጦር ቃልኪዳን ድርጅት ኔቶ ከ2006 ጀምሮ አባል ሀገራቱ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርታቸው(ጂዲፒ) 2 በመቶውን ወታደራዊ ኃይላቸውን ማጠናከሪያ በጀት ለመያዝ ተስማምተዋል።

ስምምነቱ የወታደራዊ ጥምረቱን ለየትኛውም ጥቃት ዝግጁነትና አንዱ ለአንዱ ደራሽነት ያሳድጋል ተብሎ ቢጠበቅም የአሜሪካ ዓመታዊ በጀት ከቀሪዎቹ አባል ሀገራት ድምር የሚስተካከል ነው።

ይህም የአሜሪካን ዓመታዊ መዋጮ እንዲበዛ ማድረጉ የሚነገር ሲሆን፥ ሀገራቱ በ1949 ለተመሠረተው ኔቶ የሚያዋጡትን ክፍያ በመፈጸም ረገድም ተደጋጋሚ ወቀሳ ይቀርብባቸዋል።

የትራምፕ አስተያየትም ወታደራዊ በጀቷ ከ860 ቢሊዮን ዶላር በላይ የሆነው አሜሪካ መዋጯቸውን በሚገባ የማይከፍሉ 30 ሀገራትን ከጥቃት የመከላከል ግዴታ የለባትም ያሉት ከዚህ በመነሳት ነው።

ዋይትሐውስ ግን የቀድሞው ፕሬዚዳንት አስተያየት "ያልተገራና አስደንጋጭ" ነው ብሏል።

የትራምፕ አስተያየት ወረራን የሚያበረታታና የአንዱ አባል ሀገር ወረራን እንደራሱ የሚመለከተውን የኔቶ መርሕ የጣሰ ነው በሚልም ተቃውሞታል።

አወዛጋቢው የቀድሞ ፕሬዚዳንት በ2024ቱ የምርጫ ቅስቀሳቸው አስቀድሞም ሀገራቸውን ፍትሐዊ ላልሆነ ወጪ እየዳረገ ነው የሚሉትን ኔቶ አንዱ አጀንዳቸው አድርገውታል ሲል የዘገበው አል ዓይን ነው።

# ስፖርት





# የሃዋሳ ሐይቅ የግማሽ ማራቶን ሩጫ ለ12ኛ ጊዜ ተካሄደ

ብርሃን ፈይሳ

በሃዋሳ ሐይቅ የግማሽ ማራቶን ሩጫ በግላቸው የተሳተፉ አትሌቶች በበላይነት አጠናቀዋል። ውድድሩ በርካታ አትሌቶች፣ የውጪ ሀገር ዜጎች፣ የሐዋሳ ከተማ ነዋሪዎች እንዲሁም ሕጻናትን በማሳተፍ ትናንት ለ12ኛ ጊዜ ተካሂዷል።

በዓመት ውስጥ በርካታ የጎዳና ላይ የሩጫ ውድድሮችን በማዘጋጀት የሚታወቀው ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ከሚያካሂዳቸው ዓለም አቀፍ ውድድሮች ይህ ሁለተኛው ነው። ውቢቷና ለአትሌቲክስ ስፖርት ምቹ የሆነችው ሀዋሳ በየዓመቱ በርካቶች የሚሳተፉበትን ይህንን ውድድር ስታስተናግድ ከኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ባለፈ የቱሪዝም ፍሠቱን ከመጨመር አንጻር ከፍተኛ ጠቀሜታ እንደምታገኝበት ይጠበቃል።

ሃያ አንድ ኪሎ ሜትር በሚፈጀው ውድድር ላይ ከክለቦች የተወጣጡ እንዲሁም በግላቸው 150 የሚሆኑ አትሌቶች ተሳትፈውበታል። ከ400 በላይ የሚሆኑ የጤና ሯጮችም የውድድሩ አካል ሲሆኑ፤ 35 የሚሆኑት ከእንግሊዝ ሀገር የመጡና አንዱ ደግሞ የዊልቸር ተሳታፊ ናቸው። ሕዝባዊው ሩጫ ደግሞ በ8 ኪሎ ሜትር 3ሺ500 ነዋሪዎችን እንዲሁም ሕጻናትን አሳትፏል። በሩጫው ዋዜማም የታቦር ተራራን የመውጣት መርሐ ግብር ተከናውኗል።

በሀዋሳ ሐይቅ የግማሽ ማራቶን ውድድር የኦሪገን ዓለም የማራቶን ቻምፒዮናውን ታምራት ቶላን



በወንድ አትሌቶች መካከል በተደረገው ጠንካራ ፉክክር እንየው ንጋት በግል አሸንፏል፣

የመሳሰሉ ስመጥር አትሌቶች አፍርቷል። ዘንድሮም በርካታ ልምድ ያላቸውን አትሌቶች በማሳተፍ ጠንካራ ፉክክር አስተናግዷል። በዚህም በሴቶች የግል ተሳታፊዎቹ አትሌት ሙላት ተክሉ 1:15:05፣ ክለልቱ ካያሞ 1:15 :19 እንዲሁም ጽግነሽ መኮንን 1:15:24 በሆነ ሰዓት ተከታትለው በመግባት ከወርቅ እስከ ነሐስ ያለውን ሜዳሊያ ወስደዋል።

ርቀቱን ከአንድ ሰዓት በታች በመሸፈን የ100 ሺ ብር ጉርሻ ለማግኘት በወንድ አትሌቶች መካከል በተደረገው ጠንካራ ፉክክር እንየው ንጋት በግል አሸንፏል። አትሌቱ ክብረወሰኑን መስበር ባይችልም የገባበት ሰዓት 1:02:40 ሆኖ ተመዝግቧል። ከግሎባል ከተማና ከጎላዞ አትሌቲክስ ክለብ ተከትለውት የገቡት አትሌት አሰፋ ተፈራ እና ደበበ ተካ ደግሞ 1:02:47 እንዲሁም 1:03:04 ማጠናቀቅ ችለዋል።

ውድድሩን ተከትሎም የሀዋሳ ከተማ ከንቲባ መኩሪያ መርሻዬ ይህን መሠል ስፖርታዊ ኩነቶች ለከተማዋ እጅግ ጠቃሚ መሆኑን ገልፀዋል። በቱሪስቶች ዘንድ ተመራጭ የሆነችው ሀዋሳ ሃይማኖታዊ፣ ባሕላዊና መሠል ሕዝባዊ ኩነቶችን በማዘጋጀት ትታወቃለች። የከተማዋ ነዋሪም ስፖርትን ባሕሉ ያደረገ ብቁ ማኅበረሰብ እንዲሆን ጠቃሚ ልምድ እንዲሆነውና ጤናውን እንዲጠብቅ ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ከፍተኛ ሚና መጫወቱንም ተናግረዋል።

ከስፖርት ቱሪዝም ጋር በተያያዘ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ የሚገኘው የኢፌዴሪ ቱሪዝም ሚኒስትር የዚህ ውድድር አጋር ነው። ይህንንም ተከትሎ ሚኒስትር ዴኤታዋ ሌንሳ መኮንን ሩጫ በዓለም አቀፍ ደረጃ ኢትዮጵያ የታወቀችበትና ሰንደቋን ከፍ ያደረጉ ትልልቅ አትሌቶች የተገኙበት ስፖርት መሆኑን በማስታወስ፣ ፉክክር ባሕሪው ለሆነው የሰው ልጅ የጤናማ ፉክክር መገለጫ የሆነው ስፖርት ነው ብለዋል። በመሆኑም የሩጫ ውድድር የሚያዘጋጀው ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ከውድድሩ ባለፈ ቱሪዝም ላይ የሚያከናውነው ተግባር ሊበረታታ እንደሚገባም ጠቁመዋል።